# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 231 ሚያዝያ 21 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!










# ልጓም የሚሻው የጥላቻ ንግግር ስርጭት

**ዜና ትንታኔ**

**አዲሱ ገረመው**

የማህበራዊ ሚዲያ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የጥላቻ ንግግሮች፣ ግጭት ቀስቃሽ እና የሀገርን ጥቅም የሚጎዱ ይዘቶችን እንዳያሰራጩ ቢደነገግም በሚገባው ልክ ተፈጻሚ ማድረግ አለመቻላቸው ይገለጻል። በዚህም የጥላቻ ንግግር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ በመምጣቱ የችግሩ ሁኔታም አጣዳፊ መፍትሔ እንደሚሻ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

የጥላቻ ንግግር ሥርጭት መዘዝ የሚከፋው ደግሞ የማህራዊ ሚዲያ ተጠቃሚው ማኅበረሰብ ሰፊ ሆኖ ሲገኝ ነው። የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን ሪፖርት እንደሚያሳየው እኤአ በ2023 በኢትዮጵያ የማህበራዊ ሚዲያ

ልጓም የሚሻው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል











## 50 በመቶ ኢትዮጵያዊያን የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ አይደሉም

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- 50 በመቶ የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን ኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ባለመሆናቸው አሁንም በጨለማ እየኖሩ እንደሚገኙ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በሚኒስቴሩ የኤሌክትሪፊኬሽንና ኢነርጂ መረጃ መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ መስፍን ዳቢ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ 50 በመቶ የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን

50 በመቶ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ‘ፐብሊክ ዲፕሎማሲ’ በኢትዮጵያ ላይ ሊጣሉ የነበሩ ማዕቀቦች እንዲከሽፉ አድርጓል

ገጽ 4



## «ኮሚሽኑ ወደኋላ የሚጎትቱትን ጉዳዮች እያለፈ ምክክሩን ማስጀመር ይገባዋል»

\- ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ
የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- ኮሚሽኑ ወደኋላ የሚጎትቱትን ጉዳዮች እያለፈ ምክክሩን ማስጀመር ይገባዋል ሲሉ የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ተናገሩ።

ፕሮፌሰር በየነ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኮሚሽኑ በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች ውስጥ የውይይት መድረክ ፈጥሮ ለማወያየት መቻሉ ላይ ትልቅ ተግዳሮት እንዳለበት በጉልህ የሚታይ ነው። ሆኖም ወደኋላ የሚጎትቱትን ጉዳዮች እያለፈ ምክክሩን ማስጀመር ይገባዋል።

በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች ያለው የሰላም ሁኔታ ለኮሚሽኑ ሥራ ጎታች ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የኢንስቲትዩቱ ምክር ሰላማዊ በሆኑ የሀገሪቱ ክፍሎች ምክክሮችን እያካሄዳችሁ ቆዩ የሚል መሆኑንም አስታውቀዋል።

የቀሩ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደግሞ ምቹ ሁኔታዎች ሲፈጠር እየገቡ

«ኮሚሽኑ ወደኋላ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




MOTRI
የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Regional Integration

# ከአንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን በላይ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት በ"ኦንላይን' ተሰጥቷል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት ውስጥ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ1 ነጥብ 8 ሚሊዮን በላይ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት በኦንላይን መሰጠቱን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር የዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያ አቶ ተስፋዬ ታደሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሚኒስቴሩ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥን ዲጂታል በማድረግ በኩል የሀገሪቱን ንግድን ለመጀመርና ለመስራት ያለውን የአመችነት ደረጃ ለማሻሻል በከፍተኛ ትኩረት እየተሠራ ይገኛል፡፡

በዚህም በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት በሀገር አቀፍ ደረጃ 2 ሚሊዮን 638 ሺህ 83 የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቶችን በኦንላይን ለመስጠት ታቅዶ አንድ ሚሊዮን 816 ሺህ 41 የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቶችን በኦንላይን መስጠት ተችሏል ብለዋል፡፡

የአገልግሎት አሰጣጡን ለማዘመን በተሠሩ ሥራዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ የኦንላይን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ ሽፋኑን 90 በመቶ ማድረስ የተቻለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በኦንላይን ከተሰጡት አገልግሎቶች ውስጥም አዲስ የንግድ ምዝገባ፣ አዲስ የንግድ ፈቃድ፣ የንግድ ፍቃድ እድሳት እና ማሻሻያ እንዲሁም የንግድ ስምና የንግድ ፈቃድ ስረዛ የመሳሰሉትን ጨምሮ በሚኒስቴሩ የሚሰጡ አስራ ዘጠኝ የተለያዩ አገልግሎቶች መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡

የንግዱ ማህበረብ ቴክኖሎጂውን በመጠቀም ባለበት ቦታ ሆኖ እንዴት አገልግሎቱን ማግኘት እንደሚችል የግንዛቤ እና የክህሎት ስልጠና መሰጠቱን ገልጸው፤ ኦንላይን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓቱን ከወረዳ ኔት ጋር የማስተሳሰር ሥራ በመሥራት ሽፋኑን ከፍ ለማድረግ አስችሏል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ኦንላይን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ ሽፋኑን ለማሳደግ በተለይም አገልግሎቱ ባልተጀመረባቸው አካባቢዎች ላሉ የንግድ ዘርፍ አገልግሎት ሰጪ ባለሙያዎች የተግባር ስልጠናዎችን በመስጠትና አስፈላጊውን ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ የማብቃት ሥራም ተሠርቷል ብለዋል፡፡

ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ የሚሰጠውን የንግድ ምዝገባ እና ፍቃድ የአገልግሎት ሥርዓትን በመተግበርና በማዘመን እየተሠራ ነው የሚሉት አቶ ተስፋዬ፤ ይህም ለደንበኞች የሚሰጠውን አገልግሎት በማቀላጠፍ ከአላስፈላጊ እንግልት የሚያስቀር ነው ብለዋል፡፡


አቶ ተስፋዬ እንደሚገልጹት፤ የተደረገውን የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ተከትሎ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ባካሄደው የተገልጋዮች አስተያየት ጥናት የተገልጋዮች እርካታ 93 በመቶ ማድረስ መቻሉን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በዘርፉ የሚስተዋለውን ብልሹ አሠራርና ሕገ ወጥነት በማላቀቅና ሕጋዊ የአሠራር ሥርዓትና የሕግ ማእቀፍ ለመዘርጋት በትኩረት የሚሠራ መሆኑንም አቶ ተስፋዬ ጠቅሰዋል፡፡

# በፓርኩ ቃጠሎ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቋቋም ሀገር በቀል ዕጽዋት እየተተከሉ ነው

## - ዘንድሮ ከ125 ሺህ በላይ ሀገር በቀል ችግኞች ይተከላሉ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**



አዲስ አበባ፡- በሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ በየጊዜው የሚነሳውን የእሳት ቃጠሎ የሚያደርሰውን ጉዳት መቋቋም እንዲቻል ሀገር በቀል እጽዋት እየተተከሉ መሆኑን የኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ጥበቃ ባለስልጣን አስታወቀ፡፡ ዘንድሮ ከ125 ሺህ በላይ ሀገር በቀል ችግኞች እንደሚተከሉም ተነግሯል፡፡

የባለስልጣኑ የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒዩኬሽን ጉዳዮች ዋና ሥራ አስፈጻሚ ተወካይ አቶ ናቃቸው ብርሌው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ በየጊዜው የሚደርሰው ቃጠሎ ብርቅዬ እጽዋቶች ላይ የመጥፋት አደጋ እንዳይደቅን ሀገር በቀል እጽዋት እየተተከሉ ነው፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት በ353 ሄክታር መሬት ላይ 557 ሺህ ሀገር በቀል እጽዋት ተተክለዋል ያሉት አቶ ናቃቸው፤ በዘንድሮ አረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብርም ከ125 ሺህ በላይ ሀገር በቀል እጽዋቶች ለመትከል ዝግጅት መደረጉን ተናግረዋል፡፡

አቶ ናቃቸው አክለውም፤ በፓርኩ ሀገር በቀል እጽዋትን ከመትከልና ለማህበረሰቡ ግንዛቤ ከማስጨበጥ ጎን ለጎን በፓርኩ የተለያዩ ጉዳት በሚያደርሱ አካላት ላይ እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል ብለዋል፡፡

በተደጋጋሚ እሳት ሲነሳ ጉዳት የሚያደርሰው ጥብቅ ደን እንዲሁም ሳር ላይ ነው ያሉ ሲሆን፤ ከዚህ በፊት አካባቢው እንዲያገግም በውስጥ ያሉ ዝርያዎች መርጦ የመተካት ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቁመዋል፡፡

ወይራ፣ ጽድ፣ የኮሶ ዛፎች እንዲሁም መሰል ብርቅዬ እጽዋት ፓርኩ ወደ ነበረበት ተመልሶ እንዲያገግም ከተተከሉት መካከል ተጠቃሽ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

በፓርኩ በተደጋጋሚ ጊዜ የሚከሰተው ቃጠሎ በዘላቂነት መቆጣጠር እንዲቻል ሕገወጥ ተግባራት የሚከናወኑ አካላት ላይ እርምጃ በመውሰድ ተገቢውን ቅጣት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚያስፈልግም ነው አቶ ናቃቸው ያብራሩት፡፡

የእሳት ቃጠሎው ያደረሰው የጉዳት መጠንና ምክንያቱ ምን እንደነበር ለማወቅ ኮሚቴ ተዋቅሮ ዳሰሳ እየተደረገ መሆኑን አቶ ናቃቸው ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ ናቃቸው ገለጻ፤ በፓርኩ በሦስት ቦታዎች የእሳት ቃጠሎ ተከስቶ ለመቆጣጠር ከፍተኛ ትግል ቢጠይቅም በፓርኩ ባለሙያዎች፣ በማህበረሰቡ ተሳትፎና በዞኑ መንግሥት በተደረገ ርብርብ ሙሉ ለሙሉ መቆጣጠር ተችሏል፡፡




# የጨረር ሕክምናው መጀመር ሲጉላሉ ለነበሩ ታካሚዎች ዕረፍት የሚሰጥ ነው

**በዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የጨረር ሕክምናው መጀመር ሲጉላሉ ለነበሩ ታካሚዎች እረፍት እንደሚሰጥ የሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሕክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የካንሰር ህክምና ማዕከል አሳወቀ፡፡

የሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሕክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የካንሰር ሕክምና ማዕከል በቅርብ ቀናት የጨረር ሕክምና መስጠት ይጀምራል፡፡

የኮሌጁ ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር አለሙ ጣሚሶ (ተ/ፕሮፌሰር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ማዕከሉ ቀድሞ እየሰጠ ከሚገኘው የካንሰር ሕክምና በተጨማሪ ዘመናዊ የጨረር ሕክምና መስጫ አስመርቆ ለማስጀመር ዝግጅቱን አጠናቋል፡፡ በዚህም ለመጀመሪያ ዙር ፈቃደኛ ሆነው በተገኙ 30 አካባቢ ታካሚዎች በመጪው ሰኞ የጨረር ሕክምና አገልግሎት መስጠት ይጀምራል፡፡

በዳይሬክተሩ ንግግር መሠረት፤ የሀዋሳና አካባቢው ነዋሪዎች ከዚህ ቀደም የጨረር ሕክምናውን ለማግኘት ጅማ ድረስ መጓዝ ይጠበቅባቸው ነበር፡፡ ሕክምናው እንደሚያስፈልጋቸው ከተረጋገጠ በኋላም እስከ አንድ ዓመት ድረስ ሲጠብቁ ቆይተዋል፡፡ የሕክምናው በከተማዋ መጀመር ይህን ድካምና መጉላላት የሚያስቀም ነው፡፡

የጨረር ሕክምናው ለሀዋሳ ከተማ ብሎም ለደቡብ ኢትዮጵያና ለአጎራባች ታካሚዎች በሙሉ ማገልገል የሚያስችል መሆኑንም ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተሩ በንግግራቸው ጨምረው ገልጸዋል፡፡

ማሽኑ የተለያዩ የሙከራ ሂደቶችን ማለፉን ያመላከቱት ዳይሬክተሩ፤ ከጨረር ኤጀንሲና የውሃ ሙከራውን በማለፍም ለቀጣይ የሕክምና ሂደት ተዘጋጅቷል ብለዋል፡፡

ማሽኑ በሆስፒታሉ በተያዘው በጀት ዓመት መተከሉን ያመላከቱት ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተሩ፤ በተለያዩ ምክንያቶች አገልግሎት ሳይሰጥ መክረሙን በመግለፅ አሁን ግን በሀገር ውስጥና ከደቡብ አፍሪካ በመጡ ባለሙያዎች አገልግሎት የመጀመር ሂደት ላይ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ባለሙያዎችን የማሰልጠንና የማብቃት ሥራዎች ሲሠሩ መክረማቸውን የገለጹት ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተሩ፤ በሕክምና አሰጣጥ ሥርዓቱ ላይም በስልጠናው ያገኙትን እውቀትና ክህሎት ተግባራዊ የሚያደርጉበት አግባብ ስለመኖሩ አንስተዋል፡፡

በዘርፉ ያለውን የማዕከላት ውስንነት ለመቅረፍ በአዲስ አበባ ብቻ ተወስኖ የቆየው የካንሰር ሕክምና ማዕከል በሐረር፣ ጅማ፣ ሀዋሳና ጎንደር በማዳረስ የሕክምናውን አድማስ ለማስፋት ሥራዎች መከናወናቸው ይታወቃል፡፡

# በጂኦተርማል ዘርፍ የሰው ኃይል አቅምን ለማሳደግ ትኩረት ተሰጥቷል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የጂኦተርማል ልማት የሚያስፈልገውን ቴክኖሎጂ ለማሟላት መንግሥት የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎችን በሀገርና በውጭ ሀገራት በማመቻቸት የሰው ኃይል አቅም እያሳደገ እንደሚገኝ የማዕድን ሚኒስቴር አስታወቀ።

የማዕድን ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሚሊዮን ማቲዎስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የጂኦተርማል ልማት የሚፈልገውን ቴክኖሎጂ ለማሟላት መንግሥት የተለያዩ ስልጠናዎችን እያመቻቸ ነው።

የአካባቢ ማህበረሰብን በተለያዩ ሥራዎች በማሳተፍ ለወጣቶች ስልጠና እንዲያገኙ ድርጅቶቹ እየሠሩ ይገኛሉ ያሉት አቶ ሚሊዮን፤ የሀገር ውስጥ ልምድ ያለው ባለሙያ ባይኖር እንኳን ከውጭ ከሚመጡ ባለሙያዎች ጋር በማካተት ልምድ እንዲያገኙ እየተደረገ መሆኑንም ተናግረዋል።

ማዕድንና ጂኦተርማል ዘርፍ የምርመራና የጥልቅ ቁፋሮ ሥራ የሚከናወንበት በመሆኑ ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ ይፈልጋል ያሉት አቶ ሚሊዮን፤ በዚህም የውጭ ባለሀብቶች በዘርፉ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ሁኔታዎች እየተመቻቹ መሆኑን ጠቁመዋል።



አቶ ሚሊዮን ማቲዎስ

በተጨማሪም የሀገር ውስጥ ተቋራጮች ተወዳድረው ሥራውን እንዲያከናውኑ እየተደረገ እንደሚገኝ አብራርተዋል።

አቶ ሚሊዮን አክለውም፤ ስድስት የተለያዩ ሀገራት ባለሀብቶች እንዲሁም አንድ የመንግሥት ተቋም በዘርፉ ተሰማርተዋል ያሉ ሲሆን፤ 11 የፍለጋና የማልማት ፈቃዶች በማውጣት ሥራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኙ አስረድተዋል።

እንደ አቶ ሚሊዮን ገለጻ፤ በኢትዮጵያ በተደረገ ጂኦሎጅካል ሰርቬ እስካሁን 27 የሚሆኑ ከፍተኛ ሙቀት ያላቸው የጂኦተርማል አለኝታ ቦታዎች ኤሌክትሪክ ማመንጨት ይችላሉ። ኢትዮጵያ ከዘርፉ በአጠቃላይ ከአስር ሺህ ሜጋ ዋት በላይ የማመንጨት አቅም አላት።

በማዕድን ዘርፍ ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል መፈጠሩን አያይዘው የተናገሩት አቶ ሚሊዮን፤ በጂኦተርማል ዘርፍ ለ300 ሰዎች የሥራ እድል መፍጠር መቻሉን ገልጸዋል።

የጂኦተርማል ዘርፍ ከፍተኛ ሀብት የሚጠይቅ በመሆኑ ሁለት የውጭ ኩባንዎች የኃይል ግዢ ስምምነትና የተግበራ ስምምነት ከመንግሥት ጋር በመፈራረም በሁለት ዙር እያንዳንዳቸው 150 ሜጋ ዋት ለማመንጨት ቁፋሮ እያከናወኑ መሆኑንም ነው አቶ ሚሊዮን ያብራሩት።

አቶ ሚሊዮን፤ በመንግሥት ኩባንያ በኩል 10 ጥልቅ የምርመራ ጉድጓዶች አጠቃላይ ጥልቀታቸው 27 ሺህ ሜትር በላይ መቆፈር የተቻለ ሲሆን ሁለት ተጨማሪ ጉድጓዶች በመቆፈር ላይ ናቸው።



አቶ ፍስሃ ግርማይ

# በክልሉ የማዕድን ምርት ሕጋዊ መልክ እንዲኖረው ሥርዓት እየተዘረጋ ነው

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል የማዕድን ምርት አሠራር ሕጋዊ መልክ እንዲኖረው ሥርዓት እየተዘረጋ መሆኑን የክልሉ የመሬትና ማዕድን ቢሮ አስታወቀ።

የክልሉ መሬትና ማዕድን ቢሮ ዳይሬክተር አቶ ፍስሃ ግርማይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ በክልሉ የተለያዩ ማዕድናት ይገኛሉ። ከጦርነቱ በኋላ ሕገ ወጥ ማዕድን የማውጣት እና የመሸጥ ሥራዎች በመበራከታቸው ይህንን ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት እየተዘረጋ ነው።

በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች በጉልበት እና ሕጋዊ በማስመሰል ያለአግባብ ማዕድን የመዝረፍ ሁኔታዎች እንዳሉ ጠቅሰው፤ ይሁን እንጂ ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር በክልሉ ያለው ፖለቲካዊ አለመረጋጋት በተወሰነ ደረጃ እንቅፋት መሆኑን ገልጸዋል።

ከሕዝብ ጋር በመነጋገር ወደ ሥርዓት ለማስገባት ጥረቶች በማድረግ ጅማሮዎች መኖራቸውን ተናግረዋል።

ከዚህ ቀደም በክልሉ የወርቅ ማዕድን በኮንትሮባንድ ይሸጥ እንደነበር ጠቅሰው፤ ይህንን ለመቅረፍ እና ለመለወጥ በተቻለ መጠን ከሕዝብ እና ከወጣቶች ጋር በመወያየት ሕጋዊ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

ኃላፊው እንዳሉት፤ ሕጉን ተከትለው እየሰሩ የሚገኙት ቀደም ሲል ቦታ ወስደው ሲያለሙ የነበሩ ናቸው። በመሆኑም በጦርነቱ ምክንያት የባከኑትን ጊዜያት ግምት ውስጥ በማስገባት ወደ ሥራ እንዲገቡ መደረጉን ገልጸዋል። ሌሎች አዳዲስ ወጣቶችም ማዕድን የማውጣት ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ተደርጓል።

በአሁን ጊዜ በርካታ ወጣቶች በሕጋዊ መንገድ ለመሥራት በዘርፉ መሰማራታቸውን ጠቅሰው፤ በተቃራኒው ደግሞ ቁጥራቸው የማይናቅ ወጣቶችም በሕገ ወጥ መንገድ እንደተሰማሩ ጠቁመዋል።

ሆኖም ቀደም ሲል ከነበረው አካሄድ አሁን ላይ የቁጥጥር ሥርዓቱ መልክ እየያዘ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

የወርቅ ማዕድን ከሚገኙባቸው አካባቢዎች መካከል በማዕከላዊ ዞን ወርዒ፣ ሽረ፣ ምሥራቃዊ ዞን ገጠራማ አካባቢዎች ተጠቃሽ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ይህንን የሚሠሩት የኅብረት ሥራ ማህበራት አቅማቸው ዝቅተኛ በመሆኑ አቅም ለመፍጠር እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

የማዕድን ምርት አሠራር ሥርዓቱን እንዲጠብቅ እና በሕጋዊ መንገድ እንዲከናወን በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ በክልሉ የሚገኝ ሕዝብ እና ወጣት ለማዕድን ሀብት ትኩረት በመስጠት ከባለ ድርሻ አካላት ጋር መረጃዎችን በመለዋወጥ ጥበቃ ማድረግ ይኖርበታል ሲሉ አሳስበዋል።



# በመዲናዋ ደንብ በሚተላለፉ አካላት ላይ የሚወሰደው ርምጃ ተጠናክሮ ይቀጥላል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ደንብ በሚተላለፉ አካላት ላይ የሚወሰደው ርምጃ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደንብ ማስከበር ባለስልጣን አስታወቀ።

ባለስልጣኑ ከሁሉም ክፍለ ከተማ ከተውጣጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር ውይይት አካሂዷል።

የባለስልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ በወቅቱ እንደገለጹት፤ መዲናዋ ለነዋሪዎቿ ምቹና ውብ እንድትሆን ደንብ በሚተላለፉ አካላት ላይ ቁጥጥር እየተደረገ ነው። ደንብ በሚተላለፉ አካላት ላይ እየተወሰደ ያለው ርምጃም ተጠናክሮ ይቀጥላል።

በቀጣይ በከተማዋ ከተፈቀዱ ቦታዎች ውጪ በዋናና የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ላይ የጉልት ንግድ በሚያካሂዱ፣ ተንጠላጣይ የደላላ ማስታወቂያዎችን በሚሰቅሉና ጫማ በሚጠርጉ አካላት ላይ የተጠናከረ ርምጃ እንደሚወሰድ ሻለቃ ዘሪሁን ገልጸዋል።

በሕዝብ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች የግንባታ ዕቃ በሚያስቀምጡ አካላት ላይ የሚወሰደው ርምጃም በተመሳሳይ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

እንደ ሻለቃ ዘሪሁን ገለጻ፤ በተለይ በከተማዋ በሚገኙ አደባባዮችና መንገዶች ላይ የሚደረጉ ሕገ ወጥ ንግዶች፣ ሕገ ወጥ የቤት ግንባታና መሬት ወረራ ላይ ከሕዝብ ጋር በመተባበር መሥራት በመቻሉ የመዲናዋን ውበት መጠበቅ ተችሏል።

ባለፉት ዘጠኝ ወራት በሁሉም ክፍለ ከተሞች ላይ በተሠራው ሥራ ከ15 ሺህ ኪሎ ግራም በላይ ጤንነቱ ያልተረጋገጠ ስጋ ለሕዝብ ሊቀርብ ሲል መያዙንም አያይዘው ጠቁመዋል።

በተጨማሪም መሬት በሕገ ወጥ መንገድ በግለሰቦች እንዳይወረር በተሠራው ሥራ ከ10 ሚሊዮን ካሬ ሜትር በላይ መሬት ወደ ባንክ መግባቱን አስረድተዋል።

ሕገ ወጥ የጎዳና ላይ ንግድ ኅብረተሰቡን ለዝርፊያና ለትራፊክ አደጋ እያጋለጠ መሆኑን አውስተው፤ ኅብረተሰብን ያሳተፈ ሥራ በመሥራቱ ጎዳናዎች ነፃ ሆነው እግረኞች በነጻነት እየተንቀሳቀሱ ናቸው ብለዋል።

ሻለቃ ዘሪሁን አክለውም ደንብ መተላለፍን ለመቀነስ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ያሉ ሲሆን፤ የመከላከል ሥራው ውጤታማ መሆኑን አመላክተዋል።

ከደንብ ማስከበር ጋር በተገናኘ ከኅብረተሰቡ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመፍታት እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ የሥነ ምግባር ጥሰት በፈጸሙ ደንብ አስከባሪዎች ላይ ርምጃ ተወስዷል ብለዋል።

የደንብ ማስከበር አባላት የሕዝብን ተጠቃሚነት ባረጋገጠ መልኩ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ባለስልጣኑ ተከታታይ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠቱን ጠቁመዋል።

ደንብ መተላለፍን የሚጸየፍ ኅብረተሰብ ለመፍጠር ባለስልጣኑ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠቱን ጠቁመው፤ ሁሉም አካላት ትብብራቸውን እንዲያጠናክሩ ሻለቃ ዘሪሁን ጥሪ አቅርበዋል።

# ‘ፐብሊክ ዲፕሎማሲ’ በኢትዮጵያ ላይ ሊጣሉ የነበሩ ማዕቀቦች እንዲከሽፉ አድርጓል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በዓለም አቀፍ ደረጃ በተሠራ ጠንካራ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ሥራ በኢትዮጵያ ሊጣሉ የነበሩ ማዕቀቦች መክሸፋቸውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ጉዳዮች ዳይሬክተር ጄኔራል አምባሳደር አብዱ ያሲን አስታወቁ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ጉዳዮች ዳይሬክተር ጄኔራል አምባሳደር አብዱ ያሲን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ስድስት ዓመታት በፐብሊክ ዲፕሎማሲ ብዙ ሥራዎች ተሠርተዋል።

ኢትዮጵያ ባለፉት ሦስት ዓመታት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት 15 ጊዜ አጀንዳ ሆና ቀርባለች ያሉት አምባሳደር አብዱ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ጠንካራ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ሥራ በመሠራቱ በኢትዮጵያ ሊጣሉ የታሰቡ ማዕቀቦች ማክሸፍ ተችሏል ብለዋል።

ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ስለ ኢትዮጵያ እውነቱን እንዲያውቅ የተሰሩ የሕዝብ ለሕዝብ መድረኮች ትልቅ ፋይዳ እንዳላቸው አመልክተዋል።

የፐብሊክ ዲፕሎማሲውን አዎታዊ ተጽዕኖ ለማሳደግ ኢትዮጵያ ከበርካታ የዓለም አቀፍ ከተሞች ጋር የእህትማማች ስምምነት መፈረሟን ገልጸው፤ የተፈረሙ ስምምነቶችም ለሀገራዊ አንድነት፣ ለቀጣናው ትስስርና ለሁለትዮሽ ግንኙነት ማደግ እገዛ እያበረከቱ መሆኑን አስታውቀዋል።


አምባሳደር አብዱ ያሲን

ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ስለ ሀገር ለዓለም ማሳወቅ መሆኑን በመጥቀስ፤ የተጀመሩ የከተማ ማስዋብ ሥራዎች ሲጠናቀቁ ለኢትዮጵያ የገጽታ ግንባታ ትልቅ ሚና ይኖራቸዋል ብለዋል አምባሳደር አብዱ።

የተጀመሩ ከተማን የማስዋብ ሥራዎች ሲጠናቀቁ በርካታ ቱሪስቶችን በመሳብ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የሚያስተላልፉት መልዕክት ትልቅ መሆኑን ጠቁመ፤ ከተማዋን ለማስዋብ የሚሰሩ ሥራዎች ለፐብሊክ ዲፕሎማሲው አጋዥ መሆኑንም ተናግረዋል።

ፐብሊክ ዲፕሎማሲ በአንድ ሀገር ውስጥ የሁሉም ዜጋ ሥራ ነው ያሉት አምባሳደር አብዱ፤ የተለያዩ የማህበረሰብ አባላትና ተወካዮች ሀገራቸውን በሚገባና በሚችሉት ልክ ማስተዋወቅ እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

በትምህርት ዘርፍም ከሌሎች ሀገራት ጋር ጥሩ ትስስር እየተፈጠረ በመሆኑ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ሥራዎች ውጤት እያመጡ ነው። አማርኛ በቻይና ዩኒቨርሲቲ እየተሰጠ ነው። በቀጣይም ሌሎች ቋንቋዎችን እንዲያስተምሩ እየተመካከርን በመሆኑ ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ በትልቁ የማስተዋወቅ አቅም እንደሚፈጥር አስረድተዋል።

ኢትዮጵያም ለጎረቤት ሀገራት በርካታ የትምህርት እድል ሰጥታለች ያሉት አብዱ፤ በያዝነው ዓመት ለጎረቤት ሀገራት ከ850 በላይ የትምህርት እድል መስጠቷን አንስተዋል። ይህም የትምህርት ዕድል ያገኙት የተለያዩ ሀገራት ዜጎች ስለኢትዮጵያ መልካም አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጋል ብለዋል።

በቀጣይ ጠንካራ የሕዝብ ለሕዝብ ትስስር እንዲፈጠር በማድረግ የሁለትዮሽ ግንኙነትን ለማጠናከር በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።


አቶ መስፍን ዳቢ

## 50 በመቶ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

አሁንም የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ አይደሉም።

በአሁኑ ጊዜ የኤሌክትሪክ ተደራሽነትን 50 በመቶ ማድረስ ተችሏል ያሉት አቶ መስፍን፤ ሆኖም 50 በመቶ ኢትዮጵያዊያን እስካሁን የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ አለመሆናቸውን ተናግረዋል።

በየዓመቱ ተጨማሪ ቤተሰቦችን ከዋናው የኤሌክትሪክ መስመር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሲሠራ መቆየቱን ጠቅሰው፤ ባለፉት አምስት ዓመታት ከዓለም ባንክ በተገኘ አንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ብድር ከሁለት ሚሊዮን በላይ አዳዲስ ደንበኞችን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ 50 በመቶ የሚሆኑ ዜጎች አሁንም የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ አለመሆናቸው በተለያዩ ዘርፎች ጉዳት እንደሚያስከትል በመግለጽ፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ቀሪ ዜጎችን የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

በኃይል ዘርፉ ላይ አደረጃጀቱን በመቀየር ከልማታዊ ድርጅቶች ጋር ተግባራዊ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን የገለጹት አቶ መስፍን፤ በተለይም በኃይል ማምረት፣ ማስተላለፍና ማከፋፈል ቀልጣፋ አሠራር በመዘርጋት ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

መርሀ ግብሩን ተግባራዊ ለማድረግ ከዓለም ባንክ 522 ነጥብ 6 ሚሊዮን ዶላር መገኘቱን ጠቅሰው፤ በተለይም የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት የማዘመን፣ ማደስ፣ ተጨማሪ የማከፋፈያ ጣቢያዎችንና ማዕከላትን የመገንባት እንዲሁም ተጨማሪ ደንበኞችን የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በዘርፉ ከዓለም አቀፍ ልማታዊ ድርጅቶች በተጨማሪ የግል አልሚዎችን ተሳታፊ እየተደረገ እንደሚገኝ በመግለጽ፤ ባለፉት አምስት ዓመታት አምስት የሶላር ፕሮጀክቶች፣ ስምንት የዊንግና የሀይድሮ ፕሮጀክቶች ተወስነው ወደ ጨረታ መግባታቸውን አስረድተዋል።

ያልተቆራረጠ የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ለመስጠት በሚደረገው ጥረት በዋናው መስመር ኤሌክትሪክ አቅርቦት እና በሶላር ቴክኖሎጂ በማቅረብ መሠረታዊ የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል ብለዋል።

## ልጓም የሚሻው የጥላቻ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ተጠቃሚዎች ቁጥር ስድስት ነጥብ አራት ሚሊዮን ደርሷል። ከዚህ ውስጥ ደግሞ ፌስ ቡክ 90 ነጥብ ሰባት በመቶ፣ ዩቲዩብ ሁለት ነጥብ ዘጠኝ በመቶ ኤክስ አንድ ነጥብ ስምንት በመቶ ድርሻ አላቸው።

በኢትዮጵያ የቲክቶክና ቴሌግራም ተጠቃሚዎች ቁጥርም እየጨመረ ሲሆን፤ በእነዚሁ የማህበራዊ ሚዲያዎች የሚተላለፉ የጥላቻ ንግግሮችም በዚያው ልክ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፉ መጥተዋል።

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን የመገናኛ ብዙኃን አቅም ግንባታ ዴስክ ኃላፊ ወይዘሮ ኤደን የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃ ስርጭት የሚገኝበትን ሁኔታና ከጊዜ ወደጊዜ የሚያሳየውን ዕድገትና ተጽዕኖ አስመልክቶ እንደሚገልጹት፤ ባለፉት ስድስት ወራት ብቻ በቪዲዮ በቲክቶክ 74 በመቶ፣ በጽሁፍ በኤክስ 66 በመቶ በምስልና በጽሑፍ በመታገዝ በጥምረት በኤክስ ላይ 18 በመቶ የጥላቻ ይዘት ንግሮች ተላልፈዋል። ለእነዚህ የጥላቻ ንግግሮች ደግሞ ግለሰቦች፣ አክቲቪስቶችና የማህበራዊ ሚዲያ ይዘት አመንጪዎች ቀዳሚውን ቦታ ይይዛሉ ብለዋል።

ማንነትን መሠረት ካደረጉ የጥላቻ ይዘቶች ስርጭት አንጻር፤ የፖለቲካ አመለካከቶችን መሰረት በማድረግ በቴሌግራም 64 በመቶ፣ የብሔር ማንነትን መሠረት በማድረግ በፌስ ቡክ 30 በመቶ፣ ጾታዊ ማንነትን መሠረት ያደረጉ በቴክቶክ 20 በመቶ እንዲሁም ሃይማኖትን መሠረት በማድረግ በፌስ ቡክ፣ በኤክስና በዩቲዩብ 15 በመቶ ሆኖ መታየቱን ይናገራሉ። መልዕክቶቹም ሕዝብን፣ ፖለቲከኞችና ባለስልጣናትን እንዲሁም ተጽዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦችን ዒላማ ያደረጉ መሆናቸውን ያነሳሉ።

አንጋፋው የሚዲያ ባለሙያ ጋዜጠኛ ጥበቡ ታደሰ እንደሚሉት፤ የጥላቻ ንግግር አሁን ላይ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል። ችግሩ ከተስተዋለባቸው ሀገራት መካከል ደግሞ ኢትዮጵያ አንዷ ናት።

የጥላቻ ንግግር ከመቀነስ ይልቅ እየጨመረ ነው የሚሉት ጋዜጠኛ ጥበቡ፤ በተለይ በኢትዮጵያ በርካታ ሃይማኖቶች፣ የብሔር ልዩነቶች፣ የፖለቲካ አመላካከቶችና መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ያሉ ልዩነቶችና ምስቅልቅሎች ለጥላቻ ንግግር መስፋፋት ምቹ አጋጣሚ ሳይፈጥሩ እንዳልቀረ ይናገራሉ። ይህ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቶ ከጥላቻ ንግግርነት ይልቅ ወደ ጥላቻ ድርጊት እየተቀየረ ነው ይላሉ።

ዲጂታል ሚዲያው ለሁሉም ሰው ዕድል መስጠቱና አጠቃቀም ላይ ያለው የእውቀት ክፍተት፣ የሚደረገው ቁጥጥርና ክትትል ደካማ መሆኑ ችግሩን እንዳባባሰውም ይገልጻሉ። የሰዎችን ሰብዓዊ መብት፣ ክብርና ማንነትን በሚንቅ መንገድ ከንግግር ባለፈ በድርጊት የተገለጹት ጉዳዮችን እንደማሳያ አንስተዋል።

የጥላቻ ንግግር ሥርጭት ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚያሳድር የሚገልጹት ወይዘሮ ኤደን፤ ለጥቃት ማነሳሳት፣ የሕዝብን አብሮነት መሸርሸር፣ ለአመጽ የማነሳሳትና የግለሰብን ሰብዕና መጉዳትና ማጉደፍ ላይ ጉልህ ቦታ እንደሚይዙ ይጠቁማሉ።

እንደ ወይዘሮ ኤደን ማብራሪያ፤ አክቲቪስቶችና ግለሰቦች የጥላቻ ንግግር ዋነኛ ምንጮች ሆነው የታዩ ሲሆን፤ በእነዚህ አካላት የሚንጸባረቁ የጥላቻ ንግግሮች ሕዝብን ከሕዝብ፣ ሕዝብን ከመንግሥት፣ መንግሥትን ከሀገር፣ ሕዝብን ከሀገር የሚለያዩና የሚነጣጥሉ እሳቤዎችን የሚያንጸባርቁ ናቸው።

ወይዘሮ ኤደን በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶችን መነሻ አድርገው እንደሚገልጹት፤ የጥላቻ ንግግር ስጋት ከፍተኛና አስጊ ደረጃ ላይ ደርሷል።

እነዚህ በስፋት እየተዛመቱ የሚገኙት የጥላቻ ንግግሮች ዓላማቸው ለአመጽና ለጥቃት ማነሳሳት እንደሆነ የሚገልጹት ወይዘሮ ኤደን፤ በሕዝቦች መካከልም ተቃርኖ እንዲፈጠር በማድረግ አብሮነት ላይ አስጊ ሁኔታን ይፈጥራሉ ብለዋል።

ጋዜጠኛ ጥበቡ እንደሚሉት፤ ማህበራዊ ሚዲያ ገበያ ነው። ይህንን ገበያ አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት ብዙ ተከታይ እንዲኖር ይፈለጋል። በዚህም የሰዎችን ትኩረት ለመሳብ ሰላማዊ ከሆኑ ነገሮችና ሀገርን ወደፊት ከሚያሻግሩ ሃሳቦች ይልቅ የሰዎችን ስሜት የሚኮረኩሩና አንዱ በአንዱ ላይ እንዲነሳሳ የሚያደርጉ ጉዳዮች ይለጠፋሉ። ይህ የበለጠ ተከታይ ያመጣል በሚል ጊዜያዊ ትርፍን ብቻ ከማሰብ የሚመጣ ነው።

አስተማሪ የሆኑ ርምጃዎች ላይ ክፍተቶች መኖራቸውን የሚገልጹት ጋዜጠኛ ጥበቡ፤ ከተቋማትም አልፎ ድርጊቱን በሚፈጽሙ ግለሰቦችም ጭምር ጠንካራ ርምጃዎች እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

አንዳንድ ጉዳዮች በግልጽ የወንጀልነት ባህሪ ያላቸው በመሆናቸው ጥብቅ የሆነ የመደበኛ ሕግ ተጠያቂነት ሊኖር እንደሚገባም ያነሳሉ።

የጥላቻ ንግግሩ መንጸባረቁ ብቻ ሳይሆን ይህንን የሚያዩ የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች የሚሰጡት ግብረ መልስም እንዲሁ ጉዳዩን ሊያባብሰው እንደሚችልም ነው የገለጹት።

ወይዘሮ ኤደን “ከንግግር ወደ ድርጊት እየተለውጠ ነው” የሚለውን የጋዜጠኛ ጥበቡን ሃሳብ ይደግፋሉ። የጥላቻ ንግግር በአጠቃላይ ኅብረተሰቡ መካከል ወደ መከፋፈል እያመራ ያለ መሆኑን እንደማሳያ ያነሳሉ። ሁኔታው ከባለፈው ዓመት ጋር ተነጻጽሮ ሲታይ መረጃዎቹ ከስድብ ወደ ስብዕና መጉዳት፤ ከፍረጃ ወደ አግላይ ጥቅል ፍረጃ፤ ከማስፈራሪያ ወደ ስጋትነት፤ ከጭካኔ አገላለጽ ወደ ጥቃት ማነሳሳትና የግድያ ጥሪ ከፍ ብለው ታይተዋል ሲሉም ያብራራሉ። ይህም ከማስጠንቀቂያ በዘለለ አጣዳፊ መፍትሔ እንደሚያሻው የሚያሳይ ነው ብለዋል።

በሌላ በኩል የማህበራዊ ሚዲያ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በመረጃ ስርጭት አጠቃቀም መመሪያና ደንባቸው መሠረት የሚከለከሉ ነገሮችን ቢደነግጉም በሚገባ ተፈጻሚ እያደረጉ አለመሆኑን ጠቅሰዋል።

የጥላቻ ንግግር እያስከተለ ያለው አደጋ ሰፊና ውስብስብ እየሆነ ከመምጣቱ አንጻር የሚመለከታቸው አካላት የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲወጡ ወይዘሮ ኤደን ያስገነዝባሉ።

እንደ ጋዜጠኛ ጥበቡ ማብራሪያ፤ የጥላቻ ንግግር ስርጭትን መግራት ካልተቻለ፤ እንደ ሀገር አለመረጋጋት በዚህ ውስጥ ደግሞ የበርካታ ሰዎች ህይወት እንዲጠፋ፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የትራንስፖርት አገልግሎቶች እንዳይሚሉ እና ዜጎች ተንቀሳቅሰው እንዳይሠሩ የማድረግ ውጤት ይኖራቸዋልም ነው ያሉት።

## «ኮሚሽኑ ወደኋላ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ምክክሮችን ለማካሄድ ምቹ በሆኑ አካባቢዎች ምክክሩን መጀመር ያስፈልጋልም ብለዋል።

የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ኮሚሽኑ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ አብሮ ለመሥራት ጥረቶችን ሲያደርግ መቆየቱንም ገልጸዋል።

ሀገራዊ ምክክርን በተመለከተ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ ተሞክሮዎችን የተሳኩ፣ ያልተሳኩ እና ከዚህም አልፈው ችግር የፈጠሩትን የሚያሳይ የዳሰሳ ጥናት ማካሄዱን ያነሱት ዳይሬክተሩ፤ ጥናቱ በኢንስቲትዩቱ ተመራማሪዎች አማካኝነት ለኮሚሽኑ እንዲቀርብ መደረጉንም አስታውሰዋል።

ተመራማሪዎቹ ምክክሩ በምን መልኩ ቢካሄድ አላማውን ማሳካት ይችላል በሚለውም ላይ የዳሰሳ ጥናቱን መነሻ ያደረገ አካሄድን የማመላከት ፍላጎት ነበራቸው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ኮሚሽኑን ብዙ ወደኋላ የሚጎትቱት ጉዳዮች በመኖራቸው በሚፈለገው ፍጥነት ልክ ለመሄድ እንዳልተሳካለት ነው የተረዳነው ብለዋል።

በጥናቱ በኢትዮጵያ ውስጥ አነጋጋሪ የሆኑ ጉዳዮች በመለየት ሀገራዊ መግባባትን ለመፍጠር የሚመረጡ ጉዳዮችን ምን ድረስ ወደኋላ ተጉዘን ነው መመልከት ያለብን የሚለውም ለኮሚሽኑ በቀረበው ጽሑፍ ላይ መመላከቱንም አስታውቀዋል።

ምክክሩ ሁሉንም የኢትዮጵያ ክፍል መሸፈን አለበት ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ይህ ምን ያህል ጊዜ ሊወስድ እንደሚችል መገመት አስቸጋሪ ነው የሚል አስተያየት ሰጥተዋል።

አያይዘውም፣ ምክክሩ በዚህን ያህል ጊዜ ያልቃል የሚል እቅድ የሚቀመጥለት አይደለም ብለዋል።

ኮሚሽኑ ምክክሩን መጀመሩ ላይ ትኩረት መስጠት እንዳለበትም ነው ዳይሬክተሩ የመከሩት።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሀገር ውስጥ የማምረቻ መሣሪያዎችንና ኢንዱስትሪዎችን የማስተሳሰሩ ጥረት ሲጠናከር ይገባል!

በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ የገቢ ምርቶችን ከመተካት እንዲሁም የወጪ ምርቶችን ለማምረት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ወሳኝ ሚና ከሚጫወቱት መካከል የማምረቻ መሣሪያዎች ወይም ማሽኖች ይጠቀሳሉ። ይህን በሚገባ የተረዳው መንግሥት ዘርፉ እነዚህን ማሽኖች በማሽነሪ ሊዝ አማካይነት እንዲያገኝ ለማድረግ በርካታ ተግባሮችን አከናውኗል።

የአምራቾቹን የማምረቻ መሣሪያዎች ፍላጎት ታሳቢ ባደረገ መልኩ በሀገር ውስጥ የሚመረቱ እንዲሁም ከውጭ የሚገቡ ማሽነሪዎችን ለማቅረብ እየተሠራ ሲሆን፣ በተለይ የማምረቻ መሣሪያዎቹን በሀገር ውስጥ አምርቶ ለአምራቹ ማቅረብ መቻል ፋይዳው ብዙ እንደመሆኑ በዚህ ላይ በትኩረት እየተሠራ ነው።

የማሽነሪ አምራቾችን ለማገዝ የሚያስችል ሀገራዊ አቅም መፍጠርን ያለመ መድረክ በቅርቡ በተካሄደበት ወቅት እንደተጠቆመው፤ የገቢ ምርትን ለመተካት በሚከናወን ሥራ 30 በመቶ የነበረውን የገበያ ድርሻ ወደ 60 በመቶ ለማሳደግ ታቅዶ እየተሠራ ይገኛል። የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ በአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት /ጂዲፒ/ ያለውን ድርሻ አሁን ካለበት ሰባት በመቶ ወደ 17 በመቶ ለማሳደግም ታቅዷል።

የማምረቻ ማሽኖችን በሀገር ውስጥ እያመረቱ ለአምራቾች ማቅረብና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንደሚያስፈልግ በመንግሥት በኩል ታምኖበትም እየተሠራ ነው። መንግሥት የዘርፉን እቅዶች ለማሳካት ባለው ቁርጠኝነት ባለፉት አምስት ዓመታት ብቻ ከ32 ሺ በላይ ማሽነሪዎች ለአምራች ኢንተርፕራይዞች በሊዝ ፋይናንስ እንዲተላለፉ አድርጓል።

ይህን ሁሉ ተከትሎም እንደ ሀገር ማሽን የማምረት አቅም እያደገና ከሀገሪቱ አልፎም እንዳንድ ምርቶችን ለውጭ ገበያ መላክ መጀመሩንም የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መረጃ ያመለክታል። እውን እዚህ ሀገር ውስጥ የተመረቱ ናቸው ወይ የሚያሰኙ ማሽነሪዎች በሀገር ውስጥ እየተመረቱ መሆናቸውም ታውቋል። ገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች መተካት የሚያስችል አቅም መኖሩን ያመላካቱ ለውጦች እንዳሉም አስታውቋል።

ይሁንና የሀገር ውስጥ የማምረቻ ማሽኖችን ከመጠቀም አኳያ ግን ሰፊ ክፍተት ታይቷል። ለአምራቾች በማሽነሪ ሊዝ ከተላለፉት 32 ሺ የማምረቻ ማሽኖች ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው በሀገር ውስጥ የተመረቱት። የሚገርመው ደግሞ በሀገር ውስጥ ማሽኖችን የማምረት አቅሙ በጥሩ ደረጃ ላይ ባለበት ሁኔታ ነው ይሄ እየሆነ ያለው።

ገቢ ምርትን በሀገር ውስጥ ለመተካት በትኩረት እየተሠራ ነው በሚባልበት ሁኔታ የሀገር ውስጥ የማምረቻ ማሽኖች ለአምራቾች ከማቅረብ ይልቅ ከውጭ የመጡት እንዲቀርቡ እየተደረገ ነው፤ ከፍተቱ ደግሞ እጅግ ሰፊ ነው። በሀገሬ ምርት እኮራለሁ በሚባልበት ሁኔታ ከውጭ ለሚመጡ ምርቶች ቅድሚያ መስጠት ሀገርን በተለያዩ መልኩ በእጅጉ ይጎዳል፤ በሌላ የውጭ ምንዛሬ ከውጭ የማምረቻ መሣሪያ ማስመጣት ለሌላ የተሻለ ልማት ሊውል የሚችል ሀብት ያባክናል።

ሥራ አጥነት በተንሰራፋበት እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ የሚጠይቁ በርካታ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ሸቀጦችና አገልግሎቶች ባሉበት እንደ ኢትዮጵያ ባለ ሀገር ሁሉንም የማምረቻ ማሽን ከውጭ ማስገባት አይቻልም። እንኳንስ የማምረቻ ማሽኖችን የማምረት በቂ አቅም እያለ አቅሙን ፈጥሮ ማሽኖችን ማምረት የግድ ነው።

የማምረት አቅም መኖሩ ታይቷል። ይህ በሆነበት ሁኔታ ከውጭ የሚመጡ ማሽኖችን መጠበቅ እንዲሁም ለውጭ ማሽኖች ግዥ ትኩረት መስጠት የሀገሪቱን የዘርፉን እቅድም ሆነ ራእይ ለማሳካት በሚደረገው ጥረት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳርፋል።

በሀገር ውስጥ የማምረቻ ማሽኖች የማምረት አቅም ስለመኖሩ በመንግሥት በኩል ተለይቷል። መሠረታዊው ችግር ያለው በማሽነሪ አምራች ኢንዱስትሪዎችና በሊዝ ፋይናንስ ተቋማትና ማሽን ፈላጊ ኢንዱስትሪዎች መካከል ያለው ሰፊ የመረጃና ተቀናጅቶ የመሥራት ክፍተት መሆኑም እንዲሁ ታውቋል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዞች ልማት በቅርቡ ያካሄዱት መድረክ ዋና ዓላማም በእነዚህ ተቋማት መካከል ትስስር መፍጠርና ክፍተቱን መሙላት ነው። ይህ አይነቱ መድረክ ለገቢ ምርቶች መተካቱም ሆነ ለአጠቃላይ ለአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ውጤታማነት ወሳኝ እንደመሆኑ ሊበረታታ የሚገባውና በቀጣይም በስፋት ሊሠራበት የሚገባ ነው።

ይህን ማድረግ ማሽነሪዎችን በሀገር ውስጥ የማምረት አቅም ይበልጥ እንዲጎለብት፣ ኢንዱስትሪዎችም ለሀገር ውስጥ ምርት ትኩረት እንዲሰጡ ያስችላል። የኢንዱስትሪዎቹ የማምረት አቅሙ ሊጨምር የሚችለው ገበያ ሲኖር እንደመሆኑ ምርቶቹን ለፈላጊዎች ለማድረስ የተያዘው ርብርብ ተጠናክሮ መቀጠል ይገባዋል።

ማሽነሪ አምራቾች፣ ማሽነሪ አቅራቢዎች እንዲሁም ገዥ አካላትን ማስተሳሰር የሚያስችሉ መድረኮችን መፍጠር አንድ ነገር ሆኖ፣ እነዚህ አካላት ምን ያህል ተሳስረው እየሠሩ ነው፤ ትስስራቸው ምን ለውጥ አምጥቷል፤ ምንስ ተግዳሮት ገጥሟቸዋል፣ ተግዳሮቶቹስ እንዴት ይፈታሉ የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት ለትስስሩ መጠናከርና ውጤታማነት ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ጭምር በትኩረት መስራት ያስፈልጋል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ:- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ጊዜ ያለፈበት የነጻ አውጪ ድራማ በመሥራት ማትረፍ አይቻልም !

በእምነት

ጦርነት ከግጭት የፖለቲካ ትርፍ ለማጋበስ ለሚሞክሩ ለግጭት ነጋዴዎች አዋጭ፤ አትራፊ ሥራ ነው። ስውር የፖለቲካ አጀንዳ ላላቸው ኃይሎች እንደ መልካም አጋጣሚ ተደርጎ የሚወሰድ ነው። ለጽንፈኞች እና ለፀረ ሕዝብ ኃይሎች ደግሞ የድግስ ያህል የሚቆጠር ነው።

ለአንድ ሀገር እና ሕዝብ ግን የዕልቂትና መከራ ምንጭ ነው። እጅግ አስከፊ የሰው ሕይወት የሚበላ፤ የሀገር እና የሕዝብ ሀብት የሚያወድም ፤ ሀገር ካለችበት ከፍታ አውርዶ ዓመታትን የኋሊት የሚመልስ አውዳሚ ክስተት ነው።

እኛ ኢትዮጵውያን እንደ ሀገር በብዙ ጦርነቶች ውስጥ አልፈን ፤ እጅግ ብዙ ዋጋ እየከፈልን ዛሬ ላይ የደረስን ሕዝቦች ነን። በነጻ አውጪ ስም እራሳቸውን የሚሰይሙ “ፖለቲከኞቻችን” ልዩነቶቻቸውን በንግግር ከመፍታት ይልቅ በጠመንጃ ለመፍታት የሚተጉ ናቸው። ይህ ሁኔታ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ዛሬም የተጣበቀን የፖለቲካ ታሪካችን መጥፎ ገጽታ ነው።

በቀደመው ጊዜ በዓለም አደባባዮች ገነን የወጣንባቸውን የአክሱም እና የዛጉዌ ሥልጣኔን ያዳከመውና ያጠፋው ጦርነት ነው፤ በእነዚህ ጊዜያት የነበሩ ሥልጣኔዎች በጦርነት እንዳልነበር ባይሆኑ ዛሬ የት ልንደርስ እንደምንችልም መገመቱ ለማንም ቀላል ነው። ይህም ሆኖ ግን ዛሬም ከትናንት ስህተታችን የማንማር፤ ለእያንዳንዱ ችግራችን ጦርነትን መፍትሔ አድርገን የምንወስድ ሕዝቦች ነን።

በ21ኛው ክፍለ ዘመን ችግሮቻችን በሠለጠነ መንገድ በንግግር እና በውይይት ከመፍታት ይልቅ ጠበንጃ /ሃይልን/ እንደአማራጭ እየወሰድን ነው። ዛሬም ከትናንት ውድቀታችንና ስህተታችን አልተማርንም። እንደ ሀገር የሥልጣኔ ቁንጮ የነበርን ሕዝቦች በግጭትና ጦርነት ዳፋ ወደታች ወርደን የዓለም መሳቂያና መሳለቂያ ሆነናል። ዛሬም ከድህነት ለመውጣት ለምናደርገው ጥረት ግጭትና ጦርነት ሳንካ እየሆነበት ነው።

መቼ ይሆን ከዚህ አዙሪት የምንወጣው? መቼ ይሆን ከነጻ አውጪነት አባዜ ተላቀን በነጻ ምርጫችን የምንኖረው? መቼ ይሆን ‹‹የማን ቤት ጠፍቶ የማን ሊበጅ፣ የአውሬ መፈንጫ ይሆናል እንጂ” ከሚለው የጦርነት ሸለላ ቀረርቷችን የምንወጣው ?፤ ሁላችንም እንደሀገር ተያይዘን እናልቃለን እንጂ ማንም አይተርፍም ከሚል ከዚህ አይነት ከንቱ ውዳሴ የምንገላገለው ?።

ሀገር የማናት ? የማን ቤት ጠፍቶ የማን ሊበጅ፤ እያልን የምንዘባበተውስ ማን ላይ ነው? ሀገርን አውድሞ፤ ሕዝብን አጥፍቶ የት ላይ ሊኖር? እንደዚህ አይነቶቹ የሚገራቸው ያጡ የጥፋት ሸለላና ቀረርቶዎቻችን መቋጫ ሊበጅላቸው ይገባል።

“

**ነጻ አውጪ ነን የሚሉ ኃይሎች መጀመሪያ ከራሳቸው ደካማ አስተሳሰብ ነጻ ሊወጡ ይገባል**

ጦርነት ትውልድ ያጠፋል። በጦርነት ምክንያት ሀገራቸውን ሠርተው መለወጥ የሚችሉ ወጣቶች የጦርነት ማገዶ ይሆናሉ። ለዚህ ሶሪያን፣ ኢራቅን፣ ወዘተ እንደ ማሳያ ማንሳት አያስፈልገንም ፤ ለዚህ የሚሆን የራሳችን በቂ የጦርነት ታሪክ አለን።

በቅርብ ዓመታት እንኳን ችግራችንን በንግግር መፍታት አቅቶን ባነሳነው ጠመንጃ የስንቱ ወጣት ሕይወት እንደ ቅጠል ረግፏል? ስንቷ እናት አድጎ ይጦረኛል፤ ራሱን ችሎ ይረዳኛል የምትለውን ልጇን ለጠመንጃ አረር ገብራ ብቻዋን ቁጭ ብላ በር በሩን ታያለች።

የሚያሳዝነው ከዚህ ስህተታችን ዛሬም አልተማርንም፤ ዛሬም ትርጉም አልባ ለሆኑ ጥያቄዎች በጠመንጃ ምላሽ ለማፈላለግ የሚባዝኑ፤ ባሩድ እያሸተቱ የሚያቅራሩ ፤ የጦርነት ፊሽካ ለመንፋትም እራሳቸውን የሚያዘጋጁም ጥቂት አይደሉም። በዚህም ሀገር እና ሕዝብን ብዙ ዋጋ እያስከፈሉ ነው።

እኛ ኢትዮጵውያን እንደ ሀገር ብዙ ሺ ዓመታትን አብረን የኖርን ነን ፤ ክፉ ደጉንም አብሮ አልፈናል፤ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ግለሰቦች እና ቡድኖች በፈጠሩት ግራ መጋባት ፤ በጥቂቶች የፉከራ እና ቀረርቶ ፖለቲካ የቱንም ያህል ያልተገባ ዋጋ ለመክፈል ብንገደድም ዛሬ አብረን ነን።

አሳዛኙ እውነታ እንደ ሀገር ወደ ጦርነት የምንገባባቸው ምክንያቶች አብዛኞቹ ተመሳሳይ ናቸው። የጦርነቶቻችን ምክንያቶች ከራስ ወዳድነትና ስግብግብነት ተጀምረው በዚያው የሚቋጩ ናቸው። እኔ ያልመራሁት፤ እኔ ያላዘዝኩበት ሀገር እና ሕዝብ መኖር የለበትም ከሚል እሳቤ የመነጩ ናቸው።

እንደ ሀገር እንለማለን፤ እንበለጽጋለን ከማለት ይልቅ አብረን እንለቅ የሚል የአስተሳሰብ መዛነፍ የተጠናወታቸው ናቸው። ይህ በአብዛኛው በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ሲመላለሱ የቆዩ አካላት የሚጋሩት፤ ዛሬም ነፍጥ አንስተው በየጫካው መሽገው የሚገኙ ቡድኖች የሚያራምዱት ነው።

እነዚህ ቡድኖች ቢመከሩ የማይሰሙ፤ ቢገሰጹ የማይገባቸው ልበ ደንዳኖች ናቸው። የሕዝብና ሀገር ጥቅም የሚባል ጉዳይ የማይገባቸው፤ ሀገርን ጥለው ብሄርና ኃይማኖትን አንጠልጥለው የራሳቸውን ጥቅም ሰርክ የሚያሳድዱ ናቸው። ነጻ አውጣኝ የሚል ሕዝብ ሳይኖር ነጻ አወጣሃለሁ ብለው እራሳቸውን የሚሾሙ፤ እታገልለታለሁ ብለው የተነሱትን ሕዝብ ሳይቀር የሚገድሉና ክብሩን የሚያዋርዱ ናቸው።

አስተሳሰባቸው ከፊውዳል ዘመን ያልተሻገረ፤ በአሸናፊነትና በተሸናፊነት ስሌት ውስጥ የሚዳክር፤ በጋራ ማሸነፍ የሚባለውን ዘመናዊ አስተሳሰብ የማያውቅ ፤ “እኔ የምኖረው እገሌ ሲጠፋ ነው” የሚል ቢሂል የተጫናቸው፤ ለዘመኑ አስተሳሰብ ባዕድ የሆኑ ናቸው።

እነዚህ የጦርነት ነጋዴዎች አደብ ማስገዛት የዚህ ትውልድ ሃላፊነት እንደሚሆን ይሰማኛል። ዘመኑ የሥልጣኔ፣ የእውቀት እና የፈጠራ ከመሆኑ አኳያ ሕዝባችን እነዚህን ከዘመኑ ጋር ተጣልተው ሀገር እና ሕዝብን ያልተገባ ዋጋ ከሚያስከፍሉ ግለሰቦች እና ቡድኖች አንቅሮ ሊተፋቸው ይገባል። ዛሬም በነጻ አውጪ ስም እንዲያሰቃዩት እና እንዲገድሉት ፤ ተስፋውን እንዲነጥቁት ሊፈቅድላቸው አይገባም።

በሕዝብ ስም መነገድና የብሄር ካባ ደርቦ ማታለል ዘመኑ ያለፈበት ፋሽን ነው። ዛሬ ሕዝብ ከሁሉም በላይ አዋቂ ነው። የሚጎዳውንና የሚጠቅመውን ያውቃል። ከዚህ ይልቅ ነጻ አውጪ ነን የሚሉ ኃይሎች መጀመርያ ከራሳቸው ደካማ አስተሳሰብ ነጻ ሊወጡ ይገባል። እራሱ ነጻ ያልወጣ ማንንም ነጻ ሊያወጣ አይችም።

በየጫካቸው ተሰግስገው ለሕዝብ ነጻነት እንታገላለን የሚሉ ኃይሎች መጀመርያ በነጻ አእምሮ ሀገር እና ሕዝብን ማስቀደም ይጠበቅባቸዋል። ኢትዮጵያ ከብሄር፤ ከሃይማኖት እና ከግል አስተሳሰብ በላይ መሆኗን ሊረዱ ይገባል።

ዓለም ሠልጥኖ በቴክኖሎጂ በሚራቀቅበት በ21ኛው ክፍለ ዘመን ዓለም ከመቶ ዓመት በፊት አስተናግዳ ባሰናበተችው የነጻ አውጪ፤ ድራማ የተዋጣለት ተዋንያን መሆን አይቻልም። ዛሬ ማንም ከማንም ነጻ አይወጣም። ዛሬ ሁሉም ነጻ መውጣት የሚፈልገው ከድህነትና ከኋላ ቀርነት ነው። ከቻላችሁ ተባብረን ከድህነት ነጻ እንውጣ፤ ካልሆነም ተወት አድርጉን። አበቃሁ!

# ነፃ ሃሳብ

# ብሪክስ፤ የአባላቱ አሁናዊ ይዞታና ተስፋቸው

ገርማ መንግሥቴ

በዓለማችን በርካታ አህጉርና ዓለም አቀፍ ተቋማት አሉ። የተወሰኑት ታሪካዊ ሲሆኑ አብዛኞቹ የዘመናዊው ዓለም አስተሳሰብና አኗኗር ውጤቶች ናቸው። ከእነዚህ ዘመናዊ አስተሳሰብ፣ ርእዮትና አዝማሚያው ፀንሶ ከወለዳቸው ተቋማት መካከልም በእአአ 2009 በአራት ሀገራት (ብራዚል፣ ሩሲያ፣ ሕንድ እና ቻይና) በጋራ ስምምነት "ብሪክ"፤ በ2010 ደግሞ ደቡብ አፍሪካን በመጨመሩ ምክንያት "S"ን ጨምሮ ብሪክስ (BRICS) በሚል የተመሠረተው ("ብሶት የወለደው") ድርጅት አንዱ ነው።

ኢትዮጵያም ጥቅሞቿን ሊያስጠብቁ ከሚችሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር መሥራቷን እንደምትቀጥልና ብሪክስን ለመቀላቀል በይፋ ጥያቄ ማቅረቧን አሳውቃ ነበር። ባሳለፍነው የጥምረቱ 15ኛ ጉባዔ በደቡብ አፍሪካዋ የንግድ መዲና ጆሃንስበርግ ሲካሄድ የኢትዮጵያ ጥያቄ ምላሽ ማግኘቱም አይዘነጋም፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ ሌሎች ሀገራትም (ግብፅ፣ ኢራን እና የተባበሩት አረብ ኤምሬትስና ሳውዲ አረቢያ) ተመሳሳይ ጥያቄን በማቅረባቸው ምክንያት ብሪክስን ቢቀላቀሉ ከዓላማና ተልእኮው ጋር አብረው ይሄዳሉ ተብለው በብሪክስ አመራር የታመነባቸው ሀገራት ጥያቄያቸው ተቀባይነት አግኝቶ ሙሉ የብሪክስ አባል ሆነዋል። በቅርቡም ከ40 በላይ ሀገራት ጥምረቱን ለመቀላቀል ይፋዊ ጥያቄ ማቅረባቸው ታውቋል፡፡

የሰሜን አሜሪካ እና የምዕራብ አውሮፓ የበለጸጉ ሀገራትን ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ኃይል ለመቋቋም እና ለመገዳደር በዓለም ላይ በጣም ወሳኝ የሚባሉ፤ በመልማት ላይ ያሉ ሀገራትን አንድ ላይ ለማሰባሰብ በማለም፣ በሀገራት ፈቃደኝነት የተመሠረተውና ጠቅላይ መምሪያውን ሻንጋይ (ቻይና) ያደረገው ብሪክስ፣ (በአይነቱ Intergovernmental organization ነው)፡ ፡ ያደረገው ተቋም ለመመሥረቱ ዐቢይ ምክንያቶች ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሲሆኑ፤ ቀዳሚ ዓላማውም በአባል ሀገራት፤ በሂደትም በየትም ቦታ ኢንቨስትመንትን በማካሄድ የኢኮኖሚ አቅምን መገንባት፤ እንደ ጦር መሣሪያ እያገለገለ ካለው የዩኤስ ዶላር መገላገል ነው።

የአሜሪካ ቅጥ ያጣ የበላይነት የወለደው ነው የሚሉ ሃይላት እንዳሉ ሆነው፤ እንደ አይኤምኤፍ እና ዓለም ባንክ ያሉ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማትን አሠራር የማሻሻያ መንገዶችን በአማራጭነት ለመፈለግ፤ እንዲሁም ለታዳጊ ሀገራት ምጣኔ ሀብት ድምጽ እና ውክልና ለመፍጠር ታስቦ የተቋቋመ መሆኑ የሚነገርለት ብሪክስ፣ ለዚሁ ዓላማ ይመስላል በ2014 (እአአ) በማደግ ላይ ባሉ የብሪክስ ሀገራት ውስጥ ለመሠረተ ልማት እና ለዘላቂ ልማት ፕሮጀክቶች ሀብት የማሰባሰብ ዓላማ ያለውን 'ኒው ዴቨሎፕመንት ባንክ' (ኤንዲቢ) በ250 ቢሊዮን ዶላር አቋቁሟል። የባንኩ ትኩረት በኃይል፣ በትራንስፖርት መሠረተ ልማት፣ በውሃ አቅርቦትና እና ንጽህና አጠባበቅ፣ ዲጂታል መሠረተ ልማት፣ የአካባቢ ጥበቃ እና ማኅበራዊ መሠረተ ልማት ላይ ይሆን ዘንድ ስምምነት ላይ ተደርሷል።

ባንኩ በአሁኑ ሰአት በአባል ሀአገራቱ ውስጥ ያለውን ከፍተኛ የመሠረተ ልማት የገንዘብ አቅርቦት ክፍተት ለመፍታት በመሥራት ላይ ሲሆን፣ እስከ 2016 ብቻ ባለው ጊዜም 1 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር ማበደር ከመቻሉም በላይ፤ እስከ 2017 (እአአ) ድረስ በአጠቃላይ በ11 ግዙፍ ፕሮጀክቶች ላይ መዋዕለ ነዋይ አፍስሷል።

በጎልድማን ሳክስ የምጣኔ ሀብት ባለሙያ፣ ብሪታኒያዊው ጂም ኦ'ኔል ሃሳብ አመነጪነት የተፀነሰው፤ ስያሜውንም በ21ኛው ክፍለ-ዘመን ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት የሚያስመዘግቡ ሀገራት መሆናቸውን ከወዲሁ በማመን "ብሪክስ" ሲል የሰየመው ድርጅት ባቋቋመው ባንክ (NDB) ለአባል ሀገራት መሠረተ-ልማት ፕሮጀክቶች ገንዘብ ማበደር ላይ አጥብቆ የሚሠራ እንደ መሆኑ መጠን፤ "ኢትዮጵያ ብሪክስን መቀላቀሏ ብራዚል፣ ሩሲያ፣ ሕንድ፣ ቻይና እና ደቡብ አፍሪካ ያቋቋሙት ባንክ "አዲስ የብድር ምንጭ" ሊሆናት" እንደሚችል ይታመናል፡፡

ዋና መሥሪያ ቤቱ በምሥራቅ ሻንጋይ የሚገኘውና የቀድሞዋ የብራዚል ፕሬዚደንት የሚመሩት ይህ ባንክ ከላይ የጠቀስናቸው ሀገራት "እነሆ" ባሉት 50 ቢሊዮን ዶላር መነሻ ካፒታል እነዓለም ባንክን ለመገዳደር የተቋቋመ መሆኑ የሚነገርለት ሲሆን፤ በባንኩ ዓላማና ተልእኮ የአባል ሀገራቱ ልብ ከወዲሁ በተስፋ እንዲሞላ እያደረገ እንደሚገኝ በተከታታይ እየወጡ ያሉ የመገናኛ ብዙኃን ዘገባዎች፤ የብሪክስ መግለጫዎች ያስረዳሉ።

እንደሚታወቀው፣ ቡድን 20 (ጂ20) በ1999 (እአአ) በበለፀጉ እና በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ስብስብ ተቋቁሟል። ዓላማውም በዓለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት ነው። ብሪክስም ይህንን ዓላማ ለማክሸፍ የተቋቋመ ድርጅት ነው የሚሉ ብዙዎች ናቸው። ይህ የዚህ ጽሑፍ ጉዳይ ባለመሆኑ ልናልፈው እንችላለን።

በ2023ቱ የቡድኑ ስብሰባ ላይ ባይነገርም፤ በብራዚል እና በሩሲያ ያሉ ታዋቂ ፖለቲከኞች የዶላርን የበላይነት ለመቀነስ የብሪክስ ገንዘብ እንዲጀመር ሃሳብ አቅርበዋል። "ይቻላቸዋልን?" የሚለው ያነጋገረ ቢሆንም፤ ፕሮፌሰር ካርሞዲ እና ሌሎች "የብሪክስ ሀገራት ኢኮኖሚ በጣም የተለያየ ስለሆነ የጋራ መገበያያ ገንዘብ መፍጠር ተግባራዊ ሊሆን አይችልም" የሚል አስተያየትን እየሰነዘሩ ነው። "ለዓለም አቀፍ ንግድ ክፍያዎች የሚውል አዲስ ምንዛሪ ለመፍጠር ወይም ለዓለም አቀፍ ንግድ የሚውል ክሪፕቶከረንሲ መፍጠር ላይ እያሰቡበት ብቻ ሳይሆን ወደ ማጠናቀቁ መድረሳቸውን የሚናገሩ ደግሞ በሌላው ወገን ይሰማሉ። እንደውም፣ እንደ አንዳንድ ውስጥ አዋቂዎች ከሆነ ጉዳዩ አልቋል፤ ተጠናቅቋል።

በአሁኑ የብሪክስ መሪ፣ በፑቲን አማካኝነት እንደ ተገለፀው፣ ዋነኛ ከሚባሉት የዓለማችን የሀገራት ስብስብ መካከል አንዷ የሆነችው፣ የብሪክስ መሥራችና አባሏ ሩሲያ ፍላጎት በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሥርዓት ውስጥ የብሪክስን ሚና ማሳደግ፤ በባንኮች መካከል ትብብርን ማዳበር እና የብሪክስን የገንዘብ አጠቃቀም ማስፋፋት፤ እንዲሁም፣ የግብር እና የጉምሩክ ትብብርን ማበረታት ነው። ይህ ሰፋ ተደርጎ ሲተነተን ምን ማለት እንደ ሆነ ለአንባቢያን እንተወውና ወደ ሌላኛው ነጥብ እናዝግም።

መሥራች ሀገራቱ የመሠረቱትና አሁን ተጨማሪ አራት ሀገራት የተቀላቀሉት ይህ ስብስብ (ብሪክስ) በዓለም አቀፉ ፖለቲካ እና ምጣኔ ሀብት ላይ የበለጠ ተጽኖ እንደሚፈጥር ከወዲሁ የብዙዎች ፍራት፣ ስጋት እና ተስፋ እየሆነ መጥቷል። በተለይ ዶላርን ከግብይት ውጪ ለማድረግ (De-dollarization ይሉታል) De-dollarization Strategyን በመጠቀም ጥርሱን ነክሶ ያለ እረፍት እንደሚሠራም እንደዛው።

ሰሞኑን አይኤምኤፍ በ2024 3 ነጥብ 2 በመቶ በማደግ የዓለምን ኢኮኖሚ ትመራለች በማለት የተነበየላት ሀገር መሪው ፑቲን ገና በ2022 የብሪክስ አባል ሀገራት ጉባዔ በበይነ መረብ ሲካሄድ ባስተላለፉት መልዕክት፥ "የመካከለኛው ምስራቅ ቀውስ የከሸፈ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ማሳያ ነው፤ ለጋዛ ጦርነት ፖለቲካዊ መፍትሄን ለማፈላለግ የብሪክስ አባል ሀገራት ቁልፍ ድርሻ አላቸው"፤ እንዲሁም "የጋዛ ውጥረት እንዲረግብና የተኩስ አቁም ስምምነት እንዲደረስ ዓለምአቀፉ ማህበረሰብ የተቀናጀ ጥረት ማድረግ አለበት፤ ለእስራኤልና ፍልስጤም ግጭት ፖለቲካዊ መፍትሄ መፈለግ ይኖርበታል፤ ለዚህም የብሪክስ አባል ሀገራት ቁልፍ ሚና አላቸው" ማለታቸው ከብሪክስ ርእዮተ-ዓለማዊ አቅጣጫ አንፃር ድርጅቱ የትኛውን እንደሚያራምድ ብዙዎች "ግልጽ ነው" በማለት ሲገልፁትም ይሰማል።

የብሪክስን አስፈላጊነትና ወቅታዊነትን አስመልክተው ከመሥራች ሀገራቱ አንዱ፣ የሕንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሱብራህማንያም ጃይሻንካር "ዓለም ባለብዙ መልክ ስለሆነች ባረጀው መንገድ አዲሱን አጀንዳ መፍታት አይቻልም"፤ "ከምንጋፈጣቸው ችግሮች አንዱ የምጣኔ ሀብት ጉዳይ ሲሆን ብዙ ሀገራት በጥቂቶች በጎ ፈቃድ እንዲኖሩም ሆነዋል" ብለው የነበረ መሆኑ ሆነ፤ "ሩሲያ [ብሪክስን] ከምዕራቡ ዓለም ጋር የምታደርገው ትግል አካል አድርጋ ትመለከታለች። ከዩክሬን ወረራ በኋላ የተጣለውን ማዕቀብ ለማሸነፍም ይረዳታል" የሚለው የጉዳዩ ተመራማሪዎች አስተያየትም በዚሁ ልክ ግልጽ ነውና በዚህ ጉዳይ ከዚህ በላይ መሄዱ አያስፈልግም።

ዓለማችን "ያደጉ" እና "ያላደጉ"፤ "ግራ"፣ "ቀኝ" ወዘተ ከሚባለው ጎራ ወጥታ (በከፊልም ቢሆን) "ጨፍልቀው ያደጉ" እና "በማደግ ላይ ያሉ" ሀገራት በሚሉ ምድቦች ተከፍላ እየተጠራች ትገኛለች። እነ ብሪክስም "በማደግ ላይ ያሉ" እና "ባለ ተስፋዎች" እየተባሉ ከሚገለፁት ቀዳሚዎቹ እየሆኑ ነው። (እዚህ ላይ "ያላደጉ" (አፍሪካን ለማለት ነው) የሚለው "በማደግ ላይ ያሉ" (ዴቨሎፒንግ) በሚል ከተተካ ሰንበት ያለ መሆኑን፤ ለውጡም የከባድ ፖለቲካዊና ርእዮተ-ዓለማዊ ትግል ውጤት መሆኑን ልብ ይሏል።) "ብሪክስን ተጠቅሞ ቀስ በቀስ አፍሪካ ከምዕራባውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ የባህል የሥርዓት ተፅእኖ ሙሉ በሙሉ ነፃ ለመውጣት ቀስ በቀስ አፍሪካን ሊገነባ ይችላል" እና የመሳሰሉ አስተያየቶችም እየተሰነዘሩ ይገኛሉ። የሰሞኑ የሀገራችን ብሪክስን የተመለከቱ ውሳኔና እንቅስቃሴዎችም የዚሁ አካል ተደርገው ሊወሰዱ የሚችሉ ናቸው።

### ወደ ኢኮኖሚው ዘርፍ እንምጣ፤

ሰሞኑን፣ "ከዓለም የቆዳ ስፋት 27 በመቶ በሚሸፍኑት፣ ከዓለም ሕዝብ የ42 በመቶው ባለቤት በሆኑት፣ ለጠቅላላው የዓለም ምርት 27 በመቶ ያህሉን በሚያበረክቱት፤ እንዲሁም፣ በፈጣን የምጣኔ ሀብት እድገት ላይ ከሚገኙ የዓለም ሀገራት መካከል ግንባር ቀደም በሆኑት ሀገራት ጥምረት የተመሠረተው ብሪክስ የአባል ሀገራቱ የገቢ ንግድ ከፍተኛ መሆኑ "ለወደፊት ተስፋና ተፅእኖ ፈጣሪነቱ እንደ መሠረት ድንጋይ እየተቆጠሩለት ይገኛሉ። በተለይ በምእራቡ ዓለም በኩል እነዚህን ለመድፈቅ በማሰብ ብሪክስን የማጣጣሉ ዘመቻ በስፋት እየተኬደበት መሆኑ ሌላው ለብሪክስ ተፅእኖ ፈጣሪነት በማያሻማ መልኩ ማሳያ መሆኑም እየተስተጋባ ነው።

ፈረንሳይ፣ ዩናይትድ ስቴትስ፣ ዩናይትድ ኪንግደም፣ ጀርመን፣ ጃፓን፣ ጣሊያን እና ካናዳን ካካተተው ጥምረት ጂ7 (ቡድን 7) በተፎካካሪነት የቆመው፤ ሁሉም አባል ሀገራት በዙር ለአንድ ዓመት በፕሬዚዳንትነት የሚመሩት ብሪክስ "አባል ሀገራቱ በዓለም ላይ ያሉ ሸቀጦችን ወደ ሀገራቸው በማስገባት ረገድ 14 በመቶ ጥቅል ድርሻ አላቸው፤ የቻይናን የገቢ ንግድ ብቻ ብንመለከት እስከ ሁለት ትሪሊዮን ዶላር ሲደርስ፣ በጥቅሉ አምስቱ ሀገሮች ብቻ 3 ነጥብ 6 ትሪሊዮን ዶላር የገቢ ንግድ ልውውጥ "ያላቸው መሆኑ፤ በአባልነት የሚያካትታቸው የብሪክስ ሀገራት (ኢራን፣ የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ እና ሳውዲ አረቢያ) 44 በመቶ የሚሆነውን ድፍድፍ ነዳጅ ዘይት ማምረታቸው፤ ብሪክስ ከዓለም ጂዲፒ 4 በመቶውን መያዙ የድርጅቱን አካሄድ ከወዲሁ ከባድና ተፅእኖ ፈጣሪ (potential impact) እንደሚያደርገው የብዙዎች ከግምት ያለፈ እምነት እየሆነ በመምጣት ላይ ይገኛል።

በደብሊን ትሪኒቲ ኮሌጅ የዴቨሎፕመንት ጂኦግራፈር የሆኑት ፕሮፌሰር ፓድሬግ ካርሞዲይ እንዳሉትና በጥናቶች ተጠቅሶ እንደሚታየው የብሪክስ አባል ሀገራት በሚገኙባቸው ቀጣናዎች ወሳኝ ሀገራት ናቸው፤ ይህ እንዳለ ሆኖ፣ በብሪክስ አማካኝነት አሁን ላይ ያለውን የዓለም ኢኮኖሚ ሥርዓት (dollar's dominance) እንዲወገድ አሊያም እንዲሻሻል በመጠየቅ በደቡባዊው የዓለም ክፍል የራሷ ድምጽ ከፍ ብሎ እንዲሰማ እየሠራች ያለችው ቻይና ደግሞ የበለጠ ተፅእኖ ፈጣሪ ናት።

ከዚህ አንጻር በመልማት ላይ ያሉ ሀገራት "የበለጠ ድምጽ እና ውክልና" እንዲኖራቸው በማስፈለጉ መነሻነት ለህልውና የበቃው ብሪክስ፣ ሰሞኑን ይፋ እንዳደረገው ሁሉን ነገር ጨርሶ የራሱን ገንዘብ (BRICS currency) ይፋ ያደረገና በቅርቡ ለአባል ሀገራቱ በቀላሉ ሊያቀርብ፤ የ55 ዶላር አቻ ዋጋ 1 ብሪክስ እንደሚሆን ይፋ አድርጎ የዓለምን ነባር የኢኮኖሚክስና የገበያ ፍልስፍናና አስተሳሰብ ከስሩ በመነቅነቅ እያንጫጫው ይገኛል።

ባንኩም እአአ በ2022 መገባደጃ ላይ ለመንገዶች፣ ድልድዮች፣ የባቡር መስመሮች እና የውሃ አቅርቦት ፕሮጀክቶች 32 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ ለአባል ሀገራት አቅርቧል። የመሠረተ ልማት ጉዳይ የብሪክስ ዋና ጉዳይ እንዲሆን የምትፈልገውና የደቡቡ ዓለም መሪ ድምጽ መሆን የምትሻው ቻይናም ለዚህ የባንኩ ተግባር የተከፈተ ልብ እንዳላት በተደጋጋሚ ገልፃለች።

### በብሪክስ እጅ ምን አለ?

እንደ "ዶላር እማያስፈልገኝ ደረጃ ላይ ደርሻለሁ" የምትለው ቻይና እና በዓለም አቀፍ ንግድ ሂደቱ ዶላር ሀገሯ እንዳይገባ ያገደችው ሩሲያ ያሉ ታላላቅ የዓለም ኃያላን ሀገራትን ያቀፈው ብሪክስ፤ በአህጉራቸው ላይ ተጽዕኖ ያላቸውን እንደ ደቡብ አፍሪካ እና ብራዚልንም አካትቷል፤ ከአፍሪካ ቀንድም ኢትዮጵያን። ድርጅቱ ከ3 ነጥብ 5 ቢሊዮን በላይ ሕዝብን የሚወክል፤ ከዓለማችን የቆዳ ስፋት 30 ከመቶውን የሚሸፍን ሲሆን፤ ይህም 45 በመቶ የሚሆነውን የዓለም ሕዝብ ይይዛል። የአባላቱ ድምር ምጣኔ ሀብት ከ28 ነጥብ 5 ትሪሊዮን ዶላር በላይ መሆኑ እየተነገረለት ያለው ብሪክስ፣ ከዓለም ኢኮኖሚ 28 በመቶውን፤ ከዓለም ጂዲፒ 36 በመቶ ያህሉን (G7 ሀገራት 30 በመቶ ነው ያላቸው) መሸፈኑም እንደ ትንግርት እየተነገረለት ነው።

ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርትን (በትሪሊዮን) ን በተመለከተም የተዘረዘረ አሃዝ ያለ ሲሆን፤ ቻይና 17.96፣ ህንድ 3.39፣ ሩሲያ 2.24፣ ብራዚል 1.92፣ ሳኡዲ አረቢያ 1.92፣ የተባበሩት አረብ ኤምሬተስ 0.51፣ ግብፅ 0.48፣ ደቡብ አፍሪካ 0.41፣ ኢትዮጵያ 0.31 ትሪሊዮን ዶላር እንዳላቸው የዓለም ባንክን ጠቅሰው ለንባብ ካበቁ ሚዲያዎች ለመረዳት ተችሏል።

እንደ ብሪክስ አተያይ፣ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ከ34 ትሪሊዮን በላይ እዳ ይጨፍርባቸዋል። ምእራባውያን ተብዬ አበዳሪዎች ደግሞ ከዚህ ሁሉ ትሪሊዮን ብድር ከሚገኝ ገቢ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ዶላሮች መጠባበቂያን (reserves) ያከማቹ ዘንድ እድልን ፈጥሯል። ይህ መቆም አለበት። ባለ እዳ ሀገራቱም ፊታቸውን እየቀነሱና እየወረደ ከመጣው ዶላር ወደ ብሪክስ የመገበያያ ገንዘብ ያዞሩ ዘንድ ጊዜው አሁን ነው። ከሻገተው የጦርነት፣ የጣልቃ ገብነት፣ እኔ አውቅልሃለሁ ባይነት፣ ዘር ማጥፋት፣ አጉል የበላይነት ከተጣበቀው የቅኝ አገዛዝ ሥርዓትም እንደዛው። ይህንንም የቬኑዙዌላው ፕሬዚዳንት ኒኮላስ ማንዱሮ "old colonial world with wars, interventions, genocide and a superiority complex" is being replaced by "a new world with BRICS." በማለት ከገለፁት ጋር መሳ ለመሳ መሆኑን በመግለፅ ሃሳባቸውን የሚያጠናክሩ ቁጥራቸው እየበዛ፣ የአባልነት ጥያቄዎቻቸውም እየጎረፈ ይገኛል።

የመጀመሪያው የድርጅቱ የመሪዎች ጉባዔ በሰኔ ወር 2009 በሩሲያ (ሴንት ፒተርስበርግ) አስተናጋጅነት የተካሄደው ብሪክስ የምዕራባውያን ሀገሮችን፣ ማለትም እንደ ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም እና የዓለም ባንክ ያሉ፣ እንዲሁም ለመንግሥታት ብድር የሚሰጡ "አንቱ" የተባሉ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማትን መቆጣጠሩ አይቀሬ መሆኑን ከድርጅቱ አመራሮች ባለፈ የምጣኔ ሀብት ምሁራን በእርግጠኝነት አዝወትረው እየተናገሩለት ይገኛሉ።

ኢትዮጵያን ጨምሮ በብሪክስ አባል ሀገራት እጅ ("ምን የሌለ ነገር አለ?" እስኪባል ድረስ) ብዙ ነገር ያለ ሲሆን፤ የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው። "The BRICS Wealth report: Challenging the Global economic order'' በሚል ርእስ ፌብሯሪ 2024 ለንባብ የበቃ ጽሑፍ እንደሚያስረዳው የድርጅቱ አባላት በከፍተኛ ደረጃ እያደጉና ሀብት እያፈሩ ሲሆን፤ እንደ አጠቃላይ ኢንቨስት ሊደረግ የሚችል (investable wealth) 45 ትሪሊዮን ዶላር ያላቸው ሲሆን፤ ሚሊየነር ባለሀብቶቹም በሚቀጥሉት 10 ዓመታት በ85 በመቶ ያድጋሉ ተብሎም ተተንብዮአል፡፡

በአሁኑ ሰአት በተለያዩ የሀብት ደረጃዎች ላይ ያሉ፤ በድርጅቱ ስር የሚገኙ ባለሀብቶች (BRICS millionaires፣ BRICS centi-millionaires እና BRICS billionaires) በርካቶች ሲሆኑ፣ ከ1 ሚሊዮን ዶላር በላይ ኢንቨስት ማድረግ የሚችሉ 1 ነጥብ 6 ሚሊየነሮች፤ ከ100 ሚሊዮን ዶላር በላይ ኢንቨስት ማደረግ የሚችሉ 4ሺህ 716 ማካከለኛ ቢሊየነሮች፣ እንዲሁም፣ 549 ቢሊየነሮች ይገኛሉ።

እንደዚሁ ጥናታዊ ሪፖርት ባለፈው አስር ዓመት አባል ሀገራቱ በግሉ ዘርፍ በርካታ ለውጦችን እና እድገቶችን ያስመዘገቡ ሲሆን፤ ከፍተኛዋ ቻይና 92 በመቶ በማደግ 862 ሺህ 400 ሚሊየነሮችን፤ 2ሺህ 352 መካከለኛ ቢሊየነሮችን፤ እንዲሁም 305 ቢሊየነሮችን ማፍራት ችላለች። ከአባል ሀገራቱ በመጨረሻ ደረጃ ላይ የምትገኘው ኢትዮጵያም ከፍተኛ እድገትን በማስመዝገብ የነበሯትን ሚሊየነሮች በ30 በመቶ በማሳደግ ለብሪክስ ብሎክ የበኩሏን በማበርከት ላይ እንደምትገኝ ነው እየተነገረ ያለው።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የስልጢ አባያ ሃይቅ ሙዝ አምራቾች - ከጠባቂነት ወደ አምራችነት

**ማህሌት አብዱል**

አርሶ አደር አሕመድ ረሺድ በስልጤ ዞን ምስራቅ ስልጢ ወረዳ ምዕራብ የቁጪ ቀበሌ ነዋሪ ናቸው። በቀበሌያቸው ስልጢ አባያ ሃይቅ ያለ ቢሆንም፣ እሳቸውም ሆነ የቀበሌው አርሶ አደሮች ሃይቁን ከመመልከት ባለፈ ተጠቅመውበት አያውቁም። ይልቁንም ከ30 ዓመት በፊት በሃይቁ ዙሪያ በቀደሙ አባቶቻቸው የተተከለውን ባህር ዛፍ እየሸጡ ገቢ ሲያገኙ ኖረዋል።

ይህ ግን ብቻውን ኑሯቸውን ሊደጉሙላቸው ባለመቻሉ ዘወትር መንግሥት የሚሰጠውን ሴፍትኔት ይጠብቁ ነበር። ሃይቁ ዙሪያ ባላቸው መሬት ላይ የተወሰኑ ሰብሎችን ለማልማት ቢሞክሩም በባህር ዛፉ ስር ምክንያት ምርታማነቱ እዚህ ግባ የሚባል አልሆን አላቸው፤ በዚህ የተነሳም ኑሯቸው ከእጅ ወደ አፍ የሚባል እንደነበር ያስታውሳሉ።

አርሶ አደር አሕመድ የ‹‹ስልጢ አባያ ሃይቅ ዙሪያው ለረጅም ዓመታት በባህር ዛፍ ተከቦ የኖረ ነው። አካባቢው ለምና ምቹ ቢሆንም፣ ባህር ዛፍ እየቆረጥን ከመሸጥ በዘለለ ሕይወታችን ላይ ጠብ የሚል ልማት አልነበረም›› ይላሉ።

ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ ግን የወረዳውና የዞኑ ግብርና ባለሙያዎች አርሶ አደር አሕመድንም ሆነ መላውን የቀበሌያቸውን ነዋሪ ለችግር የዳረገውንና የጠባቂነት ሥነልቦና እንዲያዳብሩ ምክንያት የሆናቸውን ባህር ዛፍ መንጥረው በምትኩ ሙዝ ቢያመርቱ ኑሯቸውን እስከ ወዲያኛው እንደሚቀይሩ ይመከሯቸዋል። እነሱም ምክሩን ተቀብለው ወደ ተግባር ለመቀየር ጊዜ አልወሰዱም፤ እሳቸውና የተወሰኑ አርሶአደሮች ተሞክሮ ለመቅሰም ወደ ሙዝ ማዕከሏ አርባ ምንጭ አቀኑ። ልምድና ተሞክሮ ብቻ ሳይሆን ምርጡን የተሻሻለውን የአርባ ምንጭ ሙዝ ችግኝ ይዘው ተመለሱ።

አርሶ አደር አሕመድና ጎረቤቶቻቸው በማህበር ተደራጁ፤ ሁለት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥም በሃይቁ ዙሪያ ያለውን ሃያ ሄክታር መሬት ከባህር ዛፍ ወረራ አፀዱ፤ በምትኩም ያመጡትን ሙዝ ተከሉ። የባህር ዛፍ ምርት ለማግኘት ሰባት ዓመታትን መጠበቅ ግድ ይላቸው የነበሩት እነዚህ አርሶ አደሮች፤ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የሙዙን ችግኝ አባዝተው በመሸጥ በኪሳቸው ብር ማስገባት ጀመሩ። ምርቱም ደረሰና አካባቢውን ሁሉ በሙዝ አጥለቀለቁ። ጎን ለጎንም እንደ ሽንኩርትና ጎመን ያሉ የጓሮ አትክልቶችን በማልማት ለቤተሰባቸው ምግብ ፍጆታም ሆነ ለገበያ ያቀርባሉ።

"ለሌሎች አርሶ አደሮች የሙዝ ችግኝ እንሸጣለን፤ ምርቱም ሰፊ በመሆኑ ከቀበሌያችንና ወረዳችን አልፈን በአጎራባች ዞኖች በሚገኙ ገበያዎች ላይ በመሸጥ ተጠቃሚ ሆነናል›› ይላሉ። አሁን የገቢ አቅማቸው በከፍተኛ ደረጃ በመጎልበቱ ምክንያት የቤተሰቦቻቸውን የእለት ጉርስ ከመሸፈን አልፈው ተጨማሪ ቤትና ሱቅ መስራት መቻላቸውን ነው አርሶአደሩ የሚናገሩት። ‹‹በአሁኑ ወቅት ገቢያችን ጨምሯል፤ ኑሯችን ተሻሽሏል፤ ልጆቻችንን እያስተማርን ነው›› በማለትም ገልጸዋል።

ለዚህ ለመድረሳቸው የወረዳውና የዞኑ ግብርና ባለሙያዎች ድርሻ የጎላ እንደሆነም ጠቅሰው፣ ‹‹ባለሙያዎቹ ከእኛ ቀድመው ማሳችን ላይ ይገኛሉ፤ ሁሌም የሙዝ ማሳችንን የልጃቸው ያህል ይንከባከባሉ። በጠራናቸው ቁጥር ፈጥነው ይመጣሉ›› ሲሉ ይገልጻሉ። በተለይም ወረዳው የተሻሻሉ ዝርያዎችን በማቅረብ፣ ማዳበሪያና መሰል የግብርና ግብዓቶችን በፍጥነትና በፈለጉት መጠን እንዲያገኙ ያላሰለሰ ጥረት ማድረጉንም አርሶአደሩ ይጠቅሳሉ።

አርሶ አደር አሕመድ እንደሚናገሩት፤ መላው የማህበራቸው አባላት የሙዝ እርሻውን የማስፋፋትና ጎን ለጎንም ሌሎች ሰብሎችን በማምረት ማዕከላዊ ገበያን መቀላቀል ይፈልጋሉ። ሆኖም በአካባቢያቸው በተለይም ምንም አይነት የመንገድ መሠረተ ልማት ባለመዘርጋቱ ምክንያት ምርታቸውን ለገበያ ማቅረብ አልቻሉም። ዘንድሮ እንኳን ሰፊ የሙዝ ምርት ቢገኝም አቅርቦቱ ከተጠቃሚው ፍላጎት በላይ በመሆኑ ምክንያት ጥቂት የማይባለው ሙዝ ለብልሽት እየተዳረገባቸው ነው።

"በስልጢ አባያ ሃይቅ ዙሪያ ያሉ ቀበሌዎች በሙሉ ለምለም ናቸው፤ ይህን ምቹ የተፈጥሮ ሀብት በመጠቀም የሙዝ፣ የፓፓያና የአባኮዶ ምርት በስፋት እያመረትን ነው፤ ምርታችን ከዚህ በላይ የማስፋትና ለማዕከላዊ ገበያ የማቅረብ ፍላጎቱም ሆነ ብቃቱ ቢኖረንም ግን በተለይ በአካባቢያችን የመንገድ መሠረተ ልማት ባለመኖሩና



ገበያ ማቅረብ ባለመቻላችን ምርታችን ለብልሽት እየተዳረገ ነው›› ሲሉ ያብራራሉ። የክልሉና የፌዴራል መንግሥታት ለዚህ የመንገድና የገበያ ትስስር ችግር በፍጥነት መፍትሔ እንዲሰጣቸው ይጠይቃሉ።

የምዕራብ የቁጪ ቀበሌ ሊቀመንበር አቶ አሕመድ መሃመድ በበኩላቸው፤ በሀይቁ አካባቢ ለበርካታ ዓመታት የኖረው የባህር ዛፍ በአካባቢው የተፈጥሮ ሀብት ላይ በተለይም በስልጢ አባያ ሃይቅ ላይ ያደረሰውን ጉዳት በሚመለከት ከወረዳውና ከዞኑ አመራሮች ጋር በመሆን ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ መሠራቱን ያስታውሳሉ። ከነዋሪው ጋር መተማመን ከተፈጠረ በኋላ ከተመረጡ አርሶአደሮች ጋር በመሆን አርባምንጭ ተሞክሮ ለመቅሰም በሄዱበት ወቅት ከፍተኛ የሆነ መነሳሳትና ቁጭት ያደረባቸው መሆኑን ይገልፃሉ። ‹‹ባየሁት ነገር ከፍተኛ ቁጭት ስላደረብኝ እንደተመለስን የራሴን ባህር ዛፍ በመቁረጥ ነው ለሌሎች ተምሳሌት ሆኜ ሥራውን ያስጀመርኩት›› ሲሉ ተናግረዋል።

አርሶ አደሩም ሳያመነታ ወዲያውኑ ዛፉን ቆርጦ ወደ ሙዝ ማምረት ሥራው መግባቱን ጠቅሰው፤ ሙዙ እስከሚደርስም የሙዝ ችግኝ እያፈሉ ለሌላ ቀበሌ አርሶአደሮች በመሸጥ እንደሚጥሚጣ፣ ሽንኩርት እና ድንች የመሳሰሉ የጓሮ አትክልቶችን በማምረት ርዳታ ጠባቂ የነበረውን የቀበሌውን አርሶ አደር ሕይወት መቀየር መጀመራቸውን ያመላክታሉ። "ከዚህ ቀደም ከ450 በላይ የሚሆነው የቀበሌያችን ነዋሪ የሴፍትኔት ተጠቃሚ ነበር፤ አሁን ግን የሙዝ ምርቱ በፈጠረው የሥራ እድል ከጠባቂነት ወደ አምራችነት ተቀይረዋል" ሲሉም ያስረዳሉ።

አቶ አህመድ ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች አጎራባች ቀበሌዎች ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሙዝ ችግኝ በድጋፍ መልክ መስጠታቸውን ይጠቁማሉ። " በግሌ በችግኝ ብቻ እስከ 15 ሺ ብር አግኝቻለሁ፤ ሌሎችም በተመሳሳይ ችግኝ በማፍላትና ሙዝ በማምረት የቤተሰባቸውንና የራሳቸውን ኑሮ እየለወጡ ነው›› የሚሉት አቶ አሕመድ፤ ይህም የቀበሌው አርሶአደር ጥረት ከቀበሌው ባሻገር ለወረዳው የንግድ እንቅስቃሴ እና ልማት መስፋፋት ትልቅ አቅም እየሆነ መምጣቱንም ያብራራሉ።

የቀበሌው ሊቀመንበር እንደሚሉት፤ ከዚህ ቀደም ማንኛውም የቀበሌያቸው ነዋሪ አንድ ኪሎ ሙዝ ለመግዛት ቡታጀራ አልያም ወራቤ መሄድ ይጠበቅበት ነበር። አሁን ግን ከራሳቸው አልፈው ለምስራቅ ስልጢ በሙሉ ማቅረብ ጀምረዋል። አሁን ላይ የቀበሌያቸው አርሶአደሮች ሙዝንም ሆነ ሌሎች ፍራፍሬና አትክልቶችን በስፋት ለማምረት ርብርብ እያደረጉ ናቸው።

ይሁንና በማዕከላዊ ገበያ ትስስር ያልተፈጠረላቸው በመሆኑ እሳቸውም ምርቱ ይበላሻል የሚል ስጋት አድሮባቸዋል። የገበያ ትስስሩ መፍጠር ከተቻለ ግን በርካታ የአካባቢው ወጣቶችን የሥራ እድል ተጠቃሚ የሚያደርግ ልማት ይመጣል የሚል እምነት እንዳላቸው ገልጸዋል።

ከመንገድ መሠረተ ልማት አኳያ አርሶአደሮቹ ያነሱትንም ችግር ሊቀመንበሩም ይጋራሉ። "በወረዳችን ካሉት 11 ቀበሌዎች ውስጥ አራቱ በበጋ መሥራት የማይቻልባቸው ናቸው። ሰባቱ ቀበሌዎች ግን ፍራፍሬም ሆነ ሌሎች ሰብሎችን በስፋት ማምረት የሚቻልበት ምቹ ሁኔታ አለ። ሆኖም የመንገድ መሠረተ ልማት ባለመኖሩ ምክንያት እንደልብ ተንቀሳቅሰን ማምረትም ሆነ ያመረትነውን ገበያ ማድረስ ተቸግረናል" ሲሉ ያብራራሉ። ይህን ችግር በሚመለከት ከወረዳውና ከዞኑ አመራር ጋር ተደጋጋሚ ውይይቶች መደረጋቸውንና ችግሩ ብዙ ባልረዘመ ጊዜ ይፈታል የሚል እምነት እንዳላቸውም አመላክተዋል።

የምስራቅ ስልጢ ወረዳ ምክትል አስተዳዳሪና የግብርና ፅህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጀማል ሃሰን እንደሚሉት፤ የስልጢ አባያ ሃይቅ የዞኑ ማዕከል ተደርጎ የሚቆጠር ቢሆንም፣ እስካሁን ልማት ላይ ባለመዋሉ አመራሩ ይወቀስ ነበር። ከባህር ዛፍ ውጪ ለልማትም ሆነ ለቱሪዝም መስህብነት ያለመዋሉ ጉዳይ የብዙ የአካባቢው ተወላጆችም የዘመናት ቁጭት ሆኖ ቆይቷል። ይህን ቁጭት መነሻ በማድረግ አመራሩ በተለይም ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ ተጨባጭና ሊተገበሩ የሚችሉ የልማት እቅዶችን በመያዝና ታች ድረስ ወርዶ ባከናወናቸው ሥራዎች ከፍተኛ ውጤት መጥቷል።

"በተለይም ሃይቁን የመታደግ አጀንዳ ቀዳሚ ሥራ አድርገን የተነሳን ሲሆን፤ ያለንንም እምቅ አቅም በመጠቀም የወንዙን ዙሪያ ማልማት ይገባል የሚል መግባባት ይዘን ነው ርብርብ ያደረግነው›› የሚሉት አቶ ጀማል፤ የአዋጭነት ሰነድ በማዘጋጀት እድሜ ጠገቡን ግዙፍ ባህር ዛፉ ጥቅምና ጉዳት ከግምት ውስጥ ያስገባ ሥራ መከናወኑን ያስረዳሉ። ለዚህ ደግሞ ባለሙያዎችን ያሳተፈ ጥናት መደረጉንና የአካባቢው ማህበረሰብ በጉዳዩ ዙሪያ እንዲወያይ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር መግባባት በተፈጠረበት ሁኔታ ወደ ልማት መግባቱን ያብራራሉ።

ባህር ዛፍ የመንቀል ሥራም ከአመራር መጀመር አለበት የሚል አቋም በመያዙ እሳቸውም የራሳቸውን የባህር ዛፍ መሬት በማፅዳት በሙዝ መተካታቸውን ይጠቅሳሉ። "ይህንን ባህር ዛፍ የመመንጠር ሥራ ስንጀምር አርሶአደሩ በአንድ በኩል መሬታቸው ወደ ቀድሞ ለምነት ይመለሳል የሚል ተስፋ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ባህር ዛፉ ብዙ ዓመት ከመቆየቱ የተነሳ ሙሉ ለሙሉ የመመንጠር አቅም ላይኖረን ይችላል፤ ምርትም እንደታሰበው ላይገኝ ይችላል የሚል ስጋት ነበረው" ይላሉ።

ዞኑና የወረዳው አመራር በመቀናጀት መስኖ ገብ በሆኑ ሰባት ቀበሌዎች ላይ የሙዝ ማልማት ሥራው መጀመሩን ያመለክታሉ። ከፍተኛ ወጪ በመመደብ የሙዝ ችግኝ ለአርሶአደሩ በማከፋፈልና የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ በስፋት ማልማት መቻሉን፤ አርሶአደሮቹ በአጭር ጊዜ ውስጥም ምርታማ በመሆናቸው ኑሯቸውም ከታሰበው ጊዜ ፈጥኖ መሻሻል ማሳየቱን ያስገነዝባሉ።

በወረዳዋ በተገኘው ፈጣን ውጤትና ምርታማነት ከፌዴራል ጀምሮ ያሉ ከፍተኛ የመንግሥት አመራሮች በሰባት ዙር ጉብኝት መደረጉን ጠቅሰው፣ ወረዳዋም እንደምርጥ ተሞክሮ ለሌሎች ተምሳሌት ሆና እየቀረበች መሆኑን አስታውቀዋል።

በስልጢ አባያ ሃይቅ ዙሪያ 105 ሄክታር መሬት በሙዝ መልማቱን በዚህም ከ262 ሺ በላይ አርሶአደሮች ተጠቃሚ መሆን መጀመራቸውን ተናግረው፤ ‹‹በወረዳው ከፍተኛ መነቃቃት ስለተፈጠረ ክረምት ላይ ብቻ ሳይሆን በጋ ላይም በመስኖ ሙዝ እየተተከለ ነው። የሴፍትኔት ተጠቃሚ የነበረ አንድ አርሶአደር በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ብቻ ችግኝ በመሸጥ 30 ሺ ብር ያገኘበት አጋጣሚ አለ›› በማለት ያስረዳሉ። መስኖ የሌለባቸው ቀበሌዎች ወጣቶች ሳይቀሩ በሙዝ ምርት በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ የሥራ እድል ተጠቃሚ ሆነዋል ይላሉ።

በተለይም ደግሞ በሌማት ቱሩፋት መርሃ ግብር አማካኝነት አርሶአደሩ በክላስተር እንዲደራጅ በማድረግ ምርታማነቱን እንዲያሳድግ መደረጉ በዘርፉ ከፍተኛ እምርታ መመዝገቡን የወረዳው ምክትል አስተዳዳሪ ይገልፃሉ። ይህም ለአመራር ምቹ ያደረገው ከመሆኑም ባሻገር ችግሮች ሲያጋጥሙ በፍጥነት ለመፍታት ትልቅ አቅም የፈጠረ እንደሆነ ነው ያነሱት። ‹‹ሙዝ ሲተከል ዘርፈ ብዙ ጥቅም ነው ያለው፤ ለምሳሌ እዚህ ባህር ዛፍ ነቅለን በተከልነው ሙዝ ከ10 ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆን ገንዘብ ያገኘነው ጎን ለጎን በተከልናቸው የጓሮ አትክልቶች ነው›› ሲሉም አስረድተዋል።

የወረዳውን ግብርና አሠራር ከማዘመን አኳያ በተለይ ሰፋፊ የእርሻ መሬት ባላቸው ቀበሌዎች ላይ በተደረገው ርብርብ ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ መካናይዝድ የሆነ የእርሻ ሥራ መጀመሩን ይጠቅሳሉ። በተጓዳኝም በተፈጠረው መነቃቃት ብቻ ዓምና ሁለት አርሶአደሮች በራሳቸው አቅም ትራክተር መግዛታቸውን ያመለክታሉ። ወደፊትም በአንድ ቀበሌ ቢያንስ አንድ ትራክተር ፤ በአንድ ወረዳ አንድ ኮምባይነር መኖር አለበት የሚል አቋም ተይዞ እየተሠራ ስለመሆኑ ነው ያብራሩት።

አቶ ጀማል ከገበያ ትስስርና ከመንገድ መሠረተ ልማት ችግር ጋር በተያያዘ በአርሶአደሮቹ የተነሱ ስጋቶችን በሚመለከት ‹‹በአርሶአደሮቹ የተነሱት ስጋቶች ተገቢና እኛም የምንጋራቸው ናቸው፤ በተለይም ወቅቱን ጠብቆ ከመጠገን አንፃር ክፍተቶች እንዳሉ እኛም እናምናለን›› ብለዋል። ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ዞን ድረስ ያሉ አመራሮች ተደጋጋሚ ለሚመለከተው አካል ጥያቄ ማቅረባቸውን ያነሳሉ። ሆኖም የቀድሞ ደቡብ ክልል ከነበረው የተበታተነ አሠራር አኳያ የሚጠየቅም አካል ባለመኖሩ ለዓመታት የሕዝብ መልካም አስተዳደር ጥያቄ ሆኖ መቆየቱን ያስታውሳሉ።

ወረዳው ባለው አቅም መንገዶችን የመጠገን ሥራ እየሠራ ቢሆንም ችግሩ ሰፊ በመሆኑ በወረዳው አቅም ብቻ የሚፈታ ባለመሆኑ ከሚመለከተው የክልል አመራር ጋር ውይይት እየተደረገበት ስለመሆኑ ምክትል አስተዳዳሪው ይገልፃሉ። ከገበያ ትስስሩ አኳያ ግን እንደዞንም ሆነ እንደ ወረዳ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለይም የቅዳሜእና የእሁድ ገበያዎችን በማዘጋጀት አርሶ አደሩ ምርቱን የሚሸጥበት እድል መመቻቸቱን ይጠቁማሉ።

‹‹ከዚህም ባሻገር እንደወረዳችን ከ350 በላይ አባላት ያሉት የሸማቾች ህብረት ሥራ ማህበር አደራጅተናል፤ እውቅና አግኝተናል፤ በመሆኑም ከወረዳው ተጠቃሚዎች የተረፈውን ምርት ወደ ማዕከላዊ ገበያ ጭምር ማቅረብ በሚቻልበት ሁኔታ ትስስር ለመፍጠር እየሠራን ነው፤ በመሆኑም የወረዳችን የሙዝም ሆነ ሌሎች ምርቶች ለውጭ ገበያ ጭምር በማቅረብ ለሀገር የውጭ ምንዛሪ ግኝት ትልቅ አቅም እንሆናለን የሚል እምነት አለን›› ሲሉም አብራርተዋል።

አዲስ ዘመን | ሰኞ ሚያዝያ 21 ቀን 2016 ዓ.ም



# የትምህርት አይነቶች፤ መንቀልና መትከል

ግርማ መንግሥቴ

ብዙ ጊዜ የምግብ አይነቶች፣ የአልባሳት አይነቶች ወዘተ ሲባል እንጂ ስለ ትምህርት አይነቶች በአደባባይ ሲነገር አይሰማም። ከሚመለከተው ተቋም በስተቀር ጉዳዩን ጉዳዬ ብሎ ሲብሰከሰክ የሚውልና የሚያድር ቀርቶ የሚያረፍድ እንኳን የለም። ማንም ልብ አይበላቸውም እንጂ የትምህርት አይነቶች ሁሌም የመነጋገሪያ ርእስ ከመሆን አምልጠው አያውቁም።

የኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት የሚታሰበው በ1898 ዓ.ም "እስከ አሁን ማንም የእጅ ሥራ አዋቂ የነበረ ሰው በውርደት ሥም ይጠራ ነበር። ስለዚህም ማንም ሰው ለመማርና ለመሠልጠን የሚደክም አልነበረም። ... ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ ለወደፊትም ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች ሁሉ ከስድስት ዓመታቸው በኋላ ወደ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ይሁን።" የሚል አዋጅ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡

የትምህርት አይነቶች፣ በተለይም በዚህ ዘመን እጅግ አነጋጋሪ፣ እጅግ ወስብስብ፣ ሲበዛ በፖለቲካል ርእዮት የተነከሩ የፖለቲካ መሳሪያዎች፣ የማንነት ማጥቂያ ምሳሮች፣ የማንነት መፈለጊያ ማይክሮስኮፖች ወዘተ በመሆን ነገር ዓለሙን ሁሉ በአራቱም ማእዘን እየናጡት ይገኛሉ። አሜሪካ የጥቁር አሜሪካዊው ጆርጅ ፍሎይድን ሞት (በነጩ ፖሊስ መገደል) ተከትላ ያነጣጠረችው "የትምህርት አይነቶች" ላይ ሲሆን፤ አወዛጋቢው "ክሪቲካል ሬስ ቲዎሪ" ን እንደ አንድ የትምህርት አይነት እንዲሰጥ ወስና በመሰጠት ላይ ትገኛለች፡፡

ድሮ ድሮ አሜሪካ ወደ ህዋ የመምጠቅን ስኬታማነት በሩሲያ በመነጠቋ ምክንያት እርር፣ እርር ድብን ማለቷን ተከትሎ በብርሃን ፍጥነት ፈቷን ያዞረችው ወደ ትምህርት አይነቶቿና የጎደሉቱ እንደ ነበር በታሪክ በደማቁ ከመፃፉም በላይ፤ በተለይ በሥነ- ትምህርት ባለሚሎች ዘንድ ሁሌም ሲነሳ ይውላል፤ ያድራልም።

ከመልካም መልካሙ ለመነሳት ብለን አሜሪካንን አነሳን እንጂ፣ በኃይል ሥልጣን የተቆጣጠሩ መንግሥታት ሁሉ ገና ወንበራቸው ላይ በአግባቡ ሳይቀመጡ ዓይናቸው የሚያነጣጥረው የትምህርት ሥርዓቱና የትምህርት አይነቶች ላይ ነው። በምሳሌ ማየት ካስፈለገ በደርግ ሥርዓት ወቅት ሲሰጡ የነበሩ የትምህርት አይነቶች (ከበባት ሳይቀሩ) በኢህአዴግ እየተነቀሉ እንደተጣሉ መጥቀሱ ብቻ በቂ ነው። በተለይ ከላይ በጠቀስነውና የማንነት ጥያቄ ጎልቶ በወጣበት የወቅቱ ፍልስፍና (ከተባለ) ከትምህርት አይነቶች ሁሉ እንደ "የቋንቋ ትምህርት" መከራውን ያየ አለ ለማለት ድፍረቱ አይኖርም።

የታሪክ፣ የባዮሎጂ (ከሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ)፣ የኃይማኖት እና ሌሎችም ምን ያህል የእሰጥ አገባ አጀንዳዎች እንደ ሆኑ እያየን–ተመለከትን እንገኛለን። የግብርና እና የገበሬ ሀገር በሆነችው ኢትዮጵያ ግብርና (እርሻ) የተባለው የትምህርት አይነት ከነከበቡ ከትምህርት ቤቶች መነቀሉን ለምናውቅ ሰዎች ነገሩ ሁሉ ግልፅ ሲሆን፤ ሙዚቃ፣ እጅ ሥራ፣ እንጨት ሥራ እና ሌሎችም ተመሳሳይ እጣ እንደ ገጠማቸው ይታወቃልና የትምህርት አይነቶች የመደብ ትግል የሚካሄድባቸው የፍልሚያ ሜዳዎች የሆኑ እስኪመስለን (ካልሆኑ ማለት ነው) ድረስ የየዘመኑ ንቅናቄና ስር ነቀል አብዮቶች ሰለባዎች ናቸው።

ቀጥሎ የምንጠቅሰውን ሰነድን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት የሚመለከታቸውን ካነጋገረ በኋላ "በአዲሱ የሥርዓተ-ትምህርት ትግበራ ከአንደኛ ደረጃ እስከ መሰናዶ ትምህርት ቤት ያሉ ትምህርቶች ላይ የሚቀነሱ እና እንደ አዲስ የሚጨመሩ የትምህርት አይነቶች መኖራቸው ተገለጸ።" የሚል ዜና ለአየር አብቅቶ የነበረ መሆኑን ስናስታውስ ከላይ እየተነጋገርንበት የመጣነው ጉዳይ ይበልጥ ግልፅ እየሆነ፤ "የሚቀነሱ" እና "የሚጨመሩ" የሚሉትም፤ "ለምን?" የሚል ጥያቄን በማጫር ይበልጥ ጥርት እያሉ ይሄዳሉ፡፡

ወደ ሰነዱ ከመሄዳችን በፊት ግን "መቀነስ" ም ሆነ "መጨመር" የሚቻለው በሕግ እና በሕግ አግባብ ብቻ መሆኑን መገንዘብ ፋይዳ አለው። ለምሳሌ ሰሞኑን በአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ርምጃ የተወሰደበትና 6ኛ እና 8ኛ ክፍሎችን እንዳያስፈትን የተከለከለው ጊብሰን አካዳሚ ከቀረቡበት በርካታ ክሶች አንዱ ከመስተዳድሩ እውቅና ውጪ "የትምህርት አይነት ጨምሮ ማስተማር" ሲሆን፤ ከቋንቋ ትምህርት ("የአፍ መፍቻ ቋንቋ የሀገራችን እንግሊዝኛ ነው' ብሎ ስታንዳርድ እስከመያዝ መድረሱ"፣ "የሀገር በቀል ቋንቋ ጠል መሆን"፤ "የትምህርት ቋንቋ አለማክበር" እና ሌሎችም) ጋር በተያያዘም ስህተት ሆነው የተገኙበት ተግባራቱ ቀላል አይደሉም።

> **የኢኮኖሚክስ እና የሥነ-ዜጋ ፈተናዎች ውጤቶች ውድቅ ወደ ተደረጉበት፤ ወደ የማህበራዊ ሳይንስ ስንመጣ ደግሞ ተማሪዎች ለ12ኛ ክፍል ፈተና የሚቀመጡባቸው ስድስት የጋራ ትምህርቶች ያሏቸው መሆኑን የምንመለከት ሲሆን፤ ከእነዚህም በአንዱ ጥሩ ነጥብ ካላቸው ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡበት መሆኑ ነው**

ከዚህ አኳያ "ከ2015 ዓ.ም ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ የሚገባው አዲሱ የኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት [ሰነድ] ምን ምን ጉዳዮችን አካቷል?" ብለን ስንጠይቅ ከላይ የገለፅናቸውንና እየተነቀሉ የተጣሉትን መልሶ የመትከል ተግባርን ያካተተ ስለ መሆኑ "ከመዋለ ሕፃናት አንስቶ የግብረገብ ትምህርት መስጠት" ግዴታ መሆኑን፤ እንዲሁም፣ "ተማሪዎች ከቅድመ መደበኛ እስከ 6ኛ የግብረገብ ትምህርት አይነት፣ ከ7ኛ ክፍል ጀምሮ የሥነዜጋ ትምህርት እንዲወስዱ ያስገድዳል።" ሲል ማስፈሩ፤ የጤና እና የግብርና ትምህርት አይነቶችንም ማካተቱ ተጠቃሽ ነው። (እዚህ ጋ፣ የግብረ-ገብ ትምህርት፣ በተለይ በንጉሡ ዘመን "ወሳኝ" ከሚባሉት የትምህርት አይነቶች አንዱ እንደ ነበር ማስታወስ ይገባል።)

በአዲስ አበባ ለ9ኛ እና 10ኛ ክፍል የሚሰጠው የኢኮኖሚክስ ትምህርት "ፐርፎርም ኤንድ ቪዥዋል አርት" በሚል መተካቱ፤ በ11ኛ እና 12ኛ ክፍል በድጋሚ ከሚሰጡ የትምህርት አይነቶች በተጨማሪ ሥራና ቴክኒክ ላይ የሚያተኩሩ የማኑፋክቸሪንግና ኮንስትራክሽን የትምህርት አይነቶች በየደረጃው ተለይተው መጨመራቸው እና ሌሎችም ተገቢ ማሳያዎች ናቸው።

ከ322 ሺ በላይ ተማሪዎች ለፈተና ከተቀመጡበትና ከሰኔ 6 እስከ 11 ቀን 2011 ዓ.ም የተሰጠውን ፈተና (እና አስከትሎ የነበረውን ችግር ያስታውሷል) በተያያዘ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አኳያም «ተማሪዎችንም ፍትኃዊ በሆነ መልክ ሊያወዳድር እና ከእነሱ ችሎታ ባሻገር ምንም መበላለጥን ሊያስከትል የማይችል ሆኖ ስላገኘነው እነዚህን ተጠቅመን ተማሪዎችን ወደ ዩኒቨርሲቲ መመደብ እና የተለያዩ ሥራዎችን ለመሥራት ወስነናል» በማለት መነሻውን ካስቀመጠ በኋላ "ከተፈጥሮ ሳይንስ የትምህርት ዘርፍ ፊዚክስ፣ ከማኅበራዊ ሳይንስ የትምህርት ዘርፍ ደግሞ የጂኦግራፊ ፈተናዎች ለመመዘኛነት ተመርጠዋል።" የሚለው የወቅቱ የኢትዮጵያ ሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ መግለጫና ሌሎችም ከዚሁ ከትምህርት አይነቶች ጋር በቀጥታ የተያያዙ ናቸውና "የትምህርት አይነቶች" ጉዳይ የዋዛ ፈዛዛ አለመሆኑን በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

ባደጉት ሀገራት "የተሻለ ገንዘብ ማስገኘት የሚችሉ የትምህርት አይነቶች ተብለው [የሚመረጡ አሉ]። ብዙውን ጊዜ ጥሩ ገንዘብ ማግኘት የሚፈልግ ሰው "ስቴም" (STEM) ተብለው የሚታወቁትን ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስና እና ሒሳብ የትምህርት አይነቶችን እንዲማር ይነገረዋል።" የሚል ምክር ሲሰነዘር መስማቱም የትምህርት አይነቶች ሚና የተለያዩ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፤ ጠብሰቅ ካለ ገቢ አኳያም የየራሳቸው ሚና አላቸውና የትምህርት አይነቶችን "የትምህርት አይነቶች" ብቻ ብሎ ማለፍ ከስህተት እንዳይጥል መጠንቀቅ ያስፈልጋል ።

ከስቴም ጋር በተያያዘ፣ በድሬዳዋ አስተዳደር ስር ከሚገኙ የ1ኛ እና 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሳይንስ (ፊዚክስ፤ ባዮሎጂና ኬሚስትሪ) እና ሒሳብ የትምህርት ዓይነቶች የተሻለ ውጤት ያላቸውን ተማሪዎች በመመልመል በተግባር የተደገፈ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሥልጠና የሚሰጠውን፣ የድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ስቴም ማዕከል (STEM Center)ን በማሳያነት መውሰድ ይቻላል።)

"ግብርና 11ኛ እና 12ኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲማሩት፤ በብሔራዊ ፈተናነትም የ12ኛ ክፍል ፈተና እንዲፈተኑት ይደረጋል" የሚለውም "ትልቅ ነበርን፤ ትልቅም እንሆናለን" እንደሚለው የአንድ ኤፍኤም ሬዲዮ መሪ ቃል፣ የነበረውን፣ በኋላም የተነቀለውን የትምህርት አይነት ወደ ነበረበት የመመለስ ሥራ ነውና የአሁኑን ሥርዓተ ትምህርት ያስመሰግነዋል። በተለይ፣ ወደ ከፍተኛ የግብርና ትምህርት ተቋማት (ግብርና ኮሌጆች) የሚገቡና በሙያው ሠልጥነው የሚወጡ ምሩቃን እስኪጠፉ ድረስ የነበረውን ክፍተት ያየ የትምህርት ሥርዓት ከመሆኑ አኳያ የበለጠ ያስመሰግነዋልና ይበል ሊባል ይገባል።

ወደ አሁኑ፣ ወደ ወቅታዊው ጉዳይ ስንመጣ የአሁኑ የትምህርት አስተዳደርን ውሳኔዎች የምናገኝ ሲሆን፤ አንዱም ተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት የመረጠ ተማሪ ሰባት የትምህርት አይነቶችን ለአካዳሚክስ (ለ12ኛ ክፍል ፈተና) የሚጠቀም መሆኑ ሲሆን፤ እነሱም እንግሊዝኛ፣ ሂሳብ፣ ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪ፣ ባዮሎጂ፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ እና ግብርና ናቸው። ከእነዚህ ከሰባቱ ውጭ ደግሞ በምርጫ ተማሪዎች አምስት የትምህርት መስኮችን መርጠው መከታተል የሚችሉ ሲሆን፤ የትምህርት መስኮቹም ማኑፋክቸሪንግ፣ ኮንስትራክሽን፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ ጤና ሳይንስና ግብርና ሳይንስ መሆናቸው በሰነዱ ላይ ሰፍሮ ይገኛል።

የኢኮኖሚክስ እና የሥነ-ዜጋ ፈተናዎች ውጤቶች ውድቅ ወደ ተደረጉበት፤ ወደ የማህበራዊ ሳይንስ ስንመጣ ደግሞ ተማሪዎች ለ12ኛ ክፍል ፈተና የሚቀመጡባቸው ስድስት የጋራ ትምህርቶች ያሏቸው መሆኑን የምንመለከት ሲሆን፤ ከእነዚህም በአንዱ ጥሩ ነጥብ ካላቸው ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡበት መሆኑ ነው። ይህ ከ30ኛው የሀገር አቀፍ የትምህርት ጉባዔ ላይ የተገኘው ሰነድ እንደሚያመለክተው ከሆነ፣ በዚሁ ስትሪም ያሉ ተማሪዎች ከቋንቋ እና ማህበራዊ ሳይንስ፤ ቢዝነስ፤ ሥነ-ጥበባት መካከል በራሳቸው ፍላጎትና ዝንባሌ አንዱን መርጠው ይማራሉ።

የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ አካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ከተማ ጥላሁን በነሀሴ ወር 2014 ዓ.ም ከመገናኛ ብዙኃን ጋር ባደረጉር ቆይታ እንደገለጹት፣ ዩኒቨርሲቲው በ2015 የትምህርት ዘመን ሥልጠና የሚሰጥባቸው አዳዲስ የትምህርት አይነቶች የተለዩ ሲሆን፤ እነሱም በማዕድን፣ በቱሪዝም እንዲሁም በግብርና ተፈጥሮ ሀብቶች ዘርፎች ላይ ያተኮሩ ናቸው። ይህ ልየታ፣ አካባቢውንና ያለውን እምቅ ሀብት የምናውቀው እንደ መሆኑ መጠን፣ ተገቢ ልየታና አካትቶ ነው ብለን እናምናለን፤ ይህ በሌሎቹም፣ ለምሳሌ ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲን በመሳሰሉና አርብቶ አደር አካባቢ ያሉ ተቋማት ዘንድም፣ አርብቶ አደሩን በሚመለከትና በሚጠቅም መልኩ (አርብቶ አደሩን የሚመለከቱ የትምህርት አይነቶችን በማካተት) ይደረጋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ይህ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት አይነቶችን መንቀልና መትከል በትምህርት አይነቶች ብቻ የታየ ሳይሆን በራሳቸው በተቋማቱም ተፈፅሞ የነበረ ትልቅ ስህተት ሲሆን፤ ለዚህም በእውቁ "ኮተቤ መምህራን ኮሌጅ" (አሁን "ኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ") ላይ ተፈፅሞ የነበረውን የነቀላና መልሶ ተከላ ተግባር ማስታወስ በቂ ይሆናል።

ወደ ሰሞኑ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ትምህርት ቢሮ ውሳኔ ስንሄድ የምናገኘው ተመሳሳይ ውሳኔን ሲሆን፤ እሱም፣ ክልሉ በማህበራዊ እና ተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፎች በጥናት መስክነት ይወሰዱ ዘንድ የተለያዩ የትምህርት አይነቶችን አካትቶ መገኘቱ ነው። ከተካተቱት የትምህርት አይነቶች መካከልም፣ በተፈጥሮ ሳይንስ በኩል አኒማል ፕሮዳክሽን፣ ማህበረሰብ ጤና፤ በማህበራዊ ዘርፍ በኩል ደግሞ ጆርናሊዝምን እና ሥነልቡናዊ ህክምና ጥቂቶቹ ናቸው።

እንደ ዘመናዊው ሁሉ፣ ከጥንት ጀምሮ አሁንም ድረስ እየተሰጠ ወዳለው፣ መሠረታችን ወደ ሆነው፣ ወደ አብነት ትምህርት ቤት ደግሞ እንሂድና የሀገራችንን የትምህርት ታሪካዊ ዳራ ከ"የትምህርት ዓይነቶች" አኳያ እንመልከት። ከሚመለከታቸው መረጃዎች ሁሉ መረዳት እንደ ተቻለው፣ በአብነት ትምህርት ቤት (ብዙዎቻችን "የቆሎትምህርት ቤት" የምንለው) የሚሰጡ የትምህርት አይነቶች የአንድን ሕዝብ ሁለንተናዊ የዕውቀት ዘርፎች ያካትታሉ።

በሀገራችን የአብነት ትምህርት ቤቶች (በእስልምናው መድረሳም የተለያዩ የትምህርት አይነቶች እንዳሉ ይታወቃል)፡፡ ከሚሰጡት ትምህርቶች ዋና ዋናዎቹ ከዚህ የሚከተሉት (ከአሁኑ ፒኤች-ዲ ጋር በአቻነት የሚታየውን "ትርጓሜ" ትምህርት አይነትን ሳንጨምር) የፊደል እና የንባብ ትምህርት ቤት፣ የቋንቋ ትምህርት ቤት፣ የዜማ ቤትና የቅኔ ትምህርት ቤት ናቸው፡፡

የፊደል እና የንባብ ትምህርት ቤት ፊደል፣ ንባብ፣ ዳዊት እና የመጀመሪያ ደረጃ የዜማ ትምህርት ይሰጣል። ይህም የንባብ እና የጽሑፍ መነሻ የሚሆን የትምህርቱ መሠረተ ነው። ትምህርት ቤቱም ከፊደል ማስቆጠር ስለሚጀምር "የቁጥር፤ የንባብ ትምህርት ቤት" እየተባለም ይጠራል።

የቋንቋ ትምህርት ቤት በቅኔ ቤት ግዕዝ ከነአገባቡ ይሰጣል፤ መምህራኑም ግዕዙን ወደ አማርኛ በመተርጎም ግዕዝን እና አማርኛን አስተባብረውና አዛምደው ያስተምራሉ። ይህም የትምህርት አይነት ሥነ ጽሑፍን፣ አገባብን፣ ንባብን፣ ምሳሌአዊ አነጋገርን እና የንግግር ችሎታ ማሳወቅን ያካትታል። (ይህ የትምህርት አይነት እዚህ እባለቤቶቹ ጋር ተጣለ እንጂ በርካታ ሀገራት እስከ 3ኛ ዲግሪ ድረስ እየሰጡት ይገኛሉ።)

በዜማ ቤት ከውዳሴ ማርያም ዜማ ጀምሮ በመስተጋብር፣ በአርባዕቱ፣ በሠለስቱ፣ በጾመ ድጓው፣ በድጓው፣ በዝማሬና መዋስዕቱ፣ በአቋቋሙ፣ በቅዳሴው እና በሌሎችም ከዜማ ጋር የተያያዙ የትምህርት አይነቶች ኢትዮጵያዊ ዜማ እዚህ የደረሰበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል። የዚህ ትምህርት አባትም ቅዱስ ያሬድ ነው። ይህም የደስታና የኀዘን ጊዜ ዜማዎችን፣ መዝሙርን፣ ማኅሌትን፣ ዘፈንን፣ ወየታን፣ ምሥጋናን፣ እንጉሩጉሮን እና ሌሎች፣ ከዜማ ጋር የተያያዙ ባሕላዊ እና ሃይማኖታዊ የዜማ ቅኝቶችን ሁሉ ያካትታል። (ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ተነቀለ እንጂ እስከዛ ድረስ እንደ አንድ የትምህርት አይነት የሙዚቃ ትምህርትም ከ7ኛ እስከ 10ኛ ክፍል ይሰጥ ነበር።)

በቅኔ ቤት የፈጠራ ችሎታ (creativity) ወቅታዊ ሁኔታዎችን የመረዳት ችሎታ (perspective and understanding) የአእምሮን ጥበብ ተከትሎና ቋንቋን መርጦ፣ አጋኖ ወይም አዋርዶ፤ እንዲሁም፣ መካከለኛ ደረጃ ሰጥቶ ሁኔታዎችን የመግለጥ ችሎታ፤ ታሪክን እና ወቅታዊ ሁኔታዎችን አገናዝቦ የማቅረብ፣ የፍልስፍና፣ የአስተሳሰብ ችሎታ ትምህርት (critical thinking) ይሰጥበታል። የቅኔን ባሕርይ እና የአሰጣጥ ስልት ልብ ብሎ ላስተዋለው ከላይ የዘረዘርናቸውን እና ሌሎችንም ጥበቦች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያጠቃልላል። ከዚህ በተጨማሪ ቅኔ በመቶዎች የሚቆጠሩ መንገዶች ያሉት በመሆኑ እንደየመንገዱ ልዩ ልዩ የአቀራረብ ስልትን እና የቋንቋን አገባባዊ መዋቅርን እና ቋንቋዊ ሙያን ለመማር ያስችላል።

ባጠቃላይ፣ ከላይ የትምህርት አይነቶች ብለንና አጥብበን በመነሳት የትምህርት አይነቶችን እንደየ አውዳቸው ወስደን ሃሳብ ተለዋውጠናል። ከአሀገራችን የትምህርት ታሪካዊ ዳራ አኳያም አጠር ባለ መልኩ ለመዳሰስ ተሞክሯል። የትምህርት አይነቶች እና ርዕዮተ ዓለማት ያላቸውን ተቃርኖ እና ተዛምዶ ጠቅሰን የትምህርት አይነቶችን የመነቀልና መተከልን እጣ ፈንታ አጋርተናል። የመልሶ ተከላና መልሶ ነቀላ ሂደት ምን መልክ እዳለውም ለመቃኘት ሞክረናል። በሂደቱም ሀገራችን ሁሉንም ያለፈችና እያለፈች ያለች ሀገር መሆኗን እያስረገጥን፤ መንቀልም ሆነ መትከል እየተስተዋለ መሆኑን እያሳሰብን የዛሬውን በዚሁ እናጠቃልላለን።

# "ትውልዱ ያለውን ሀብት በቁጠባ ተጠቅሞ ለቀጣዩ ትውልድ በኃላፊነት ስሜት ማስተላለፍ ይጠበቅበታል"

**አቶ ኃይሉ ጀልዴ**
**የአዳማ ከተማ ከንቲባ**



ፎቶ፡- ሔዱሽ አብርሃ

አስቴር ኤልያስ

**በኦሮሚያ ብሔራዊ፣ ክልላዊ መንግሥት፣ በምስራቅ ሸዋ ዞን የምትገኘው የስምጥ ሸለቆዋ እንቁ አዳማ፤ የንግድ፣ የቱሪዝምና የኮንፍረንስ ማዕከል መሆኗ ይታወቃል። በስድስት ክፍለ ከተማ እና በ 19 ወረዳዎች በተዋቀረች በዚህች ከተማ፤ ከቱሪዝምና ከኮንረፍረንስ ከተማነቷ ጎን ለጎን ብልጽግናን መሠረት ያደረጉ ሥራዎች ያስመሰልቸት ተግባራዊ በመደረግ ላይ ናቸው። በከተማዋ ከሚሠሩ ሥራዎች መካከል የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ አንዱ ሲሆን፣ ይህንንም ስኬታማ ለማድረግ ለወጣቶችና ለሌሎቹ ሥራ አጦች የሥራ እድል በመፍጠር ለተሻለ ለውጥ እየተሠራ ነው፡፡**

**ከሰሞኑን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣ የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል የሥራ እድል ፈጠራ ቢሮ በጋራ በመሆን በሥራ እድል ፈጠራ ላይ ያተኮረ የመስክ ምልከታን ለመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች አዘጋጅቶ የነበረ ሲሆን በአዳማ ከተማና በዙሪያዋ እየተከናወነኑ ያሉ ሥራዎችን ማየት ተችሏል። የሥራ እድል የተፈጠረላቸው ወጣቶች፤ በተለያየ የሥራ መስክ በመሠማራታቸው ከተሞች በገጠራማው ክፍል የሚመረተውን ብቻ ተቀምጠው እንዳይጠብቁ ማድረጋቸው አንዱ ማሳያ መሆን መቻላቸውን አስተውለናል፡፡**

**ከሥራ እድል ፈጠራ ጋር ተያይዞ በአዳማ ከተማ እና ዙሪያ ባሉ የተወሰኑ ክፍለ ከተማዎችና ወረዳዎች ላይ ያደረግነውን የመስክ ምልከታ በተመለከተ ማብራሪያ እንዲሰጡን ከአዳማ ከተማ ከንቲባ አቶ ኃይሉ ጀልዴ ጋር ቆይታ አድርገናል።**

**አዲስ ዘመን፡- ከሥራ እድል ፈጠራ ጋር ተያይዞ በተያዘው በጀት ዓመት እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት ምንድን ናቸው?**

**አቶ ኃይሉ፡-** በ2016 በጀት ዓመት ዋና የሥራዎቻችን ማዕከል የሆኑት የሕዝብን ችግር የምንፈታበት ተግባራት ናቸው። ከዚያ ውስጥ እንደከተሞች የተቀመጡ ግቦች አሉ። በክልላችን በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በአዳማ ከተማ ልናሳካ የሚገባን እና የሁሉም እቅድ መነሻ የሚሆነው አራት ግቦች አሉን።

ከዚያ ውስጥ አንዱ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ሲሆን መሠረተ ልማት ዝርጋታን ጨምሮ የትኛውም ሥራ አሊያም ደግሞ የምንሰጠው አገልግሎት ይሁን የሥራ እድል ፈጠራም ድምር ውጤቱ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ነው። አምርተን ወይም ደግሞ ከሌላ ቦታ እንዲመጣ ምቹ ሁኔታን ፈጥረን ሊሆን ይችላል፤ ዋናው ትኩረታችን ግን የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ነው።

በሁለተኛነት ደረጃ የተቀመጠው ግብ ክህሎት እና ፈጠራ ጋር የተያያዘ ነው። ሥራን ሊያበረታታ የሚችል ክህሎት እንደከተማችን መሠራት አለበት የሚል ነው። ይህም ክህሎት ያለው ማኅበረሰብ የመፍጠር እንዲሁም የሥራ ባሕል የማሳደግ ሥራ ነው፡፡

እንደ ከተማ አስተዳደር ልናሳካ ይገባል ብለን በአቅጣጫችን መሠረት የምንተገብረው ሶስተኛው ግብ ደግሞ ኢንተርፕርነርሺፕ ማስፋት እና መፍጠር ነው። ራስን ሆኖ መገኘት እና ኢንተርፕርነር ላይ በአግባቡ መሥራት ነው። ራሱ መንግሥት የኢንተርፕርነርን እሳቤ የተላበሰ እና አመቻች መንግሥት እንዲሆን፣ እስከታች ባለው የመንግሥት መዋቅር በዚህ መልኩ እንዲሆን እየሠራን ነው ያለነው።

በአራተኛ ደረጃ የመንግሥትን አገልግሎት ማሻሻል ነው። እንዲህም ሲባል የሚሰጠውን አገልግሎት ማዘመን ማለት ነው። በሒደትም ወደ ኢ-ገቨርነንስ (E-Governance) የማሸጋገር ሥራ ነው። የእነዚህ ግቦች ዋና ዓላማው በተለይ አራተኛው የመንግሥትን አገልግሎት የማሻሻል እና የማዘመን ግብ ለሶስቱ ግቦች ወሳኝ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- መንግሥት አገልግሎት ማሻሻል ሲባል መገለጫው ምንድን ነው?**

**አቶ ኃይሉ፡-** ጠንካራ መንግሥት የማይኖር ከሆነ፣ አቅዶ መፈጸም የማይችል መንግሥት ከከተማ አስተዳደር እስከወረዳው ድረስ ባለው ሰንሰለት የማይታይ ከሆነ ሶስቱም ግቦቻችን ሊሳኩ አይችሉም። እኛም ስንሠራ የነበረው ይህንን አቅጣጫ ይዘን ነው። ከዚህ አንጻር አራቱንም ግቦች የሥራ እድል ፈጠራ ያካትታል ብዬ ገምታለሁ።

በመሆኑም በ2016 ዓ.ም ዋና የሥራ እድል መፍጠሪያ ማዕከል ያደረግነው ማነሳሻዎችን (ኢንሴቲቮችን) የማሳካት ሥራ ነው፤ ማነሳሻዎቹ (ኢንሴቲቮቹ) ብዙ ናቸው። የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል የሥራ እድል መፍጠር አንዱ ሲሆን፣ ሁለተኛው የሕዝባችንን የኑሮ ሁኔታ እና የአመጋገብ ሥርዓት የመቀየር እና ብቁ ዜጋ የመፍጠርን ራዕይ ነው።

ለምሳሌ የእንቁላል ዶሮ እርባታ ልማት ሥራ አንዱ ማዕከል ነው። ሁለተኛ የወተት ልማት ሥራ ሲሆን፣ ሶስተኛ የሥጋ ልማት ስራ ነው። እነዚህ ብቻ ሳይሆኑ የዓሳማ እርባታ ሥራ፣ የንብ ማነብ፣ ኮቴጅ ኢንዱስትሪ፣ አትክልትና ፍራፍሬንም ጭምር የሚጠቀሱ ሥራዎች ናቸው።

እነዚህን ማዕከል አድርገን በሠራነው ሥራ እስካሁን አጠቃላይ ሲደመር ወደ 900 ሼዶችን ገንብተን የሥራ እድል መፍጠሪያም እንዲሆኑ ለማድረግ እየሠራ ነው፤ እነዚህ ሼዶች ለከተማውም ምርት የሚያቀርቡ ይሆናሉ። የሕዝብንም ችግር ይቀንሳሉ በሚል አቅደን ወደሥራ በገባነው መሠረት እስካሁን ወደ አንድ ሺ 300 በላይ ሼዶችን መገንባት ችለናል።

በእነዚህ በተገነቡ ሼዶች የእንቁላል ዶሮ የሚያረቡትን፣ የወተት ከብት የሚያረቡትን፣ የሚያደልቡት እና ሌሎችንም ወደሥራ ማስገባት ችለናል። በማሳ ደረጃ ደግሞ አትክልት እና ፍራፍሬው ላይ እየሠራን ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት አቡካዶውና ፓፓያ በመተከሉ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሚደርስ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- እነዚህን ሥራዎች የምታከናውኑት እንዴት ነው? የተቀመጠላቸው አሠራር ምን ይመስላል?**

**አቶ ኃይሉ፡-** የዚህ ድምር ውጤት የምናሳካበት ደግሞ አቅጣጫዎች ነበሩን። የምናሳካበት እና የሚኖረን ሀብት ለመለየት የምንሠራበት አቅጣጫ እንዴት ነው የምናሳካው የሚለው አንዱ እቅድ ነው፤ እቅዱ ላይ የተቀመጠውም ማን ምን ይሥራ የሚል ነው። 900 ሼዶችን መገንባት እንዴት እንችላለን? ብርስ ከየት ይመጣል? ይህን ከመንግሥት በጀት ብቻ ብናወጣ ብዙ ቢሊዮን ብር የሚጠይቅ ነው። በመንግሥት ብቻ ስለማንችል በእቅዱ ላይ ያስቀመጥነው ሞዳሊቲውን ለይተን ነበር። በክልል ደረጃ በክቡር ፕሬዚዳንቱ የተቀመጠ አቅጣጫ ስለነበረ እነዚህን ግቦች ለማሳካት አንደኛ የተጠቀምነው የጋራ አቅምን ነው። የጋራ አቅም የምንለው በሌላ ሴክተር በሌላ መልኩ የሚገለጽ ነው።

በሥራ እድል ፈጠራ ባለው ብቻ መግለጽ ካስፈለገ

**የቤተሰብን ብልጽግና የምናረጋግጠው ራሱ ቤተሰቡን በሥራው ተሳታፊ እንዲሆን በመቀስቀስ ነው። ቤተሰብ ውስጥ ያልተጠቀምንበት አቅም አለ**

የአዳማ ባለሀብቶች ብር በማዋጣት ሼድ ሠርተዋል። ካላቸው ማሽነሪ ቀንሰው ሰጥተዋል። በሚችሉት ሁሉ እየደገፉን ነው። ዶሮ እና ላም ገዝተን እንድናስገባ በብዙ ረድተውናል። ስለዚህ አንድ ማዕከል ሙሉ በሙሉ በባለሀብት የተገነባ ሼድ ዶሮ ገብቶበት በመልማት ላይ ይገኛል። ሌሎችም በየወረዳውና በየክፍለ ከተማው በብዛት ተሠርቷል። በጋራ አቅም የሠራነው ከ35 እስከ 40 በመቶ ከጠቅላላው ሥራዎቻችን ይሸፍናል፡፡

ሁለተኛውና ዋናው ነገር የሥራዎቻችን ማጠንጠኛው የሥራ እድል ፈጠራን ቦታ ማእከል ያደረገ እንቅስቃሴ ነው። በዚህ ሒደት ውስጥ ደግሞ የምግብ ዋስትናን የማናረጋገጥ ይሆናል። የምግብ ዋስትናን የምናረጋግጥበት መንገድ አንዱ የቤተሰብ ብልጽግናን ማረጋገጥ ነው፡፡

የቤተሰብን ብልጽግና የምናረጋግጠው ራሱ ቤተሰቡን በሥራው ተሳታፊ እንዲሆን በመቀስቀስ ነው። ቤተሰብ ውስጥ ያልተጠቀምንበት አቅም አለ። መሥራት የሚችል ጉልበት እና ክህሎት አለ። መነሻ ካፒታል አላቸው። ትንሽ ድጋፍ ካደረግንላቸው ምን እንደሚሠሩ በተግባር አይተናል። እሱም ከ55 እስከ 60 በመቶ ይዟል። እኛ ወደሥራ የገባነው እሱን አደራጅተን ነው።

በሶስተኛ ደረጃ የተጠቀምነው የመንግሥት አቅምን ነው፤ መንግሥት ይህን ሁሉ በሃሳብ መምራት እና መሥራት እንዲሁም ሁሉንም አቅሞች ማቀናጀት አለበት። ያለውን ሀብት ለዚህ ሥራ ማዋል አለበት። ከዚህ ጎን ለጎን ሀብትን በቁጠባ የመጠቀም ባህል ማሳደግና ያለውን ሀብት ለሥራ እድል መፍጠሪያና ለአራቱ ግቦች ማሳኪያ እንዲውል መመደብም አለበት። እኛም ያንን መድበን ወደሥራ ገባን፤ በዚህ መልኩም የተወሰኑ ሼዶች መሥራት ችለናል፡፡

ትልቁን ቦታ የያዘው ጉዳይ ሁለት ነው፤ አንደኛው በሥራ እድል ፈጠራ የሕዝብን አቅም በአግባቡ መጠቀም ሲሆን፣ እሱ የስኬት ምንጭ ነው። ሁለተኛው ደግሞ የቤተሰብ አቅምን በደንብ መጠቀም ነው፤ ቤተሰብ በራሱም ይሠራል፤ ተመልሶም የሥራ እድል መፍጠሪያ ማዕከል ሆኗል። እስካሁን ባየነው ነገር ይዘን እየሄድን ያለነው እነዚህን ነው። ብዙ ሥራዎችም በዚህ መልኩ ተሠርተዋል፡፡

በእርግጥ እነዚህን ሥራዎች ገና ስንጀምር

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ወቅታዊ

## "ትውልዱ ያለውን ሀብት በቁጠባ ተጠቅሞ ለቀጣዩ...

ከገጽ 9 የዞረ

የምንፈጽምበት አቅጣጫዎች ላይ ጭምር ግልጽ አልሆነልንም ነበር። ግልጽ ከሆነልን በኋላ እንኳ ሀብት የምናገኝበት መሆኑን አልተረዳነውም ነበር። በማስቀጠል ግን ሥራውን መሥራት ጀመርን፤ ከተማችን ለሼዶች ብቻ ከመቶ ሔክታር በላይ ምንም ካሳ ያልተከፈለበት ያለሥራ ተቀምጦ የነበረን መሬት ለዚህ ሥስራ ማዋል ቻለ።

ምናልባት የተወሰኑት በሕገ ወጥ የተያዙ እንዲሁም በተወሰኑ አካላት ተይዘው የነበሩ ሲሆን፣ ወደሕጋዊነት የማምጣት ሥራ በመሥራት የሥራ እድል መፍጠሪያ ማእከል ሆኖ እንዲያገለግል ማድረግ ቻልን። አጠቃላይ ድምር ውጤቱ ሲታይ ብዙ ሀብት ለዚህ ሥራ ውሏል ማለት ይቻላል። ብዙ ሀብት ለዚህ ሥራ በመዋሉ ብዙ ወጣቶች እና ሥራ አጦች የሥራ እድል አግኝተዋል።

ይህም በገንዘብ ሲሰላ ከአምስት ቢሊዮን ብር በላይ ለሥራው ማዋል ተችሏል። ይህ ማለት ለአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም ለንብ ቀፎ የተደረገውን ዝግጁነት ሳይጨምር ማለት ነው። ይህ ወጪ ከመንግሥት የወጣው ትንሹ ሲሆን፣ እሱም ከሃያ በመቶ አይበልጥም። ምክንያቱም መንግሥት ሥራው ሼድ መገንባት ብቻ አይደለም። የመንግሥት ሃላፊነት ሁሉም ማዕከላት ላይ እንደ ውሃ እና መብራት ያሉ መሠረተ ልማቶች እንዲኖራቸው የማመቻቸቱን ተግባር በትጋት መወጣት ነው፤ ይህ የእኛ ድርሻ ስለሆነ ተግባራዊ አድርገነዋል። ስለዚህ ዘንድሮ በዚህ በኩል ያለውን ችግር ፈተናል ማለት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ግን ጌጠኛ ድንጋይ አንድም ኪሎ ሜትር አልሠራንም። ትኩረታችንን ያደረግነው የሕዝብን ኑሮ መቀየር በሚችሉ ፕሮጀክቶ ላይ ብቻ ነው። በዚህም ሥራችን ውጤት ማየት ችለናል። መሠረተ ልማት ያስፈልጋል። የአስፓልት መንገድ ያስፈልጋል። ነገር ግን ማስቀደም የተገባንን ማስቀደም የግድ ስለሆነ እሱን አስቀድመናል። በእርግጥ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ከዚህ ቀደም ሠርተናል፤ ይሁንና እንደ አሁኑ ትኩረት አልሰጠነውም ነበር። ሥራውን አጠናክረን የጀመርነው ዘንድሮ ነው፤ ይህ በቀጣይ ተጠናክሮ የሚሠራበት ይሆናል፤ የሠራነው ያለንን ሀብት ይበልጥ በቁጠባ በመጠቀም የሕዝብን ችግር የሚፈታ እና ኑሮን የሚያሻሽል እንዲሆን በማድረግ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የሥራ እድል በዚህ መልኩ መፍጠር በመቻላችሁ የመጣ ለውጥ አለ ይላሉ?**

**አቶ ኃይሉ፡-** የሥራ እድል ፈጠራው በርካታ ችግሮችን ፈቷል ብለን እናስባለን። አንደኛ ለብዙ ወጣቶች እና ሥራ አጦች የሥራ እድል ፈጥሯል። የሥራ እድል መፈጠሩ ብቻ ሳይሆን ራሳቸው የሥራ እድል የተፈጠረላቸው አካላት የከተማው ዋስትና መሆን ችለዋል። ብዙ ምርት ወደከተማ እንዲመጣ ምክንያት ሆነዋል። ይህ ማለት ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች መትረፍ ችለዋል እንደ ማለት ነው። በአሁኑ ሰዓት ብዙ ምርት ወደከተማ መጥቷል።

ለዚህ ማሳያ ይሆን ዘንድ ሁለት ነገሮችን መጥቀስ እፈልጋለሁ። ይህን እቅድ ስናቅድ የእንቁላል ዋጋ በአማካይ 13 ብር ነበር። በዓመቱ መጨረሻ ልንደርስበት የነበረውን በስምንተኛ ወር አካባቢ ልናሳካው ችለናል። በአሁኑ ሰዓት የአንድ እንቁላል ዋጋ በአማካይ ከስምንት እስከ ሰባት ብር በመሸጥ ላይ ነው። ይህ ትርጉሙ ብዙ ነው። በአንድ ነገር ላይ ተባብረን የምንሠራ ከሆነ የሕዝባችንን ችግር መፍታት ይቻላል የሚለየውን መለየት ችለናል።

በኮቴጅ ኢንዱስትሪ ብናይ ብዙ አሉ። አጠቃላይ የሥራ እድል ፈጠራ ሴክተር የሁሉም ሴክተር እንዲሆን ተደርጓል። ሁሉም ሴክተር ተሳትፎበታል። የሆነው ነገር ቢኖር በከተማው ያለ ሀብት የሥራ እድል መፍጠሪያ ማዕከል እንዲሆንና ተመልሶ ወደሕዝብ እንዲሰራጭ ነው። በእስካሁኑ ሒደት ጅማሮው ጥሩ የሚባል ነው ብለን ገምግመናል።

**አዲስ ዘመን፡- አቅምን ለማጎልበትና ቴክኖሎጂንም በግብዓትነት ለመጠቀም በቀጣይ ያቀዳችሁት ነገር ይኖር ይሆን?**

**አቶ ኃይሉ፡-** እስካሁን በሠራነው ሥራ ለብዙ ወጣቶች እና ሥራ አጦች በርካታ የሥራ እድል ተፈጥሯል። የሥራ ልምምድም አድርገናል። ያልተለመዱ ሥራዎችን መተግበር ጀምረናል። ብዙ ምርት ማምረትም እንዲሁ ጀምረናል። አሁን ላይ ቆም ብለን ስናይ ግን አንደኛ ቀጣይነቱን ማረጋገጥ አለብን። የጀመርነው በቅርብ ነው። ይሁንና ቀጣይነት ያለው እንዲሆን በአግባቡ መሠራት አለበት።

ለምሳሌ የዶሮ እርባታው ቀጣይነት የሚኖረው የኢንቨስትመንት ወጪውን መቀነስ ስንችል ነው። እንዲህም ሲባል በኢንቨስትመንቱ ላይ የሚወጡ ሀብቶችን እዚሁ በእዚሁ እንዲሆን ማድረግ ነው። ለምሳሌ እንደሚታወቀው የዶሮ መኖ የሚመጣው ከሌላ ቦታ ተጭኖ ነው። ይህን የዶሮ መኖ እዚሁ በማምረት ከሌላ ቦታ ማምጣቱን ሙሉ ለሙሉ መተው አንድ ርምጃ ወደፊት እንደመሄድ ነው።

ይህ አይነት አካሔድ ብቻ ሳይሆን በየማዕከሉ የማዘመን ሥራ መሥራት ይጠበቅብናል። የምናረባው ዶሮ ጤንነት መጠበቅ አለበት። ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ ሥራውን ወደእርሻ እየቀየርን እርሻዎቹ ክሊኒክ እንዲኖራቸው እየሠራን ነው። በአሁኑ ሰዓት እየተከናወነ ያለው እንቅስቃሴ ቀጥለን ለምንሠራው ሥራ ማዕከል እንዲሆን ታስቦ ነው።

ይህ ብቻ ሳይሆን የሥራ እድሉ የተፈጠረላቸው ወጣቶች በተለያየ የሥራ መስክ ግንዛቤው ይኖራቸው ዘንድ ታስቦ ሥልጠና ወስደዋል። ዘንድሮ ወደሥራ የገቡት ወጣቶች በልዩ ኢንሼቲቭ ለመለየት ጥረት አድርገናል። ሙሉ በሙሉ በዲጂታል አይ.ዲ (Digital ID) እንዲመዘገቡና በጉዳዩ ዙሪያ ሥልጠና ወስደው ወደሥራ እንዲገቡ ተደርጓል። አሁንም ሥራው ያለቀ ሳይሆን ክትትልን የሚጠይቅ ነው። በእነርሱ ላይ ያለመሰልቸት መሥራት ያስፈልጋል። ተከታታይ የሆኑ ሥልጠናዎችን በመስጠት ማጠናከር ግድ ይላል፡፡

ሥልጠና መስጠት እና ክትትል ማድረጉ ላይ በአግባቡ ከሠራን ቀጥሎ የሚመጣው የሥራ ባህል ነው። በአሁኑ ወቅት የኮቴጅ ኢንዱስትሪው በብዛት እያመረተ ነው። በኮቴጅ ኢንዱስትሪው ልብስ፣ ጫማ፣ ካልሲ እና የምንገለገልበትን ሁሉ በማምረት ላይ እንገኛለን። በዚህ መልኩ ለገበያ አቅርቦት የሚውል የምንጠቀምባቸውን ቁሳቁስ እናምርት በሚል ወደትግበራ ገብተናል፤ ውጤትም እያመጣን ነው። ነገር ግን ይህን በአግባቡ ማስፋትና ማስቀጠል ይጠይቃል። የምናመርተውን ምርት ይበልጥ ማሳደግን ይጠይቃል። ምርት ለመጨመር የሥራ ባህልን ማሳደግ ወሳኝ ነው። ሌላው ምርት የምንጨምር ከሆነ እና ወጣቶች ጠንክረው እንዲሠሩ በሥልጠና የምንደግፋቸው ከሆነ ቀጥሎ የሚመጣው የገበያ ሁኔታ ነው። የገበያ ችግር እንዳይገጥመን ከወዲሁ በእቅድ ይዘን ስንሠራ ቆይተናል።

ለኢንሼቲቩ በሙሉ የሚሆን አስር የገበያ ማዕከላትን ለመገንባት አቅደን በእስካሁኑ ሒደት ስድስቱን ማጠናቀቅ ችለናል። ስለዚህ በዚህ አይነት ሁኔታ ቀሪዎችንም እየገነባን ከመጣን የገበያ ችግር አይኖርባቸውም። እኛ እየሠራን ያለነው ወጣቶቹ የሥራ እድል እንዲያገኙ ብቻ ሳይሆን ለቀጣይነቱም ዋስትና እንዲሆን ጭምር ነው፡፡

**እኛ እየሠራን ያለነው ወጣቶቹ የሥራ እድል እንዲያገኙ ብቻ ሳይሆን ለቀጣይነቱም ዋስትና እንዲሆን ጭምር ነው**

በጌጠኛ ድንጋይ (በኮብል ስቶን) መንገድ መሥራትን ትተን በጀቱን ወደማምረት የምናዞረው ለሥራ አጦች ሥራ ፈጠርን ለማለት ብቻ አይደለም። ከሥራ እድል ፈጠራ ባሻገር በቀጥታ ጠቀሜታው ኅብረተሰቡ ድረስ እንዲዘልቅ በማሰብ ነው። የአንድ እንቁላል ዋጋ ከ13 ብር ወደ ስምንት ብር ዝቅ ያለው እንዲሁ በምኞት አይደለም። እኛ ለመሥሪያ ቦታ የሚሆኑ ሼዶችን በአግባቡ ገንብተን፣ ለሼዶቹ መብራት አስገብተንና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች አሟልተን ነው። በሌላ አገላለጽ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት የሚከፈል ዋጋ አለው ማለት ነው። ይህ ክፍያ የመጣው ግማሹ በመንግሥት፤ ግማሹም በኅብረተሰቡ ትብብር ነው። ይህ ትብብር ተደምሮ መድረስ ያለበት ራሱ ኅብረተሰቡ ዘንድ ነው። ወደኅብረተሰቡ ይደርስ ዘንድ ገበያ ወሳኝ ነው። ከዚህ የተነሳ የገበያ ሰንሰለቱን በደንብ መጠበቅ ይጠይቃል። ስለዚህ እንደ ከተማ የምናመርተውን ምርት መቆጣጠርና ወደገበያ በአግባቡ መድረስ መቻሉን ማረጋገጥ አለብን። ይህ የሚሆነው ግን በእኛ ደረጃ ባለው ሁኔታ ነው። ሀገራዊ እና ዓለምአማቀፋዊ ሁኔታ ከፍ ሊል ይችላል።

ምርት እንጨምራለን ወጣቶች ይጠነክራሉ። ገበያው ደግሞ አለ፤ ቀጥሎ የሚመጣው ቁጠባ ነው። ወጣቶቹ የሥራ ባህላቸውን ካሳደጉ፣ ያለንን ሀብት ጨርሰን መሔድ አይፈቀድም ማለት ነው። አሁን እያልን ያለነው ትውልድ፣ ያለውን ሀብት በቁጠባ ተጠቅሞ ለቀጣዩ ትውልድ ኃላፊነት በተሞላው ስሜት ማስተላለፍ የሚጠበቅበት ይሆናል። ቀጥሎ ያለው ወጣት ይጠብቃል። አንደኛ የሠራነው ሥራ መሸጋገር አለበት። ተሞክሮውም ሥራውም ሁሉም ዘንድ መድረስ አለበት። ሥራው ራሱ ራሱን መግለጽ መቻል አለበት። ሁለተኛ ደግሞ ሀብቱም መሸጋገር መቻል አለበት፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከወጣቶቹ የሚጠበቀው ምንድን ነው?**

**አቶ ኃይሉ፡-** ቁጠባ ነው፤ ወጣቶቹ እንዲቆጥቡ ማድረግ ይጠበቃል፤ ይህ ግዴታም ጭምር ነው ። ይህን ሒደት መንግሥት ማቀናጀት፣ መደገፍ እና ሁኔታውን መከታተል ይጠበቅበታል። ሁሉም በስንቁ ባንክ አካውንት እንዲኖራቸው ተደርጓል። ስለዚህ መቆጠብ ይጠበቅባቸዋል።

ከቆጠቡ በኋላ በቀጣዩ ዓመት በርካቶቹ ወደ መለስተኛ ኢንዱስትሪ እንዲሁም ወደ ኢንቨስትመንት መሸጋገር መቻል አለባቸው። ለዚህ አሠራር ደግሞ ክልላችን ግልጽ ሕግ አለው። አርሶ አደሩም ጭምር ወደ ኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚገባበት ግልጽ አሠራር አለ። የራሱ የሆነ መመሪያ እና ደንብም ተዘጋጅቶለታል።

ወጣቶችም በዚያ መልኩ በልዩ ማበረታቻ ወደ ኢንቨስትመንት የሚገቡበት ሕግ አለ። ስለሆነም እነርሱን ለዚያ ማዘጋጀት አለብን። የፈጠርነው የሥራ እድል ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ አሁን የያዝናቸውን ይዘን ወደሚቀጥለው መሔድ ይጠበቅብናል። እሱን ደግሞ ጀምረነዋል። ዋና ማነቆዎች ናቸው የሚባሉትን እየፈታን እና መፍትሔ እያበጀን የማበረታቻ ጥቅሎችን እያጠናከርን የምንሔድ ከሆነ አንደኛ እነርሱ የሚሠሩት ሥራ ለሕዝባችን የሚተርፍ ይሆናል። ሁለተኛ ደግሞ የኢንዱስትሪ እና የግብርና ማዕከላት ማቀነባበሪያ እየሰፉ እንዲሔድ ለሚቀጥለው ዘመንም ሰፊ እቅድ ይዘን እየሠራን እንገኛለን።

ግራም ነፈሰ ቀኝ የሥራ እድል መፍጠሪያ የሆኑትን አራቱን ግብ ማሳካት የግድ ነው። በተለይ ደግሞ ሶስቱን ግብ ማለትም የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ የክህሎት መፍጠሪያ ማዕከል ለመሆን እና ኢንተርፐነር መፍለቂያ ለመሆን መትጋት ይጠበቅብናል። ይህን ክንውን ግማሹን የመንግሥት ሴክተሮች የሚይዙት ይሆናል። ግማሹን እዛው ማዕከል ፈጥረን ማሠልጠኑን ተያይዘነዋል። የኮቴጅ ኢንዱስትሪውን ደግሞ ኃላፊነቱን ለኮሌጁ ሰጥተናል። ኮሌጁ በዚህ ዘርፍ በአግባቡ እየሠራ ይገኛል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን መረጃ እናመሰግናለን።**

**አቶ ኃይሉ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡



ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## የወንዶች የውበት ሳሎን

**ሰሚራ በርሀ**

የሰዎችን እይታና ውበት ከሚቀይሩ ነገሮች ውስጥ ፀጉርና አለባበስ ቀዳሚ መሆናቸውን ብዙዎች ይስማሙበታል።

ለወትሮው ስለ ጸጉራቸው ውበትና ጤንነት ተጨንቀው እና ‹‹እንዴት እናድርገው›› ብለው በማሰብ ረጅም የሚባል ሰዓትን በውበት ሳሎን የሚያሳልፉት ሴቶች ናቸው ። በሴቶች የውበት ሳሎን ውስጥ ጸጉርን ከመሥራት አገልግሎት ባሻገር የተለያዩ ከውበት ጋር የተያያዙ እንደ ጥፍር መሰራት ፣ ሜክ አፕ አልያም ደግሞ የተለያዩ ለጸጉር እና ለፊት ተብለው በሚዘጋጁ ውህዶች የጸጉር እና የፊት ስቲም አገልግሎት ዓይነት ሥራዎችም ይከናወናሉ።

በአንጻሩ ወንዶች ጸጉራቸውን የሚስተካከሉበት ሳሎን ደንበኛው በፈለገው አይነት ጸጉሩን ከማስተካከል እንዲሁም ጢሙን ከመላጨትና ከመሳሰለው ውጪ ሌላ አገልግሎት አይሰጥም፤ ወረፋ ከሌለው በቀር በጸጉር ቤቱ ረጅም የሚባል ሰዓትን አንድ ወንድ ላያጠፋ ይችላል ፤ አሁን ላይ ግን ይህ አመለካከት የተቀየረ ይመስላል።

በዛሬ የፋሽን ገጻችን በወንዶች የውበት ሳሎን ሥራ ከሁለት ዓመት በላይ ልምድ ካለው እና በአሁኑ ሰዓት በተለየ መንገድና ሃሳብ የራሱን የውበት ሳሎን በአዲስ መልክ ከፍቶ እየሠራ ካለ ወጣት ጋር ባደረግነው ቆይታ ባለሙያው ጋር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የወንዶች የውበት አጠባበቅ ልምድ እየተቀየረ መምጣቱን ገልጾልናል።

ይህ ባለሙያ ወጣት አድናን ሡልጣን ይባላል። የዞያ የወንዶች የውበት ሳሎን ማናጀር ሲሆን በሙያው ከሁለት ዓመት በላይ ሠርቷል። ከዚህ ቀደም የነበሩ የወንዶች የውበት ሳሎኖች ወንዶች ጸጉራቸውን ተቆርጠው እና አራግፈው የሚሄዱበት ነበር የሚለው አድናን፣ አሁን ግን ይህ ተቀይሮ የወንዶች የውበት ሳሎኖች የሚሰጡት አገልግሎት እየተሻሻለ መምጣቱን ይናገራል።

ዞያ የወንዶች የውበት ሳሎን በመጠኑ ሰፊ የሚባል ሲሆን፣ ከውጭ ለሚመጡ ተገልጋዮች ቤቱን ወደውት ሊስተናገዱበት እንዲችል ተደርጎ ዲዛይኑ ተሠርቷል። የጸጉር መታጠቢያ ቦታ ፣ ጸጉራቸውን የሚስተካከሉበት ሥፍራ እና በልዩነት መገልገል ለሚፈልጉ ደግሞ የቪአይፒ የብቻ ክፍልንም የያዘ ነው። በክፍሉ ውስጥ የተለያዩ ታሪኮችን የሚያስታውሱ በሀገራችን ከሚገኙ ጥንታዊ ከተሞች የጅማን እና የጅማ አባ ጅፋርን ታሪክ የያዙ ምስሎች ተመለከትን። ምስሎቹ በእርግጥም ለክፍሉ ተጨማሪ ውበት ሆነዋል። ‹‹ ትውልድና እድገቴ ጅማ በመሆኑ በሳሎኑ ውስጥ ጅማን የሚያስታውሱ ነገሮችን ማድረግ እፈልጋለሁ ›› ሲል አድናን አብራርቷል፡፡

በሳሎኑ የሚሰጡ አገልግሎቶች አንድ ደንበኛ ጸጉሩን ከተቆረጠ በኋላ እንደ ፍላጎቱ መታጠብ ፣ ቀለም መቀባት ፣ የተለያዩ ለፊት ቆዳ የሚሆኑ ውህዶችን መቀባት ፣ የፊት እና የጸጉር ስቲም አገልግሎትን ማግኘት ይችላል። ‹‹ በቪ አይፒ ክፍል የሚገለገሉ ደንበኞቻችን በአብዛኛው ብቻቸውን ሆነው መስተናገድ የሚፈልጉ ፣ አገልግሎቱን እየተጠቀሙ ራሳቸውን ማረጋጋት እና ማዳመጥ የሚፈልጉ ናቸው ›› ሲል አድናን ጠቅሶ፣ በቪአይፒ ክፍሉ በቤት ውስጥ የተዘጋጁ ልዩ ውህዶችን የሚያገኙበት ሁኔታም እንዳለ ይናገራል ።

ብዙ ሰዎች ጸጉራቸውን ለመሠራት የለመዱበትን እና አንድ ጊዜ ሞክረው የወደዱበት ቤት ደንበኛ ሆነው መዝለቅ ይፈልጋሉ ። ‹‹ታዲያ በዚህ ሥራ አዲስ ደንበኛ ማፍራት ከባድ ይሆን›› ብለን ላቀረብንለት ጥያቄ ሲመልስ ‹‹በእኛ የውበት ሳሎን ደንበኛ ክቡር ነው ። ይህንንም ለምንቀጥራቸው ሠራተኞች ሁሉ እንነግራቸዋለን ። ደንበኞቻችንም የሚፈልጉትን አገልግሎት አግኝተው እስከሚወጡ ድረስ ቡና ቢፈልጉ ውሃ እንደየፍላጎታቸው በነጻነት የማስተናገድ ባህል አለን ። ይህ ተግባር ደግሞ ተመልሰው እንዲመጡ ያደርጋል›› በማለት አገልግሎታቸው ምን ድረስ እንደሆነ አብራርቷል።





አድናን በውበት ሳሎኑ ውስጥ 20 ሠራተኞች ያሉት ሲሆን፣ ጸጉር ከመቁረጥ ባለፈ የተለያዩ አገልግሎቶች ያሉት የውበት ሳሎን ለመክፈት ምክንያት የሆነው እሱ ጸጉሩን ለመስተካከል በሚሄድበት አንድ የውበት ሳሎን ውስጥ ያለው አገልግሎት እና ጥራት ነው።

እሱ እንዳለው፤ አገልግሎቱ በደንበኞች ዘንድ ተቀባይነት በማግኘቱ አብዛኛዎቹ ጸጉራቸውን ከመቆረጥ ባለፈ ሌሎች አገልግሎቶችን ተጠቅመው ይሄዳሉ ። በሴቶች የውበት ሳሎን ውስጥ የተለመደው የጸጉር ስቲም በወንዶች የውበት ሳሎንም አለ። አሁን ወንዶችም ጸጉራቸውን ቂቤ ተቀብተው እና ፊታቸውን በቤቱ የተዘጋጀ ውህድ ተቀብተው ለተወሰነ ደቂቃ የጸጉር እና የፊት ስቲም ውስጥ ይቆያሉ።

‹‹ እኛን የሚያውቁ ደንበኞቻችን የሚፈልጉትን አገልግሎት ይነግሩናል ፤ አዲስ ከሆኑ ደግሞ እንድንገልጽላቸው እና የሚፈልጉትን ይጠቀማሉ›› በማለት አንድ ደንበኛ እነርሱን መርጦ ከመጣ በኋላ የሚያልፈውን ሂደት አብራርቷል፡፡

ወንዶች ምንም እንኳን የተለመደው ወደ ውበት ሳሎን የሚሄዱት ጸጉራቸውን ለመቆረጥና በተለያየ ቅርጽ ለመስተካከል ቢሆንም፣ ጸጉራቸውን አሳድገው የተለያየ አይነት የሹሩባ ዲዛይኖችን የሚሠሩ ፣ ከርል የጸጉር አይነትን ምርጫቸው የሚያደርጉ ደንበኞችም ወደ ሳሎኑ እንደሚመጡ አስታውቋል። የራሳቸውን የሹሩባ ዲዛይን ከማህበራዊ ገጽ ላይ ይዘው የሚመጡም እንዳሉ ይናገራል።

ይህንንም የሚሰሩ ሴቶች በሳሎኑ ውስጥ ይገኛሉ ያለው ወጣት አድናን፣ አንድ ደንበኛ ጸጉሩን ተስተካክሎና ሌሎች አገልግሎቶችን አግኝቶ ለመጨረስ ከ45 ደቂቃ እስከ አንድ ሰዓት ሊወስድበት እንደሚችልም ይገልጻል። አንዳንድ ደንበኞችም አስቀድመው ቀጠሮ በማስያዝ ወደ ሳሎኑ እንደሚመጡ ነግሮናል።

ደንበኛው ለተጠቀመው አገልግሎት የሚጠየቀው ክፍያ እንደ የውበት ሳሎኑ እንደሚለያይ አመልክቶ፣ በዞያ የውበት ሳሎን ጸጉሩን ከተቆረጠ በኋላ ታጥቦ፣ ፊቱን ደግሞ ስክራፕ ተቀብቶ 700 ብር እንደሚከፍል አስታውቋል። የቤቱን ውህድ ከተጠቀመ እስከ አንድ ሺህ ብር እና ሌሎች አገልግሎቶችን እስከ ሁለት ሺህ ብር ድረስ እንደሚከፍልም ጠቁሟል።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ቅድሚያ ለሴት ወይስ ቅድሚያ ለቆንጆ?

**ዋለልኝ አየለ**

ብዙ ጊዜ የምታዘበው ቢሆንም የቅርብ አጋጣሚ ብቻ ልጥቀስ። ባለፈው ሐሙስ ላምበረት አደባባዩ አካባቢ አንዲት ከክፍለ ሀገር እንደመጣች የምታስታውቅ ልጅ መንገድ ልታቋርጥ ሻገር ማለት ስትጀምር አንድ በወጣትነት ዕድሜ ላይ የሚገኝ አሽከርካሪ ልትሻገር በምትችልበት ርቀት ላይ እያለ አካባቢውን የሚያናውጥ ‹‹ክላክስ›› አደረገ። ልጅቷ ተደናግጣ ወደኋላ ተመለሰች። ይህ ብቻ አይደለም! ሲያልፍ አንገቱን አሾልኮ የስድብ መዓት አወረደባት። ‹‹ክላክስ›› ከማጮሁ ጀምሮ በቁጣና በትዝብት ሲያዩት የነበሩ ሰዎችን አላያቸውም።

እንዲህ አይነት ማደነባበር እንኳን እንግዳ ነው ተብሎ ለሚታሰብ ሰው ለከተማው ነዋሪም ያስደነግጣል። ጭራሽ ልጅቷ ተደናብራ አደጋ ላይ እንድትወድቅ የሚያደርግ ነው። ደግሞስ በዚያ ልክ አካባቢውን በሚያናውጥ ሁኔታ ባይሆን ምን ችግር ነበረው? ማስጠንቀቁ ትክክል ሆኖ ሳለ ያንን ሁሉ ቁጣ እና እልህ ምን አመጣው? የማይናገሩና የሚፈሩ ሴቶችን ሲያዩ ለምን ደማቸው ይፈላል? ይህን የምልበት ምክንያት ብዙ ጊዜ ስለታዘብኩት ነው። ምናልባት አለባበሷ እና ገጽታዋ እነርሱ ማየት የሚፈልጉት አይነት ስላልሆነ ይሆን?

‹‹ዘናጭ›› የሚባል አይነት የተራቆተ አለባበስ የለበሰች፣ በሹል ጫማ የተንጠለጠለች ሴት ሲያዩ ግን ገና ከብዙ ሜትር ርቀት ላይ እጃቸውን አውጥተው እንድታልፍ ይማጸናሉ። ይህ ተገቢ እና መሆን ያለበት ነው፤ ዳሩ ግን ነገርየው የሰብዓዊነት ከሆነ ለምን ለተጎሳቆሉት አይሰራም?

እዚህ ላይ ግን ‹‹ዘናጭ›› የሚባሉትን አይሳደቡም፣ አይገላምጡም ማለቴ አይደለም፤ ይህንንም ብዙ ቀን ታዝቤ አውቃለሁ። የሚሳደቡበትና የሚናገሩበት ዓውድ ግን ይለያያል። ‹‹ዘናጭ›› የተባለችዋ በተለምዶ ‹‹መላከፍ›› የሚባለውን አይነት ነው። መጨቃጨቁንም

**በአካላዊ ቁመናም ይሁን በአለባበስ ‹‹ቆንጆ›› የምትባል ሴት ስትመጣ ቦታ ለመስጠት፣ ቅድሚያ ለመስጠት፣ ለሚያስፈልጋት ነገር ለመተባበር የሚረባረበው ብዙ ነው። በዚያው አገልግሎት ቦታ ላይ ግን ጎስቆል ያለች ሴት ካለች ማንም ልብ አይላትም**

ሆነ መሳደቡን እንደ አንድ የመግባቢያ መንገድ በማየት ወይም ‹‹ይሄውም ተስፋ ነው›› በሚል ነው። ከተናገሩም ‹‹ምን ትመስላለች! ሂጂ ወደዚያ!›› አይነት ጭቅጭቆች ናቸው። ያም ሆነ ይህ ይህም ቢሆን የኋላቀርነት መገለጫ የሆነ ነውር ነው። ከዚህም በላይ የከፋው ግን የተጎሳቆሉና ‹‹ዘናጭ›› የማይባሉትን የሚሳደቡበት ቋንቋ በጣም የከፋ መሆኑ ነው። ከልባቸው ተናደው፣ የደም ሥራቸው እየጠወጣጠረ ነው የሚሳደቡ፤ ይህ ከምን የመጣ ይሆን? ለምን እኔ በምፈልገው ልክ አልዘነጠችም ነው? አንደኛው ምክንያት ይህ ሲሆን ሌላኛው ምክንያት ግን ወዲህ ነው፡፡

‹‹ዘናጭ›› የሚባሉት ትንሽም ቢሆን ነቃ ያሉ ናቸው ተብሎ ይታሰባል። መብታቸውን ያስከብራሉ፣ ለነፃነታቸው ይሟገታሉ ተብሎ ይታመናል። ያም ሆኖ ግን እነርሱም ቢሆን ከስድብ ያለፈ ትህትና ያለው ነገር ማየት እምብዛም ነው። እንዲህ አይነቶቹን እናገራለሁ ቢል እጥፍ ስድብ ይጠብቀዋል። እንዲያውም አንዳንዶቹ አስቀድመው የዱቤ የሚሳደቡም አሉ። ‹‹ምናባቱ ይመስላል!›› በማለት በያዘው መኪና አይነትም ሊሳደቡ ይችላሉ። ይህ የስድብ አቻነት ያመጣው ጫና ነው መሰለኝ ዘናጮቹ ላይ ቁጣውና ስድቡ ያን ያህልም ነው፡፡

በአለባበሷ፣ በተክለ ሰውነቷም ሆነ በአጠቃላይ ነገረ ሁኔታዋ ከገጠር የመጣች የመሰለቻቸውን ግን እንደማትሳደብ ያውቃሉ። ስለዚህ የስድብ አምሮታቸውን ሁሉ የሚወጡ እንደዚች አይነቷ ላይ ነው። ‹‹ምናባሽ! እያየሽ አትሄጂም?›› ሲላት ተደናግጣ ዝም ነው የምትለው። የአብዛኞቻችን ችግር ደግሞ ፈሪ ላይ መበርታት ነው። የማይናገሩት ላይ መደንፋት ነው። ይናገሩኛል ተብሎ የሚጠረጠሩት ላይ የማሽቃበጥ ቀብዲ ነው የሚሰጠው። ይህንን በብዙ ሁኔታዎች ልብ ብሎ መታዘብ ይቻላል፡፡

ለምሳሌ፤ አለቃውን ቀና ብሎ የሚናገር ሠራተኛ አይኖርም፤ ወይም እጅግ በጣም ጥቂት ነው። የበታቹን ቁም ስቅል የሚያሳይ ግን መዓት ነው። የታክሲ ረዳት ላይ የሚደነፋው ብዙ ነው፤ ለአንድ የቀበሌ የሥራ ኃላፊን ግን ጠንከር ያለ አስተያየት እንኳን አይሰጥም። አስተናጋጅ ላይ የሚጮኸው ብዙ ነው፤ ባለቤቱ ሲመጣ ግን እየተሽቆጠቆጠ ያስተባብላል፤ ወይም በጣም ተለሳልሶ ይናገራል። እንዲህ አይነት ልማድ ባህላችን የሆነ ሁሉ ይመስላል፡፡

በብዙ የአገልግሎት ቦታዎች ላይ በግርምት አስተውየ አውቃለሁ። በአካላዊ ቁመናም ይሁን በአለባበስ ‹‹ቆንጆ›› የምትባል ሴት ስትመጣ ቦታ ለመስጠት፣ ቅድሚያ ለመስጠት፣ ለሚያስፈልጋት ነገር ለመተባበር የሚረባረበው ብዙ ነው። በዚያው አገልግሎት ቦታ ላይ ግን ጎስቆል ያለች ሴት ካለች ማንም ልብ አይላትም። ምናልባት በዕድሜ የገፋች ወይም የአካል ጉዳት ከሌለባት በስተቀር ቅድሚያ የሚሰጣት የለም። ሲጀመር በዕድሜ የገፋች ካልሆነችና የአካል ጉዳት ከሌለባት ለምን ቅድሚያ ይሰጣታል? ይባል ይሆናል። ‹‹ዘናጭ›› የምትባለዋን ታዲያ ለምን ይረባረቡባታል? ቅድሚያ ለሴት ከተባለ አገልግሎቱን ማግኘት ያለባት የትኛዋም ሴት ናት። የተጎሳቆለች የምትመስለዋን ማንም ልብ ካላላት ግን ነገርየው የሰዋዊነት ሳይሆን የግል ስሜትና ፍላጎት ነው። በእርግጥ ትብብር የሚደረገው በግል ስሜትና ፍላጎት ነው። ቆንጆ ቆንጆዎችን ብቻ እየለዩ ማድረጉ ግን ከሰብዓዊነት ያርቃል። ይህ ነገር ግን ተፈጥሯዊ ይሆን ወይስ በልማድ የመጣ?

ለምሳሌ፤ አንድ በሀሜት የሚነገር ነገር አለ። የሥራ ቅጥር ወይም ሌላ ውድድር ላይ ቆንጆ ሴት ካለች ‹‹ውይ! በቃ ይቺ ናት የምታልፍ!›› እየተባለ በቀልድም በቁም ነገርም ይነገራል። ከዚህ ሁኔታ በመነሳት ይህ ሀሜት እውነትነት ይኖረዋል ብሎ ለመገመት ያስገድዳል። ፈታኙ ወይም አወዳዳሪው አካል ቢያገኛትም ባያገኛትም መጓጓቱ አይቀርም ተብሎ ይገመታል። ይህ ደግሞ ከሕግና መርህ ጋር ብቻ ሳይሆን ከሰብዓዊነትም ጋር ይጣረሳል ማለት ነው። ሰዎችን እኩል ማድረግ ሕግ ብቻ ሳይሆን ሰብዓዊነትም ነው።

እንዲያውም በዚህ ሀሜት ምክንያት አንድ የተዛባ ልማድ ተፈጥሯል። ለምሳሌ፤ አንዲት ቆንጆ የምትባል ሴት (‹‹ውበት እንደ ተመልካቹ ነው›› የሚለውን እንያዝና) አንድ ውድድር ብታልፍ በብቃቷ አይደለም ሊባል ነው ማለት ነው። በብቃቷ መመስገን ሲገባት በሌላ ነገር ነው የሚል ሀሜት ለወርድባት ነው ማለት ነው። ስለዚህ ይህ ሀሜት መቅረት አለበት፣ ይህ ሀሜት ይቀር ዘንድ ደግሞ አካላዊ ገጽታን መሠረት ያደረጉ ግልጽ ልዩነቶች ሊቀሩ ይገባል። የአሠራር ሕግና ደንብ ባላቸው በትልልቅ ቦታዎች ብቻ ሳይሆን እንደ ወረፋ ባሉ ጥቃቅን ነገሮችም ጭምር ማለቴ ነው።

መነሻዎቹ አሽከርካሪዎች ነበሩና ቅድሚያ ለቆንጆ ብቻ ሳይሆን ቅድሚያ ለሰው ስጡ!

# ዓለም አቀፍ




## አሜሪካ ለዓለም ፍጻሜ መሸሸጊያ የሚውል አውሮፕላን እንዲሠራ አዘዘች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አሜሪካ ለዓለም ፍጻሜ መሸሸጊያ የሚውል አውሮፕላን እንዲሠራ አዘዘች።

የዓለማችን ልዕለ ኃያል ሀገር አሜሪካ እንደ ኑክሌር አይነት ጦርነት ቢነሳ ከአደጋ መጠበቅ የሚቻልበት አውሮፕላን እንዲሰራ ማዘዟ ተገልጿል።

እንደ ሮይተርስ ዘገባ አሜሪካ በ1970ዎቹ የተሠራ የክፉ ቀን መጠለያ አውሮፕላን የሠራች ሲሆን፤ ይህ አውሮፕላን አርጅቷል በሚል አዲስ ልዩ አውሮፕላን እንዲሠራ ስምምነት ላይ ተደርሷል።

ለክፉ ቀን ማምለጫ ይሆናል የተባለው ይህ አውሮፕላንም 13 ቢሊዮን ዶላር ወጪ ይፈጃል የተባለ ሲሆን፤ ሴራ ኔቫዳ ኮርፖሬሽን የተሰኘው ኩባንያ አዲሱን አውሮፕላን እንደሚሠራው በዘገባው ላይ ተጠቅሷል።

ኢ-4ቢ የተሰኘ ስያሜ ያለው ይህ አዲስ አውሮፕላን በፈረንጆቹ 2036 ላይ እንደሚጠናቀቅም ተገልጿል።

የአሜሪካ አየር ኃይል ንብረት የሆነው ይህ ልዩ የክፉ ቀን መሸሸጊያ አውሮፕላን የሀገሪቱ ፕሬዚዳንትን ጨምሮ ሌሎች ቁልፍ አመራሮች፣ ባለሙያዎች እና ሌሎች እጅግ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች እና ቴክኖሎጂዎችን ይይዛል ተብሏል።

እንዲሁም አውሮፕላኑ እንደ ኑክሌር ጦርነት፣ አውዳሚ አደጋዎች እና ሌሎች አስጊ ክስተቶች ቢከሰቱ መሪዎች በዚህ አውሮፕላን ላይ በመሆን ትዕዛዝ እና ውሳኔዎችን እንዲያካሂዱ ያገለግላልም ተብሏል።

የመሰብሰቢያ ቢሮዎች፣ የነዳጅ መሙያዎች እና የተግባቦት መሳሪያዎችም ያሉት ሲሆን፤ አሁን በሥራ ላይ ያለው የክፉ ቀን መሸሸጊያ አውሮፕላን ከ2030 በኋላ ከአገልግሎት ውጪ እንደሚሆን ተገልጿል።

## ጋናዊው ግለሰብ ከአንድ ሺህ 100 በላይ ዛፎችን በማቀፍ አዲስ ክብረወሰን አስመዘገበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



የተፈጥሮ ጉዳዮች ማህበራዊ አንቂ እና የስነ ደን ተማሪ የሆነው ጋናዊው አቡበከር ታሂሩ በአንድ ሰዓት ውስጥ በርካታ ዛፎችን በማቀፍ አዲስ የዓለም ክብረ ወሰን አስመዝግቧል።

አቡበከር ታሂሩ የተባለው የ29 ዓመቱ ጋናዊ በአንድ ሰዓት ውስጥ በአጠቃላይ አንድ ሺህ 123 ዛፎችን ያቀፈ ሲሆን፤ በአንድ ደቂቃ ውስጥም በአማካይ 19 ዛፎችን ማቀፍ መቻሉ ነው የተነገረው።

በጋና ገጠራማ አካባቢ በሆነችው ቴፓ ያደገው አቡበከር፤ በአርሶ አደር ቤተሰቦች መካከል ማደጉ ለተፈጥሮ ልዩ ፍቅር እንዲኖረው እንዳደረገው ይናገራል።

አቡበከር በስነ ደን የመጀመሪያ ዲግሪውን በጋና ታዋቂ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ካጠናቀቀ በኋላ በዚሁ የስነ ደን ትምህርት ሁለተኛ ዲግሪውን ለመማር ወደ አሜሪካ ማቅናቱም ነው የተነገረው።

አዲስ ክብረወሰን የማስመዝገብ ሙከራውን ያካሄደው አሁን በሚገኝባት ሀገረ አሜሪካ ሲሆን፤ ክብረወሰኑን ያስመዘገበውም በአላባማ ውስጥ በሚገኘው ቱስኪጊ ብሔራዊ ደን ውስጥ ነው።

በዚህም አቡበከር ዛፎቹን በሁለት እጆቹ ጥብቅ እያደረገ ሲያቅፍ የነበረ ሲሆን፤ በሙከራው ወቅትም አንድን ዛፍ ደግሞ ማቀፍ እንደማይቻል እና በሚያቅፍበት ጊዜ በዛፎቹ ላይ ጉዳት ካደረሰም ሙከራውን እንደሚሰርዘው ቅድመ ሁኔታ ተቀምጦለት ነበር።

አቡበከር ስለ ዛፍ ማቀፍ ክብረ ወሰኑ ሲናገር፤ “በጣም ከባዱ ነገር በዛፎቹ መካከል የሚደረገው ምልልስ እንዲሁም እያንዳንዱ ዛፍ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት መታቀፉን ማረጋገጥ ነበር” ብሏል።

ክብረወሰን የመስበር ሙከራውን የበለጠ ከባድ አድርጎበት የነበረው ሌላኛው ነገር ደግሞ የረመዳን ወቅት መሆኑ እና በመሀል ውሃ መጠጣት አለመቻሉ እንደሆነም አቡበከር ተናግሯል።

ያም ሆኖ አቡበከር ክብረወሰን የመስበር ሙከራውን ያሳካ ሲሆን፤ በየሦስት ሰከንድ ልዩነት አንድ ዛፍ በማቀፍ በአጠቃላይ 700 ዛፎችን በአንድ ሰዓት ውስጥ ማቀፉ አቡበከርን የክብወሰን ባለቤት ለመሆን በቂው ነበር።

ሆኖም ግን ጋናዊው አቡበከር በአንድ ደቂቃ በአማካኝ 19 ዛፎችን በማቀፍ በአጠቃላይ በአንድ ሰዓት ውስጥ አንድ ሺህ 123 ዛፎችን በማቀፍ ክብረወሰኑን የግሉ አድርጓል።

**ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም**

# 2 ነጥብ 6 ሚሊዮን ጎልማሶችን ያሳተፈው ፕሮግራም

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

የጎልማሶች ትምህርት ከመሠረታዊ ዕውቀት አንስቶ ግላዊ ልምምዶች በማካተት የዕድሜ ልክ ተማሪ በመሆን የከፍተኛ ደረጃ ዲግሪዎችን ማግኘትንም ይጨምራል። በዚህ ትምህርት ጎልማሶች ምርታማ ሠራተኛ ይሆናሉ፤ ቤተሰባቸውን በአግባቡ ይመራሉ፤ የገቢ ምንጫቸውን ይጨምራሉ።

መርሀ ግብሩ ግልማሶች በልምድ የሚያውቁትን በቀለም ትምህርት እንዲረዱትና እንዲተገብሩት እገዛ ያደርግላቸዋል። የሚፈልጓቸውን መሠረታዊ ክህሎቶች እንዲያገኙና ወደ ተግባር በልበ ሙሉነት እንዲቀይሩት ይታገዙበታል። ከሁሉም በላይ ከእድሜ እኩዮቻቸው ጋር መማር ባለመቻላቸው እንዳይሰማቸውና እድሜ ሳይገድባቸው በመደበኛው ትምህርት በመግባት ያሰቡት ትምህርት ደረጃ ላይ መድረስ የሚችሉበት ነው። ምክንያቱም ይህ መርሀ ግብር እንደመደበኛው ቀጣይነት ያለው ትምህርት የሚሰጥበት ፕሮግራም ነው።

ፕሮግራሙ በርካቶችን ተጠቃሚ አድርጓል። የፌዴራል ትምህርት ሚኒስቴር ከክልል ትምህርት ቢሮዎች ጋር በመተባበር የመደበኛ ትምህርት እድል ማግኘት ያልቻለውን የማህበረሰብ ክፍል የትምህርት ፍላጎት ለማርካት በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል። በተለይም አምራች የሆነውን የኅብረተሰብ ክፍል በትምህርት ተደራሽ ለማድረግ ቀደም ሲል የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራምን ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል።

ነገር ግን የሚፈለገውን ያህል ውጤት ማምጣት ባለመቻሉ ለጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ትኩረት ተሰጥቶት በመሪ ሥራ አስፈጻሚ ደረጃ ተዋቅሮ የተለያዩ ፕሮግራሞችን በማካተት እየሠራ ይገኛል። የሥራ ክፍሉ ሁለት ዴስኮችን አቅፎ ይዟል። አንዱ የጎልማሶች መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ዴስክ ነው። የዴስኩ ኃላፊ ወይዘሮ በቀለች ተስፋዬ ይባላሉ። የዛሬ አምዳችን ትኩረት የዴስኩ የሥራ እንቅስቃሴ ይሆናል። መረጃና ማብራሪያ የሰጡን የዴስኩ ኃላፊ ናቸው።

እንደወይዘሮ በቀለች ገለፃ የጎልማሶች መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ዴስክ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል። ቀደም ሲል በተለያየ ምክንያት የትምህርት ዕድል ያላገኙ ዕድሜያቸው 15 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆናቸው ወጣቶችና ጎልማሶች ማንበብ፣ መጻፍና ማስላት እንዲችሉ ለማድረግ ሲሰጥ የነበረውን የሁለት ዓመት የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርትን በመከለስ በአንድ ዓመት የሚጠናቀቅ የጎልማሶች መሠረታዊ ትምህርት እየተሰጠ ይገኛል።

በተለያየ ሁኔታ ማለትም በቤተ-ክህነት (በአብነት)፣ በመስጊድ (በመድረሳ) እንዲሁም በራሳቸው ተምረው ማንበብ፣ መጻፍና ማስላት የሚችሉ “በትምህርት ብርሃን ምዘና” በማሳተፍ እውቅና በመስጠት በትምህርት ብርሃን ምዘናው 50 በመቶ እና በላይ ያመጡትን የ2ኛ ክፍል ካጠናቀቁት ጋር አቻ ምስክር ወረቀት



ወይዘሮ በቀለች ተስፋዬ

እንዲሰጣቸው ይደረጋል። ይህም ሰልጣኞቹ በሚፈልጉት የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላል።

እንደ ኃላፊዋ ማብራሪያ፤ ዴስኩ ምዘና ከመስጠት ባሻገር ከላይ የተጠቀሱ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ በርካታ መመሪያዎችና ማኑዋሎችን ያዘጋጃል። ሥራ ላይ እንዲውሉም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ለአብነትም የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ስትራቴጂ፣ የጎልማሶች መሰረታዊ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ፣ የጎልማሶች መሰረታዊ ትምህርት የአተገባበር መመሪያ፣ የመማማር ብቃት መለኪያ (MLC)፣ የትምህርት ብርሃን ምዘና መመሪያ፣ የበጎ ፈቃደኞ አገልግሎት ማኑዋል፣ የሽግግር መመሪያ፣ የአመቻቾች ማመቻቻ ማኑዋል እና የአዲስ አንባቢያን ጽሁፍ ናሙና በዋናነት የተጀዘጋጁና ለክልሎች የተሰራጩ ናቸው።

ከሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በጎልማሶች መሠረታዊ ትምህርት የመማማሪያ ፅሁፍ አዘገጃጀት፣ የጎልማሶች መሠረታዊ ትምህርት የማመቻቸት ሥነ-ዘዴ፣ የትምህርት ብርሃን ምዘና አሰጣጥ፣ የክትትልና ድጋፍ አገልግሎት ላይ የአሰልጣኞች ስልጠና መሰጠቱን ወይዘሮ በቀለች አመላክተዋል።

በ2016 ዓ.ም ብቻ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስዳደሮች ሦስት ሚሊዮን ወጣቶችና ጎልማሶችን በመሠረታዊ የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ለማሳተፍ እቅድ ተይዞ እስከ አሁን ባለው አፈጻጸም 2 ነጥብ 6 ሚሊዮን ጎልማሶችን ማሳተፍ እንደተቻለ ጠቁመዋል።

በትምህርት ብርሃን ምዘናም ቢሆን እንዲሁ የተከናወኑ ተግባራት መኖራቸውን አንስተዋል። በዚህም እስከ 800 ሺህ የሚሆኑ ወጣቶችና ጎልማሶችን ለማሳተፍ ታቅዶ እየተሰራ ያለ ተግባር ነው ብለዋል። እስከ አሁን ድረስ ደግሞ 727 ሺህ 212 ወጣቶችና ጎልማሶች ምዘናውን ወስደዋል። ምዘናውን ከወሰዱት መካከል 622 ሺህ 87 ጎልማሶች ምዘናውን ማለፋቸውን አስረድተዋል።

# ስፖርት





## ‹‹በዕድሜ ጉዳይ የማያዳግም ርምጃ ሊወሰድ ይገባል››

- የአትሌቲክስ ቤተሰቦች

ዓስማየሁ ግዛው

የኢትዮጵያ ታዳጊ ፕሮጀክቶች አትሌቲክስ ቻምፒዮና ዘንድሮ ለ2ኛ ጊዜ በሃዋሳ ከተማ ተካሂዷል። ውድድሩ ዕድሜያቸው ከ16 ዓመት በታች እና ከ18 ዓመት በታች በታዳጊ ፕሮጀክቶች የታቀፉ አትሌቶች የሚሳተፉበት ቢሆንም ከዕድሜ ማጭበርበር ጋር ተያይዞ ጥያቄ የሚነሳባቸው ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች መኖራቸው ተስተውሏል። በዚህም ላይ አስተያየታቸውን የሰጡ አሠልጣኞችና ታዳጊ አትሌቶች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የማያዳግም ርምጃ መወሰድ እንደሚኖርበት አሳስበዋል። ፌዴሬሽኑም በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የዕድሜ ማጭበርበር ችግር መኖሩን አምኗል።

የኢትዮጵያ ታዳጊ ፕሮጀክቶች አትሌቲክስ ቻምፒዮና ባለፉት ቀናት በርከት ያሉ የማጣርያና የፍጻሜ ፉክክሮችን እያስመለከተ ቆይቷል። ታዳጊ አትሌቶች የውድድር ዕድልን እና ልምድን የሚቀስሙበት መድረክ ቢሆንም ከዕድሜ ማጭበርበር ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉት ችግሮች በታዳጊ አትሌቶች ዘንድ የሞራል ውድቀትን እንዳያደርስ ያሰጋል። ችግሩ መፍትሔ ያልተገኘለት ጉዳይ ሆኖ መቀጠሉን ተከትሎም ሀገርን የሚወክሉ ተተኪ አትሌቶች እንዳይፈጠሩ እንቅፋት መሆኑ አይቀርም፡፡

በአትሌቲክሱ ላይ የተጋረጠውን ይህንን ችግር ለማስቀረትም አስተማሪና የማያዳግም ርምጃ መወሰድ እንደሚኖርበት አትሌቶች፣ አሠልጣኞች እና የቴክኒክ ኃላፊዎች ገልጸዋል። በክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮች እና በብሄራዊ ፌዴሬሽኑም በትኩረት ሊሠራ ይገባል። በማጭበርበር የሚገኘው ውጤት ጊዜያዊና ስፖርቱን የሚያቀጭጭ ነውና።

ታዳጊ ሞገስ ጌታሁን የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልልን በመወከል ከ16 ዓመት በታች በ800 ሜትር 2ኛ ደረጃን ይዞ ያጠናቀቀ ታዳጊ ነው። እድሜን በሚመለከት የምርመራው ሁኔታ መጠናከር እንደሚኖርበትና የዛሬን ውጤት ብቻ ሳይሆን በትክክለኛ ዕድሜ ለሚወዳደሩ አትሌቶች መንገድ መከፈት እንደሚኖርበት ይልጻል። ለጊዜያዊ ውጤት ተብሎ የሚደረገውን የዕድሜ ማጭበርበር ለማስቀረትም ትኩረት ሊሰጥ ያስፈልጋልም ባይ ነው።

ከትግራይ ክልል ከ18 ዓመት በታች 3 ሺ ሜትር ውድድር ሶስተኛ ደረጃን የያዘችው ህልፈይ ካህሳይ፤ ውድድሩ ጥሩ ፉክክር የተስተናገደበት ቢሆንም የዕድሜ ተገቢነት ክፍተት መኖሩን ጠቁማለች። ይህ በመሆኑም በውጤቷ ላይ ተጽዕኖ ያሳደረ ሲሆን፤ በቀጣይ መስተካከል እንደሚኖርበት ገልጻለች። ሌላኛዋ የትግራይ ክልልን የወከለችው ተወዳዳሪ ማዕረግ ዓለም ከ18 ዓመት በታች 800 ሜትር ሁለተኛ ነው ያጠናቀቀችው። ፉክክር በተስተናገደበት ውድድር ከዕድሜ ጋር ተያይዞ የሚታዩ ክፍተቶች መስተካከል እንደሚኖርበት ገልጻለች። አዲስ አበባን ከ18 ዓመት በታች 800 ሜትር ወክላ አንደኛ የወጣችው ኤደን ከተማም በተመሳሳይ የዕድሜ ፍትሃዊነት ላይ እርማት እንደሚያስፈልግ ገልጻለች።

የደቡብ ኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የቴክኒክ ኃላፊ አቶ መንግስቱ ጋልቹ በበኩላቸው፣ የታዳጊ ወጣቶች ውድድር ታዳጊ አትሌቶችን ለማፍራት የሚደረግ እንደሆነና የሚሻሻሉ ነገሮች ቢኖሩም ጅማሮው መልካም መሆኑን ይገልጻሉ። ሀገርን የሚወክሉ አትሌቶችን እየተመለከቱ የሚያድጉ ሠልጣኞች እንደመሆናቸው ክልሎች፣ ፕሮጀክቶችና አሠልጣኞች መሥራት ያለባቸው የእድሜ ጣራ ላይ ሊሆን ይገባል። ፌዴሬሽኑም መታረም የሚገባውን አርሞ ማለፍ ይኖርበታል። ባለፈው ዓመት ከነበረው ሁኔታ መሻሻል ቢኖርም አሁንም ግን ክልሎች በዕድሜ ጉዳይ ኃላፊነትን መወጣትና ፌዴሬሽኑም የጠበቀና የማይቆራረጥ ርምጃ መውሰድ አለበት።

የትግራይ ክልል አትሌቲክስ ቡድን ዋና አሠልጣኝ ሰለሞን ጸጋይ፤ ውድድሩ ጥሩ ቢሆንም ከዕድሜ ተገቢነት ጋር ተያይዞ ተገቢነት እንደሌለ ይጠቁማሉ። ትክክለኛውን የዕድሜ እርከን ጠብቀው የሚወዳደሩ እንዳሉ ሁሉ ከተፈቀደው ዕድሜ በላይ የሆኑ አትሌቶችን ያሰለፉ በመኖራቸው ፌዴሬሽኑ የማስተካከያ ርምጃ መውሰድ ይኖርበታል። በዕድሜ ማጭበርበር ምክንያት ወደ ፊት ኢትዮጵያ የምትኮራበት ውጤት ሊጠፋ ይችላል። በፌዴሬሽኑ በኩል ለበርካታ ዓመታት ችግሩ ሲፈጠር ርምጃ ይወሰዳል ቢባልም አስተማሪ አለመሆኑንና ክልሎች ተገቢውን አትሌት የማያሰልፉ ከሆነ ተቀጥቶ ለሌሎች ማስተማርያ ማድረግ እንደሚኖርበትም አመላክተዋል።



**በፕሮጀክቶች ቻምፒዮና በተገቢው እድሜ የተወዳደሩ ክልሎች ቢኖሩም ችግሩ አሁንም እንዳልተቀረፈ ታይቷል፣**

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የተሳትፎና ውድድር ዳይሬክተር አቶ አስፋው ዳኜ፣ ውድድሩ አስፈላጊው ዝግጅት ተደርጎ እየተካሄደ ቢሆንም ከዕድሜ አንጻር እንደተጠበቀው አለመሆኑን አስረድተዋል። ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አትሌቶችን ሕጋዊ ከሆነ የህክምና ተቋም አስመርምረው በትክክለኛ የዕድሜ ደረጃ የሚገኙትን እንዲያሳትፉ መልዕክቱን አስተላልፏል። ነገር ግን አሠልጣኞችና የሚመለከታቸው አካላት ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው ሁኔታው ቀጥሏል።

በእርግጥም በሁሉም የውድድሩ ተካፋይ ክልልና ከተማ አስተዳደር የዕድሜ ችግሮች ይስተዋላሉ። በተወዳዳሪ አትሌቶች ምትክ በትክክለኛ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ሠልጣኞች መቅረታቸውንም ይገልጻሉ። ጉዳዩ ስህተትም ወንጀልም በመሆኑ የአሠልጣኞች፣ ቡድን መሪዎችና የቴክኒክ ኃላፊዎች የቤት ሥራ መሆን ይኖርበታል። ለተከሰተው ጥፋትም በሚቀርበው ሪፖርት መሠረት ውሳኔው በቀጣይ እንደሚገለጽም አስረግጠዋል።


## የጨረታ ማስታወቂያ የጨረታ ቁ-01/2016

በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን አስተዳደር መርቲ ወረዳ የአቦምሳ ማዘጋጃ ቤት በ2016 የበጀት ዓመት ለመስሪያ ቤቱ አገልግሎት የሚውል ሲኖ ትራክ መኪናና ባክሎደር (ባክኦ ሎደር) በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

**በመሆኑም፡-**

1. ለተጠየቁት የግዢ ዳምፕ ትራክ መኪናና ባክሎደር (ባክኦ ሎደር) ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸውና የዘመኑን ግብር ከፍለው የንግድ ፈቃዳቸውን ያሳደሱ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር (Tax Payer Registration No) የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ፤ እና በፌዴራል፤ በክልል ወይም በዞን ገንዘብ ጽ/ቤት ወይም በግዢዎችና ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ የአቅራቢነት የምስክር ወረቀት ያላቸው ዋናውንና ኮፒውን ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ።
2. ተጫራቾች በዳምፕ ትራክ መኪናና ባክሎደር (ባክኦ ሎደር) የጨረታ ሰነድ የማይመለስ ብር 700.00 (ሰባት መቶ ) በአቦምሳ ማዘጋጃ ቤት ስም ኦሮሚያ ሕብረት ሥራ ባንክ በሂሳብ ቁጥር 1000008959928 ገቢ በማድረግ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ለ15 ተከታታይ የሥራ ቀናት የጽ/ቤቱ የግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ቢሮ ቁጥር 2 ድረስ በመቅረብ መውሰድ ይችላሉ፡፡
3. ተጫራቾች ከግብር ሰብሳቢው መ/ቤት የዘመኑን ግብር አጠናቀው ለመክፈላቸው እና ጨረታ ለመሳተፍ የሚያስችላቸውን ደብዳቤ ማቅረብ አለባቸው፡፡
4. ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን የዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ በመሙላት በዝግ ፖስታ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ እስከ 16ኛው የሥራ ቀናት ማቅረብ የሚኖርባቸው ሲሆን፤ ጨረታው በ16ኛው የሥራ ቀን ከቀኑ7፡30 ሰዓት ታሽጎ በዚሁ ዕለት ከቀኑ በ8፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት የጽ/ቤቱ ይከፈታል፡፡
5. ማንኛውም ተጫራች ዳምፕ ትራክ መኪናና ባክሎደር (ባክኦ ሎደር) ሰነድ የጨረታ ማስከበሪያ ለእያንዳንዱ ሰነድ ማስከበሪያ ብር 150,000 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ) በአቅራቢያችሁ በሚገኝ የታወቀ ባንክ በክፍያ ማዘዣ (CPO) ብቻ ማቅረብ አለባቸው፡፡
6. አሸናፊው ተጫራች ያለምንም የአቅርቦት ችግር አስተማማኝ የሆነ ዳምፕ ትራክ መኪናና ባክሎደር (ባክኦ ሎደር) ክምችት ያለውና ማሺኖቹን በራሱ የማጓጓዣ ወጪ አቦምሳ ከተማ ውስጥ በሚገኘው ማዘጋጃ ጽ/ቤት ድረስ አምጥቶ ማስረከብ ይኖርበታል፡፡
7. ማዘጋጃ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

ለተጨማሪ ማብራሪያ ስ.ቁጥር 0910942641, 0912383025, 0910746302, ይጠይቁ

**በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን አስተዳደር መርቲ ወረዳ የአቦምሳ ማዘጋጃ ቤት**

## የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቤት ቁጥር 122 ግብር ከፋይ (TIN) 0001289082 የሚታወቀው ሃይረዲን ጁሀር : የሱፍ በሚል በግብር ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብንበት ከአራዳ ክ/ከ/አ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፈቃድ በማግኘት ከምንጠቀምባቸው ደረሰኞች ውስጥ ከቁጥር ከ001-0037 የተሰራበት፣ 0038-2500 ያልተሰራበት ገንዘብ መክፈያ ደረሰኝ ከ001-500 ያልተሰራበት የእጅ በእጅ የመክፈያ ደረሰኝ ስለጠፋብኝ በማናቸውም አካል እጅ ውስጥ ገብተው ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡ ፡ ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈጸሙ በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት ለአራዳ ክ/ከ/አ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብርእንዲያደርጉ እናስታውቃለን፡፡

## የግብር ከፋይ ስም፡- ሃይረዲን ጁሀር

## ማስታወቂያ

የህዛል ሪል እስቴት አክሲዮን ማህበር 44 ነባር ባለአክሲዮኖች ያላቸውን አክሲዮን ለ44 አዲስ ገቢ ባለአክሲዮኖች አክሲዮናቸውን ሙሉ በሙሉ በሽያጭ ለማስተላለፍ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡

የነባር ባለአክሲዮኖች (ሻጭ) አድራሻ

44 ባለአክሲዮኖች - አአ በአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የቤ.ቁ 50/ለ

የአዲስ ገቢ ባለአክሲዮኖች (ገዥ) አድራሻ

44 ባለአክሲዮኖች - አአ በአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የቤ.ቁ 50/ለ

ከላይ በህዛል ሪል እስቴት አክሲዮን ማህበር የተገለጸላቸው አመልካቾች በዚህ የ15 ቀናት የተቃወሞ ጥሪ ጊዜያት ውስጥ ውህደቱ (የአክሲዮን በሽያጭ ማስተላለፍ እንዳይመዘገብ ተቃውሞ ከቀረበበት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ይህንኑ ለሚመለከተው አካል የሚያሳውቅ ሲሆን ተቃውሞ ካልቀረበ ግን የተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያው ከተጠናቀቀበት ጊዜ ጀምሮ በሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን የአክሲዮን ማህበራት አደረጃጀት ድጋፍና የውህደት ዴስክ በመቅረብ የአክሲዮን ሽያጭ ማስታወቂያ ደብዳቤ የሚሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር**